ናፍቆት ETHIOPIA

እውነትን ግዛት፤ አትሸጣት!

September / October, 2013

መስከረም ፪ ሺሕ ፯ ዓ.ም.





ጥቂት ስለ ዘመን አቆጣጠር

ኢትዮጵያን ጨምሮ የራሳቸው የዘመን አቆጣጠር ያላቸው ሀገራት የባሕረ ሐሳባቸው (Calendar) መሠረት ጥንታዊ አምልኮአቸው ወይም አንዳች የተፈጥሮ ክስተት አልያም ከነዚህ ጋ የተያያዘ ጉዳይ ነው። በተለይ ጨረቃና ፀሐይ በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች አቆጣጠሮች ዐይት ላይ መሠረታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋሉ። የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በፀሐይ ዐይት ላይ የተመሠረተ (Solar) ሲሆን የእስራኤላውያንና የሒጂራ (እስልምና) አቆጣጠር ደግሞ ጨረቃን መሠረት ያደረገ (Lunar) ነው።



ጲላጦስ

አንዳንድ ሰዎች የሚናገሩት፣ የሚያምኑበት፣ በየመድረኩ የሚደሰኩሩት፣ አጠናን ብለው የሚተነትኑት፣ ከልብ ጓደኞቻቸው ጋር ሲያወጉ የሚዘረገዙት፣ «ቢሆን መልካም ነው» የሚሉት እና በቦታው ላይ ሆነው የሚፈጽሙት የሚለያየው ለእውነት መቆም የሚያስከፍለው ዋጋ ስላለ ነው።




ታላቁ የታሪክ ምሑር

ታላላቅ የታሪክ ምሁራንን እንዳፈራም የሚነገርላቸው ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ከሚፈቷቸው ሥራዎቻቸው መካከል በሚገባር ቀደምትነት የሚጠቀስላቸው "Church and state in Ethiopia 1270-1527" የሚለው ነው።



አንደበት አእምሮ ወይም አንጎል ማለት ብቻ እንዳልሆነና በተለይም የስሜት የፍርድ አሰጣጥና የሚዛናዊነትን ተግባር የሚያካትተው የአ አእምሮ ክፍል አሠራር መዳበርና አለመዳበርን አጠቃሎ የሚይዝ፤ የቸግርን አፈታት በብዙ አቅጣጫ ለመመልከት የሚያስችል የአእምሮአችን ረቂቅ አስተሳሰብ ነው።



ኢሕአዴግን መቃወም ሌላ!! ... ሽብርተኛት ሌላ!!


ቀደምት የኃይማኖት አባቶች ይዘው የቆዩትን አመለካከትና እምነት በሰላማዊና በፍቃድ ላይ በተመሰረተ መንገድ ሳይሆን በኃይል በማስወገድ እና እኛ ባልናችሁ መንገድ ብቻ አምልኩ አለበለዚያ ‹መናፊቁን› ናችሁ ሲል የሚዝተው የእነ መሐመድ ቢን አብድል-ዋሀብ አስተምህሮ በማስፈራራት አላምን ያለውን በእሳት ከማጋየት፣ በቦምብ ከመበጣጠስ ወይም በገጀራ ከመቆራረጥ ወደ ኋላ ብሎ የሚያውቅበት ወቅት የለም።

For advertisement and Sales, please contact
@ 703-256-9113 , 202-253-4414, 703-628-5716 or 773-746-9513

በዚህ መጽሔት ላይ የወጡ ማናቸውም ጽሑፎች የአዘጋጁን ወይም የቦርድ አባላትን አመለካከት አያንጸባርቁም። በመጽሔቱ ላይ የወጡትን ሥራዎች ያለ አሳታሚው ፍቃድ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መልሶ ማሳተም በፍፁም ክልክል ነው።

NAFQOT Ethiopia is an Independent Magazine published Monthly in Amharic and English. Views expressed do not necessarily reflect that its editors and advisors. Fully or partially copying of the articles is prohibited.

አዘጋጁ



በአዲሱ የኢትዮጵያውያን ዘመን ስለ አዲስ ነገር ማለት ፈልጌ ነበር። ለምሳሌ በአዲሱ ዓመት ምን ተመኝታችኋል? ምን ወስናችኋል? በሕይወታችሁ ውስጥስ ምን ዓይነት ለውጥ ለማምጣት አስባችኋል እና ሌሎችንም። ነገር ግን እነዚህን በማንሳት የእንባቢያንን ጊዜ ማጣበብ አልፈለኩም። ለምን ቢባል በየዓመቱ በዚሁ ጉዳይ ብዙ ብዬበታለሁ የሚለው ሚዛኑ ከፍ ስላለ።

በቅድሚያ ግን መላውን የናፍቆት ኢትዮጵያ መጽሔት አንባቢያን እና መላውን የሃገሬን ሕዝብ «እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ በሰላም አሸጋገራችሁ» እላለሁ።

ከላይ እንዳልኩት በአዲሱ ዘመን ላይ ስለ አዲሱ ውሳኔያችሁ መጠየቅም መወያየትም አልፈለኩም ብያለሁ። ከዚህ ይልቅ የቀን ዳክዛ የለሊት ቅዠት ስለሆነብኝ ስለ ባንዲራችን ማንሳት ፈለኩ። ወደ ባንዲራችን ወደታዘብኩት በጥልቀት ከመግባቴ በፊት ግን አንዳንድ ጥያቄዎችን ማንሳት እፈልጋለሁ። ጥያቄውም ሁላችንንም ስለሚመለከት ኢትዮጵያዊ የሆነ እና በአጋጣሚ ይኽንን ጽሑፍ የሚያነብ ሁሉ ራሱን ለአንድአፍታ እንዲጠይቅ ለመነደርደሪያ እንዲሆንኝ በጥያቄ ልጅምር።

ለመሆኑ የአንድ አገር ባንዲራ ምንድነው? የምንስ ምልክት ነው? ብለን መጠየቃችን ወይም መልሱን ለማወቅ መፈለጋችን አይቀሬ ነው። በእርግጥስ እንዲህ በባንዲራ በሽታ ከመወረራችን በፊት ስለሃገራችን ባንዲራ ያለን አመለካከት እና ትርጉም ምን ነበር? በያዝነው ዘመን በየከፍለ ዓለማቱ በሚደረጉ ሰላማዊ ሠልፎች፣ ስብሰባዎች እና በየግለሰብ ቤቶች ያሉትን በኢትዮጵያ ሥም ወይም የኢትዮጵያን ቀጣና የሚያመላክቱ የባንዲራ ብዛቶች በትኩረት ተመልከታችኋል?

ለመሆኑ እነዚህን የባንዲራ ቀለማቶች ማን ፈጠራቸው? የሕዝብስ የይሁንታ ተቀባይነት አግኝተው ይሆን? ወይስ ነፃ አውጪዎች ወይም የኃሣ መሪዎች በሚፈልጉት መልክ የቀረጿቸው ናቸው። በተለይ ከ«ድምፃችን ይሰማ» ከሚለው የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች የተቃውሞ ሠልፍ በኋላ የታዘባችሁት የባንዲራ ጉዳይ አለ?

በአውሮፓ፣ በአሜሪካ እና በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን በሚበዙበት የአፍሪካ ሃገሮች የሚደረጉ የተቃውሞ ሠልፎችን ልብ ብላችሁ ተመልከታችኋል? እኔ እንደታዘብኩት ከሆነ ሠልፈኞቹ ከየት አገር እንደሆኑ ግራ ሳይገባኝ አልቀረም። አንድ በአውሮፓ በተደረገ ሰላማዊ ሠልፍ ያየሁት ግን ከሁሉም በእጅጉ የተለየ ሆኖብኝ።

ቁጥሩ በግምት ከ400 የማያንስ ታዳሚ ባለበት በዚህ ሠልፍ ላይ «እኛ ኢትዮጵያውያን ነን፣ ድምፃችን እንዲሰማ እንፈልጋለን፣ አለአግባብ ታፍነናል» የሚል መሪ ቃል እንዳላቸው በጩኸት የሚያሰሙ ሠልፈኞች የጆርመኑን ፓርላማ በራፍ በጩኸት የጥለቀልቁታል።

ወደ ቢሮዋቸው የሚገቡ የፓርላማ አባላት እና ሠራተኞችም የሠላማዊ ሠልፈኞቹን ብዛትና የመረረ ጩኸት በመስማት በተወካቸው አማካይነት የቀረበላቸውን የጽሑፍ ደብዳቤ ተቀብለዋቸው ወደ ውስጥ ይዘልቃሉ። ጩኸቱ ግን አሁንም አላቆመም። «አሏህ ኩበር! አሏህ ኩበር!» ይላል ጩኸቱ።

ይኽንን የተመለከተ አንድ የሃገር ልጅ በአጋጣሚው ግራ ይጋባና ካሜራውን አስተካክሎ ወደ ሠልፈኞቹ ጠጋ በማለት ካሜራውን ይደግናል። በሠልፉ ውስጥ በዓይን የሚያውቃቸው ኢትዮጵያውያኖች አሉበት የያዙት ባንዲራ ግን የኢትዮጵያ አይደለም። በአስቸኳይ ወደ ቅርብ ጓደኛው ይውልና እንዲመጣ ይነግረዋል። እንግዲህ እነዚህ ሁለት ወጣቶች የቀረፁትን ቪዲዮ ነበር የላኩልኝ።

ቪዲዮውን በጥሞና መረመርኩት፡ ደጋግሜም አየሁት። ይኽን ቀረፃ ያካሄዱትም ወጣቶች የዋዛ አልነበሩምና ቅጂውን በድምፅ አጅበውታል፣ የቃለመጠይቅም አድርገዋል።

እንግዲህ የእኔ ትዝብት የጀመረው እዚህ ላይ ነው። የአንድ ሃገር ሕዝብ የራሱ የሆኑ ከሌሎች አገሮች ከሚለይባቸው አንዱ የሃገሩ የመታወቂያ ዓርማ ሳይሆን አይቀርም። ነውም።

እነዚህ ሠልፈኞች ኢትዮጵያዊ ከሆኑ የኢትዮጵያ መታወቂያ የሆነው የባንዲራ ዓርማ የት አለ? የሚል ጥያቄ አእምሯችሁ ማጫሩ አይቀርም። በዚህ ሠልፍ ላይ አንድም የኢትዮጵያ ባንዲራ የለም። ሁሉም ግን ባንዲራ ያዘዋል። እንዲያውም ከሠልፈኞቹ ይልቅ የባንዲራው ቁጥር ይበልጣል ብል ማጋነን አይሆንም።

ላስረዳ፡- ከሠልፈኞቹ አብዛኞቹ ሴቶች ናቸው። እነዚህ ሴቶች እንደ ሻርፕ በአንገታቸው ላይ፣ መሉ ጸጉራቸውን የሸፈኑበት (ሒጃብ) በእጃቸው የያዙት ደግሞ ተጨማሪ ሦስት ባንዲራ ይዘዋል። ወንዶቹም በልብሳቸው ቀለም እና በእጃቸው የያዙት ባንዲራ በሙሉ ከቁጥራቸው የበዛ ነው። ሁሉም የያዙት የባንዲራ ቀለም፡ ከላይ ቀይ ከታች ቀይ ሆኖ መሐሉ ላይ ባለው አረንጓዴ ቀለም ላይ ትልቅ ወርካ ያለበት ነው። አንድ ሁለት የሚሆኑት ደግሞ ከላይ ቀይ ከታች ጥቁር ሆኖ መሐሉ ላይ የቢጫ ጨረር ያለበት ትልቅ ዋርካ ያለበት ነው።

በኋላ በጥያቄ ሳጣራ የ«ኦሮሚያ እስላሚያ» ባንዲራ መሆኑ ተነገረኝ። ሠልፈኞቹ ትክክል ነበሩ። በወቅቱ ያሰሙት የነበረው መፈክር እና አቋም ኢትዮጵያን ስለማይወክል የያዙት ባንዲራ ትክክለኛ መግለጫቸው በመሆኑ በዚህ በኩል በወሰዱት እርምጃ ማንነታቸውን አልደበቁም። በዚህ ሠልፍ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በሙሉ የመካከለኛው ምሥራቅ እና የሱማሊያ ዜጎች ናቸው። «እስላሚክ ብራዘር ሁድ» ይሏችኋል ይኽቺ ናት። እንዲያውም አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ወጣት የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዞ ሠልፉን በመቀላቀሉ ተገፍቶ ከሠልፉ ውጭ መሆኑ ፊልሙን በቀረፁት ወገኖች ተነግሮኛል።

እኔ የሠልፈኞቹን እምነት እና ጥያቄ የመቃወሙ አቅምም ሆነ ፍላጎት የለኝም፣ የኔ ትዝብት የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዞ የመጡት ጥያቄ ማንሳት ሲቻል የቀደሞ የታላቋን ሶማሊያ የመስፋፋት ዓላማ እና የአክራሪ እስልምናን አጅንዳ ይዞ ለመጣ ክፍል ለምን መሣሪያ እንሆናልን የሚል ነው።

በእውነት እነዚህ ሠልፈኞች ሥነ-ልቡና ውስጥ ቀድሞ የሚፈልቀው ኢትዮጵያዊነት ነው ወይስ ኃይማኖት የሚል ጥያቄም ያጭራል። መቼም እኛ ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም ነገሮችን ሸፋፍኖ እና ተቻችሎ መኖር እንወዳለን። ይኽ ተቻችሎ መኖር እንደነዳን የምንረዳው ደግሞ ካለፈ በኋላ ነው። የአንድ ሃገር ሰው ተዋድዶ እና ተፋቅሮ እንጂ እንደ ክፉ ጎረቤት ለመኖር ሲል ተቻችሎ አይኖርም።

በጀርመን ውስጥ ብዙ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች እና እስላሞች ይኖራሉ። የመብት ጥሰት ጥያቄም ሲነሳ ሁሉንም አቀፍ እንጂ አንዱን ኃይማኖት ብቻ ያዘለ መሆን አይኖርበትም።

ባለንበት እና በምናየው አዲስ ክስተት የዚህ የባንዲራ እና የማንነታችን ጥያቄ ከዘር ወይም ከብሔረሰብ ጥያቄ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ቀን ቆጥሮ እውነቱ እያፈጠጠ ሲመጣ የኃይማኖት ጥያቄ እየሆነ የመጣ አይመስላችሁም? በስሙ የሚነገደውስ ክርስቲያኑ አሮሞ ይኽንን እንዴት ያየው ይሆን?

በአዲሱ ዓመትስ ሌላ ተጨማሪ ባንዲራ እንፈለስፍ ይሆን? ቀለሙን ለማየት ቸኩያለሁ።

ሰላዩ



የኢቲቪ ጋዜጠኛ የጻፈው የፍቅር ደብዳቤ

(ክፍል ሁለት)

Selayunafqot@gmail.com

"ውዴ!

የኔ እርኃ! እንዴት ከረምሽልኝ? እኔ ካንቺ ናፍቆት በስተቀር ደህና ነኝ። እንዴት እንደናፈቅሽኝ ታውቂያለሽ? አታውቂም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቁ መሪያችንን የናፈቀውን ያህል ነው የናፈቅሽኝ። ምን ያህል እንደምወድሽስ ታውቂያለሽ? አታውቂም። የህገራችን ገበሬ ያመረተውን ማኛ ጤፍ እንኳን እንዳንቺ አልወድም። አሸባሪዎች እንደማልወድሽ አድርገው ሲያወሩ አትስሚያቸው። ባልወደሽ ኖሮማ አሸባሪዎችን ለመቃወም በተደረገው የሰፊው ሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ይገፍሽ አልወጣም ነበር።

ያ ቀን ግን ትዝ ይልሻል? አይልሽም። በፍቅራችን ታሪክ እንደዛ አይነት ውብ ጊዜ አሳልፈን እንደማናውቅ እርግጠኛ ነኝ። መቼስ አሸባሪዎችን በሚያወግዝ ሰልፍ ላይ ከመሳተፍ የበለጠ ምርጥ የፍቅር ጊዜ አይኖርም። የዛን ጊዜ ምን እንደተሰማኝ ታውቂያለሽ? አታውቂም። በቃ... ምን ልበልሽ? ደስታ፤ ዴሞክራሲ፤ ልማት፤ ነፃነት፤ ቁርጠኝነት፤ ...ብቻ ያልተሰማኝ ነገር የለም። አባቶቻችን ለካ ለጦርነት የሚሰለፉት እንዲህ አይነት ስሜት እየተሰማቸው ነው። ሰልፍ ማለትኮ ዴሞክራሲ ነው። ለዚህ ነው መንግሥት ሰልፍ እንድትወጡ (ባትወጡ ግን...) ብሎ ሲጠራ ሕዝቡ ዴሞክሪያሲያዊ መብቱን ለማክበር ግልጥ ብሎ የሚወጣው።

ሰልፍ እኮ ማለት ክብር ነው። ሰልፍ እኮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላችን ነው። ሰልፍ እኮ ማለት ልማት ነው። ሰልፍ እኮ ማለት በቃ ... ሁሉ ነገር ማለት ነው። እኔ ብዙ አይነት ሰልፍ ተሰልፌያለሁ እንደበቀደሙ ግን የሆነልኝ የለም። አንቺ አብረሽኝ ስላለሽና እግረመንገዳችንን ፍቅራችንን ስላጣጣምን ነው መሰለኝ፤ እንጂ ለሰልፍማ አዲስ አይደለሁም። ብዙ ሰልፎች ላይ ተሰልፌያለሁ። በሀገራችን ሰልፍ በሽ አይደል? ዳቦ ቤት ሰልፍ አለ፤ ታክሲ ለመያዝ ሰልፍ አለ፤ አውቶቡስ ለመያዝ ሰልፍ አለ፤ እቃ ለመግዛት ሰልፍ አለ፤ ቤንዚን ለመሙላት ሰልፍ አለ፤ ከሀገር ለመሰደድ (ኢሚግሬሽን) ሰልፍ አለ፤ ለኮንዶሚኒየም ሰልፍ አለ፤ ባንክ ቤት ሰልፍ አለ፤ መብራትና ውሃ ለመክፈል ሰልፍ አለ፤ ሲኒማ ለማየት ሰልፍ አለ፤ ት/ቤት ሰልፍ አለ፤ ሥጋ ቤት ሰልፍ አለ፤ አሸባሪ ሲመጣ ሰልፍ አለ፤ ... ብቻ ምን አለፋሽ ... ባለራእዩ መሪያችን ምስጋና የድረሳቸውና ሰልፍ በሰልፍ ሆነናል። እኛም ታዲያ የሳቸውን ራእይ ለማሳካት እንሰለፋለን።

"ውዴ!

የኔ አዝመራ! አንቺ እኮ ማለት የህይወቴ ሀዳሴ ነሽ። እንደ ሀገራችን ኢኮኖሚ ቀን በቀን የሚንረው ፍቅሬ እስካይሽ አላስችል ብሎኛል። ለነገሩ ሰሞኑን ለታላቁ መሪያችን አንደኛ የሙት አመት በሚዘጋጀው ዝግጅት ላይ ስለምወስድሽ አገኝሻለሁ። ከዛ በኋላም የባንዲራ ቀን እንደሚመጣ አትርሽ። የብሔር ብሔረሰቦች ቀንም ብዙ ሩቅ አይደለም። ብቻ ደጋግመን እንደምነገናኝ ሳስብ ልቤን ልማት ልማት ይለኛል። ደሜ ራሱ አረንጓዴ የሆነ ይመስለኛል። አንዳንዴማ ናፍቆትሽ አላስችል ብሎ የምሆነውን ሲያሳጣኝ ምን እንደማደርግ ታውቂያለሽ? አታውቂም። የህገራችንን ሕገ መንግሥት አነባለሁ። ከወንበሬ ሳልነሳ ሕገ መንግሥታችንን በፍቅር ካነበብኩ በኋላ ናፍቆቴ ጋብ ያለ ሲመስለኝ አዲስ ዘመንን ገረፍ አድርጌ ኢቲቪን አያለሁ። የኔ ውድ! አንቺ እኮ ማለት ለኔ ሕገ መንግሥታችን ባንናፀፈን ዴሞክራሲያዊ ነፃነት በአብዮታዊ ልቤ ያፈቀርኩሽ ውድ ፍቅሬ ነሽ።

"ውዴ!

የኔ ማኛ ጤፍ! ከሰሞኑን አንዳንድ ኪራይ ሰብሳቢዎች ካጠመዱት ወጥመድ ተጠንቀቂ። የአብዮታዊ ፍቅር ትርጉም ያልገባቸው ናቸውና እንዳያታልሉሽ። ከአንዳንድ አሸባሪዎች ጋር በማሴር ዝም ብለው ይለፈልፋሉ አሉ። ልማትን እንጂ ልፍለፋን የማይወደው ፀሐዩ መንግሥታችን እንደ ውቅያኖስ በሰፋ ትእግስቱ የታገሳቸው ስላላገኛቸው ነው። በቅርቡ ሲያዙ ግን አትጠራጠሪ መጨረሻቸው ቃሊቲ ነው።

"የኔ ፍቅር! እኔ ግን አልናፈቅኩሽም? ናፍቄሻለሁ። ቀንም ሌሊትም ከኔ መለየት እንደማትፈልጊ አውቃለሁ። ሙሉ ድምጽሽን ሰጥተሽ በአብዮታዊ ልብሽ መርጠሽ እንዳፈቀርሽኝ ባትነግሪኝም አውቃለሁ። ደግሞም ባታፈቅሪኝ ነው የሚገርመኝ። ያ ወልጋዳ የቀድሞ ፍቅረኛሽ የማፍቀር መብትሽን ነፍጎ ሲያንገላታሽ አይደል እንዴ እኔ ደርሼ ዲሞክራሲያዊ ፍቅርን ያሳየሁሽ። ለዛ ነው ብታፈቅሪኝ የማይበዛብኝ። ደግሞ አይዞሽ የፍቅራችንን ሀዳሴ ገና እናያለን። ሊወሽመሽ አልያም ከኔ ሊነጥቁሽ ያሰቡ ሁሉ ቁርጣቸውን ይወቁ። ለዘላለም ከልብሽ ዙፋን እንድወርድ እንደማትፈልጊ ስለማውቅ ሁሌም የልብሽ ንጉስ እንደሆንኩ ቀጥላለሁ።

"ውዴ!

የኔ በጎ አሳቢ! በሚቀጥለው ደብዳቤ እስካገኝሽ ድረስ በዚሁ ልሰናበት። ማታ ዜና ካነበብኩ በኋላ አስተያየትሽን በጉጉት እጠብቃለሁ። ለታላቁ መሪያችን የሙት አመት ዝግጅት ላይ ቃለ መጠይቅ እንድትደረጊ ስለማደርግ የሐዘን ልብስ ለብሰሽ አይንሽን በደንብ አሽተሸው ነይ። በደንብ ካለቀስሽ እኔም እመሰገናለሁ። ስለዚህ አደራ! በተረፈ ከዜና በኋላ የሚታየው ጥናታዊ ፊልም እንዳያመልጥሽ። ሕዝቡ ሰሞኑን ወቅሳ ስላበዛ ሐሳቡን ለመበተንና በቅርቡ ሊሠራ የታሰበ ሥራ ስላለ ነው የሚታየው።

ያንቺው ልማታዊ ፍቅረኛ"


የዘመኑ አንፋሎት

ኢህአዴግን መቃወም ሌላ! ... ሽብርተኝነት ሌላ

የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ይሆን?

በቅርብ ዓመት ውስጥ የተፈፀመ ነው:: ፒያሳ በሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲን ምዕመናን ፀሎታቸውን እያሠሙ ምህላቸውን እያደረሱ ከአምላካቸው ጋር በአርምሞ እየተነጋገሩ ባሉበት ደቂቃ አንድ ለየት ያለ ድምፅ ተሠማ ‹‹አሏህ አክበር!›› የሚል:: ሕዝበ ክርስቲያኑ በድንጋጤ ድምፁን ወደሰማበት አቅጣጫ ዞረ ያ ድምፅ በድጋሚ በነላ ሁኔታ ደግሞ ደጋግሞ ‹‹አሏህ አክበር!!... አሏህ አክበር!!›› ይላል:: የሚያዩትን ለማመን የከበዳቸው ምዕመናን ግራ ተጋቡ መ·ሉ የመ·ስሊም ልብስና ቆብ ያደረገ ግለሰብ አውደምህረቱ ላይ ሆኖ እየሰገደ ነው:: ሰውየውን ከቅጥር ግቢው ለማስወጣት ከድንጋጤ እና ካለማመን የተነሳ ረዥም የሚባል ግዜ ወስዶ ነበር:: ይሄ የሆነው አፍጋኒስታን... ኢራቅ ... ፍልስጤም ሳይሆን መ·ስሊም ክርስቲያኑ በፍቅር እና በመተሳሰብ በሚኖሩባት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ::

ሌላ ልጨምር... ክርስቲያን ወንድምና እህቶች በጉበረት ፈጣሪያቸውን እያመለኩና በመዝመር እና በወንጌል ትምህርት ላይ ተመስጠው በነበሩበት ቅፅበት ሆን ተብሎ የሚያመልኩበት ቤተክርስቲያን በእሳት እንዲያያዝ ተደረገ፣ በድንጋጤና በነፍስ አውጪኝ ግድግዳውን እና በሩን ገንጥለው የወጡ ወንድምና እህቶች ከውጭ የጠበቃቸው ‹‹አይዞዋችሁ ወድሞቼ... ደርሰንላችኋል እህቶቻችን›› ብሎ እሳቱን ለማጥፋት ውሃና እርጥበ ቅጠል የያዘ ኃይል ሳይሆን ገጀራ ፣ጦር፣ ሜንጫ የያዘ ፀረ ክርስቲያን የሆነ ቡድን ነበር:: በሚያሳዝን ሁኔታ ከእሳት ያመለጡ እህቶችና ወንድሞች በገጀራ ተከታትፈው በጦር ተበሳስተው በሜንጫ ተቆራርጠው ፈጣሪን በሚያመልኩበት ደጃፍ ነፍሳቸው አለፈች:: ይሄ የሆነው አፍጋኒስታን... ኢራቅ... ፍልስጤም ሳይሆን መ·ስሊም ክርስቲያኑ በፍቅርና በመተሳሰብ በሚኖርባት፣ ራጉኤልና አንዋር ኩታ በገጠመባት ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገ አሳዛኝ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው::



ሠላማዊው እስልምና ጽንፈኛው ወሀቢያ

እንቀጥል... በሀገራችን ሌላኛው ክፍል የተደረገ ነው ይሄ ደግሞ::

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን አካባቢያችንን ልቀቁልን የሚል ዛቻ መሰንዘር ከጀመረ የሰነባበተ ቢሆንም ‹‹ከዚህ ለቀን የት ነው የምንሄደው? ሀገሩን የእናንተ ብቻ ያደረገው ማነው?›› የሚል ምላሽ ከኦርቶዶክሶቹ የደረሳቸው ሀገራችንን ልቀቁ ባዮች ‹‹አሏህ አክበር!›› ብለው አንዲት ቤተክርስቲያን መ·ሉ በመ·ሉ ሲያቃጥሉ በርካታ ሰዎች መኖሪያቸውን ወደ አመድነት መለወጥ ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውንም አስከፈለ:: ይሄም የሆነው አፍጋኒስታን... ኢራቅ... ፓኪሲታን ... ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ነው!

ከቅርብ አመታት ወዲህ በአስልምና ስም እየተፈጸሙ ያሉ አሰቃቂ ድርጊቶች እየሰማን እየታዘብን ነው::

በፊት በፊት በፓኪስታን..... አፍጋኒስታን... ኢራቅ... እና መሰል ሀገራት ስንሰማና በቴሌቭዥን ስናይ የነበረው በኃይማኖት ሽፋን የሽብርተኝነትና የአከራሪነት አካሄዶች አሁን አሁን መሐላችን ሀገር ውስጥ በአስደንጋጭ ሁኔታ እየተስፋፋ ነው:: ሀገሪቷን በኃይማኖት ሰበብ ወደማይፈለግና የሰውን ሕይወት ወደሚቀጥፍ መንገድ በግርግር የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በሚያስቡና በሙስሊሙ ስም የሚነግዱ በድኖች እንደ አሸን እየፈለሉ ነው::

ኢህአዴግ ሌላ! ሽብርተኝነት ሌላ! መሆኑ ያልገባቸው በወጪው በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩ ግለሰቦች ለነዚህ ቡድኖች በድብቅ እርዳታ ከመስጠት አልፈው ዋነኛ ስትራቴጂ አውጪዎች እስከመሆን መድረሳቸው የጉዳዩን ከብደት አስረጂ ነው:: መንግስትን መደገፍ አልያም መቃወም የማንኛውም ሰው መብት ቢሆንም ሀገርን የሚበጠብጥ... የደህ ልጅ በጥይት እንዲሞት በአውሮፓና በአሜሪካ ቁጭ ብለው አይዞህ እና በርታ የሚሉ ሰዎች ግን ወንጀለኛ ብቻ ሳይሆኑ ሽብርተኛ ደጋፊዎችም ናቸው::

- ኃይማኖታዊ ፕሮግራሞች ካልሆኑ በቀር ሌሎች የቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን ማየት (መከታተል) ክልክል ነው።
- የአበባ ስጦታ ማበርከት ክልክል ነው።
- የሰውም ሆነ የእንሰሳትን ስዕል መሳል ክልክል ነው።
- ልብወለድ መጻፍም ሆነ ማንበብ ክልክል ነው። ውሸት ነውና።
- በግራ እጅ መጻፍም ሆነ መመገብ ክልክል ነው።
- ሪዝን መላጨት ክልክል ነው።
- ውሻ አብሮ ቤት ውስጥ ማኖር ክልክል ነው።
- በቲያትር (ድራማ) ውስጥ ተዋናይ መሆን ክልክል ነው። ውሸት ነውና።
- የልደት ቀንን (የነብዩንም ቢሆን) ማክበር ክልክል ነው ወዘተ ይገኙበታል።

ዝርዝሮቹ ብዙ ናቸው ። ይህ እንግዲህ ወሀቢያ የተሰኘው አስተምህሮ ወደድንም ጠላንም ልጫንባችሁ የሚለን መመሪያዎቹ ናቸው። የሙስሊም ሀገራትን የነበኘ ሰው እንደሚያውቀው ከሳውዲአረቢያ በስተቀር እነዚህ ክልከላዎችን (አደቦች) የሚከተል የለም። ከጽንፈኞች በስተቀርም በነዚህ የሚተዳደር ሙስሊም የለም።

ዛሬ ኢትዮጵያን የሚያስተዳድረው መንግስት ‹ወንጀለኛ› ያለውን ‹ጀግና› የማድረግ አባዜ፣ መንግስት ‹ተጠንቀቁ› ያለውን ጉዳይ እንደውሸት ማስፈራሪያ የመቁጠር አጉል ልማድ በተንሰራፋ ቁጥር እንደ ወሀቢያ ያሉ የጥፋት ቡድኖች እንዲደላደሉ እና በቀላሉ ሊነቀል የማይችል የጥፋት ስራቸውን አጥልቀው እንዲቀብሩ እድል መስጠት ነው።

በቀርቡ በኢቲቪ ለውይይት ቀርበው የነበሩትና አገር የማስተዳደር ብቃቱ አለን ሲሉ የሚደመጡት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ያንጸባረቁት ሀሳብ ይህን የሚገልጽ ነው። ‹‹በሀገራችን ሽብርተኝነት የለም›› ‹‹ሙስሊሙ ሙበቱ ተረግጧል›› ‹‹የታሰሩት ጀግኖች እንጂ አሸባሪዎች አይደሉም›› የሚሉ ነጥቦችን ደጋግሞ ሲያነሱ የነበሩት እነዚሁ አመራሮች በእርግጥም በወሀቢያ እየተካሄደ ያለውን እኩይ ተግባር ሳያውቁት ቀርተው ሳይሆን ‹የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው› በሚል ያረጀ ያፈጀ አባባል የሚመሩ በመሆናቸው ነው። በስልጣን ላይ ያሉት እነሱ ቢሆኑና ‹‹ወሀቢያ ካልሆንክ›› ‹‹ጺምህን ካላንገረገግህ›› ‹‹ሂጃብ ካላደረግሽ...›› እየተባሉ በአደባባይ አንገታቸውን የሚቀሉ ከእድርና ከማኅበር የሚባረሩ ዜጎችን ጉዳይ እንዴት ይፈቱት ይሆን? ያስብላል።

በፖለቲከኞቻችንም ሆነ በወሀቢያ ግልገሎች እንደማደናገሪያ የምትቀርበው ‹የሀይማኖት ነጻነት መብት› የምትለዋ ነች። በእርግጥ ማንኛውም ዜጋ እምነቱን በነጻነት እንዲያካሂድ ይፈልጋል ይሁን እንጂ ‹‹የኔ እምነት ተከታይ አይደለህምና መሞት አለብህ›› ብሎ ሌሎች ላይ ፍርድ የመስጠት ስልጣን ፈጽሞ አይሰጥም! ወደፊትም አይሰጥም! ለዚህም ነው ኢህአዴግን መደገፍ ሌላ ሽብርተኝነትን መደገፍ ሌላ የምለው ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ እንደማለት።

ኢሕአዴግ ቀድሞ የዘራውን እራሱ እያጨደ ቢሆንም እሱን ለማቃወም ሲባል ብቻ ለአክራሪዎች ቀዳዳ መክፈት አገርን አሳልፎ ከመስጠትና ነገ የሚመጣ ቁጭት ውስጥ መግባት ይሆናል።

በቀጣይ ፅሑፌ በርካታ ማስረጃዎችንና ወሀቢያ ስለተባለው አስተምህሮ አነሳስና በአለም ላይ ስለፈጸማቸው አሰቃቂ ድርጊቶች ጭምር የምለው ይኖረኛል።


በ«አያት ሪል ስቴት» ገንዘባችሁን ለተቀማችሁ ሁሉ

ባለፉት 10 ወራት የጀመርነውን በአክሰስ ሪል ስቴት በቤት አሰራላችኋለሁ ሽፋን የተፈጸመውን ከፍተኛ ገንዘብ ዘረፋ ማጋለጥ ከመጀመሪያችን ላይ የተመለከቱ አንባብያን በተመሳሳዩ በ«አያት ሪል ስቴት» ተመሳሳይ ወንጀል እንደተፈፀመባቸው በመጥቀስ ለዝግጅት ክፍላችን ቅሬታቸውን ልከዋል።

ዳሩ ግን በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን አቤቱታ ብቻ ከማስተናገድ ይልቅ በዚሁ የ«አያት ሪል ስቴት» በደል የተፈፀመባችሁ ቤተ-ሠራዎች ዝርዝራችሁን ለመያዝ እንዲረዳን እና በሕጋዊ መንገድ በቡድን ጥያቄ የሚቀርብበትን ለመፈለግ ለዝግጅት ክፍላችን ማስረጃችሁን መላክና በስልክ በዝርዝር ማነጋገር የምትችሉ መሆናችሁን እንገልጻለን።

የናፍቆት ኢትዮጵያ የዝግጅት ክፍል


ፀደይ አበባ ግሮሰሪ
TSEDEY ABEBA GROCERY



- ማንኛውም የአበሻ ቅመማ ቅመሞች
- ጥሬ ሥጋ ስቀርጥ እና ስክትፎ
- Ethiopian Spices & Blend

672 South Pickett Street
Alexandria, VA 22304
Tel: 703-461-9420

- Ethiopian Coffee
- Deli
- ቡና የተፈጨ፤ ያልተፈጨና ጥሬ
- እንጀራ /ክትስያየ አክፋፋዮች



በሚቀጥለው እትም የሚቀርቡ

- ኢትዮጵያ ! ‘‘በጥቁር ደመና ሥር’’ በሚል ርዕስ እናቀርበዋለን ያልነው የአቶ ተክሉ ለሚ ጽሑፍ በዚህም ወር በስምምነት ላይ ባለመድረስ ሊዘገይብን ችሏል። እሳቸው ጽሑፉን እንደወረደ አውጡልኝ ሲሉ፣ እኛ ደግሞ አንዳንድ መራራ የሆኑ ቃሎችን እናስወግዳለን በሚለው ላይ መስማማት አልቻልንም። አሁንም ድርድሩ እንደቀጠለ ስለሆነ በሚቀጥለው እትም ላይ ለማቅረብ እንሞክራለን።
- በአሻራ አምዳችን ትግራይን ክፍል እንዳስሳለን።
- በሠላዩ አምዳችን አስተምሮ ፈገግ የሚያሰኝ ሥራ እናጣምራ።
- የሸገር ወጎች የአዲስባን ጉዳንጉድ ይዘልናል።
- «ገራፊው ብርዬ» በሚል የተዘጋጀ የጠመኔው ሥራ ይኖረናል።

ርህራሄ አልባው አርታኢ

«ጉንዳኗ» የተሰኘውን የዲ/ን ዳንኤል ክብረትን መጣጥፍ በናፍቆት ኢትዮጵያ መጽሔት ላይ አነበብኩ። እንደማንኛውም ጽሑፋቸው በሳል እሳቤ እና ትምሕርታዊ ይዘት አለው። ሆኖም በዚህ መጣጥፍ የፊደል ግድፈት በብዛት ይስተዋላል። መጣጥፉ ከ«ርህራሄ አልባው» አርታኢ ብዕር እንዳመለጠ። ግልፅ ነው።

የፊደል ግድፈት በመጀመሪያ በቅርፅ ከዚያም በይዘት ላይ ጫናውን ያሳርፋል። ግድፈቱ መረን ከለቀቀ በስንት ድካም እና ጥበብ የተፈጠረን ረቂቅ ውበት መና ሊያስቀር ይችላል።

አንድ መጣጥፍ ከራስ አርትኦት ቢያፈተልክ የማስተካከል ኃላፊነት የሚያርፈው ምንግዜም ዝግጅት ክፍሉ ትከሻ ላይ ነው። ዝግጅት ክፍሉ ይኸንን እንዲፈፅም የሚገደደው በሙያዊ ሥነ-ምግባር ብቻ ሳይሆን በእሱ እና በጸሐፊው መካከል «ያልተፃፈ ውል» በመኖሩ ጭምር ነው።

ስለሆነም ለመጽሔቷ ስም፣ ለፀሐፊው ክብር እንዲሁም ለአንባቢዎች ሲባል የዚህ ዓይነት ስህተት ለወደፊት እንዳይደገም ጥንቃቄ ቢደረግ መልካም ነው እላለሁ።

ደምሌ አያሌው / ከቺካጎ/

«በደብዳቤዎቻችሁ» ገጽ ላይ ለሚቀርቡልን ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሞከርንበት ጊዜ አይታወሰኝም። ገጹ ነፃ የሃሳብ መግለጫ ስለሆነ ከአንባቢዎች የመጣውን ጥያቄ ለአንባቢዎች አስተያየት እንተወዋለን፣ የደብዳቤዎቻችሁ ገፅም ዋናው ዓላማ ያኼው ነው። ነገር ግን በዚህ ጥያቄ ላይ አንድ ነገር ማለት ፈለግሁ። መልስ ከመስጠቱ በፊት ግን ይኸንን እርስዎ የፊደል ግድፈት እና ስህተት በብዛት ይታይበታል ያሉትን እትም እንደገና ደጋግሜ አነበብኩት።

በእርግጥ እርስዎ እንዳሉት ሳይሆን በጣም ጥቃቅን የሆኑ የታይፕ ስህተቶች አሉበት። ይኸንንም ስል ለምሳሌ ያልተሟሉ ቃሎች አይቻለሁ። ግን በስሜት ሊነበቡ የሚችሉ እንጂ እርስዎ እንዳሉት የሚጋነኑ ሆነው አላገኘኋቸውም።

ለምሳሌ «ላይ» ለሚለው ቃል «ላ» ብቻ ታይፕ ተደርጓል። እንደምሳሌ ይኸን አቀረብኩ እንጂ «ጥረት» ለሚለው «ትረት» ተብሎ የተፃፈበትም ሳረፍተነገር አይጠፋም። ግን የአረፍተነገሩ ሃሳብ ቃሉን እንዲለውጠው ወይም የፀሐፊውን ሃሳብ እንዲያበላሸ ሆኖ የተፃፈበት ቦታ በችራሽ አላየሁም። ለምሳሌ ያኽል ከዚህ አረፍተነገር በፊት «በጭራሽ አላየሁም» ከማለት ይልቅ «በችራሽ አላየሁም» የሚል ቃል ይታያል። ግን ምን ለማለት እንደተፈለገ አንባቢን ያደናግራል ወይም የፀሐፊውን መሰረተ ሃሳብ ያበላሻል ቢሉኝ ለያመኝ ይከጅለኛል።

እንግዲህ ያየሁት የታይፕ ስህተቱ ከዚህ ያለፈ እንዳልሆነ ከተረዱልኝ በመልክትዎ ላይ የተጠቀመባቸው «አስደንጋጭ ቃሎች» አለአግባብ የገቡ እና በ«አርታኢ እና በታይፕ ግድፈት መካከል ያለውን ግንኙነት እና ልዩነት» ለመረዳትዎ አጠራጠራለሁ። በእርግጥ መፃሔታችን ከምንም ዓይነት የቃላትም ሆነ የአባባል ስህተት ነፃ ቢሆን እንመርጣለን። ግን አንዳንድ ጊዜ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከእጅ የሚያፈተልኩ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፣ እንደምሳሌም የታይፕ ቃላት ግድፈት አንደኛው ነው። የታይፕ ግድፈት የተሳታፊዎችን የጽሑፍ ገጽታ አይለውጥም አላልኩም። በእርግጥም ከመለወጥም አልፎ ጭራሽ ሊያበላሸውና የትርጉም ለውጥም ሊያስከትል ይችላል። እኔ መከላከል የያዝኩት አሁን እርስዎ ባቀረቡት የአንድ አምደኛ ፅሑፍ ላይ ብቻ መሆኑ ይታወቅልኝ።

በመልእክትዎ የመጨረሻ መስመሮች ላይ የመከሩን ተገቢ በመሆኑ ስህተቶቹ እንዳይደገሙ በብርቱ እንጥራለን። አባባልዎም ትክክል እና ገንቢም ስለሆነ ሙሉ በሙሉ የምንቀበለው ነው።

እርስዎን በቅርብ እስከማውቅዎት ለጽሑፍ ባዕድ ያልሆኑ እና መጣጥፎችን ማንበብ ሳይሆን መጽሐፍ ደርሰው ለአንባቢያን ለማብቃት ሙሉ ብቃት እንዳለዎት አውቃለሁ። ታዲያ ያንን የሚያክል ሙያዊ በእውቀት እና ተሰጥኦ በቦርሳዎ ተሸክመው በእኔ ትንሽ ስህተት ላይ እንዲህ ሲረማመዱብኝ ለምን አይከፋኝ?

ምሥጋናዬ ያንሳችኋል

«ከወዳጅነት ወደ ደመኝነት» በሚል ርዕስ በእኔ እና በጓደኞቼ ላይ ከሃገር እስከ መሰደድ ያደረሰንን የ«አክሰስ ሪል ስቴት» በደል አስመልክቶ ያቀርብነውን አቤቱታ ማስረጃ ሰብስባቸሁ ለአንባብያን ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረባችሁት እና ስር የሰደደው ዘረፋ እንዲጋለጥ እና እንዲቆም በማድረጋችሁ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን ላቀርብላችሁ እወዳለሁ። ናፍቆቶች የሰራችሁት ሥራ ቀላል እንዳይመስላችሁ። ብዙ ሰዎችን ከመጪው ዘረፋ አድናችኋልና ምሥጋና ማቅረብ ብቻ ያንሳችኋል። ተባረኩ!

ሙላት መንግሥቴ / ከቦስተን /



ደብዳቤዎቻችሁ

ለዲ/ን ዳንኤል ክብረት

ነሐሴ 23 ቀን 2005 ዓ/ም

ሰላም፤ ለተከበርክ ለመምሕር ዳንኤል ክብረት፤ ከጥቂት ቀኖች በፊት፤ ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ ከመነቃቀፍ ባሕርይ፤ በበጎ ነናችን የመመሠጋገንም ባሕል እንድናዳብር ተወያይተን ነበር። አሁን የምጽፍልህ፤ ባንተ በኩል ሰፊ ተሰሚነት ያለህ በመሆንህና ካስፈለገህም ሌሎች ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች የማሰባሰብ ችሎታ ያለህ ስለሚመስለኝ፤ በተጨማሪም፤ ስለ ጉዳዩ ጥልቅ ስሜት ኖሮት ሐሳቡን ያካፈለ ሌላ ኢትዮጵያዊ ስላላጋጠመኝና በእድሜህም ከኔ ጋር ሳወዳድርህ (እኔ የ78 ዓመት ሽማግሌ ነኝ) ወጣት ስለ ሆንክ፤ የጠቆምከውን ዓላማ እንድትገፋበት በአክብሮት አሳስብሀለሁ።

ጉዳዩ ቀላልና በፍጥነት ሊከናወን እንድማይችል እገነዘባለሁ። ቢሆንም፤ ጥረቱ ዛሬ ከተጀመረ፤ ለዘለቄታው ተጨባጭ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል። እንደ ምሳሌ ልጠቅሰው የምችለው፤ እኔ ራሴ ሐሳቡን አመንጭቼ፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በዱባይ ማዘጋጃ ቤት የተገበረው፤ ብዙ ሐገሮችና በሺዎች የሚቆጠሩ ተወዳዳሪዎች የሚሳተፉበት የሽልማት ሥርዓት ነው። ዝርዝሩን ከዚህ በታች በተጠቀሰው መመልከት ይቻላል፤

http://dubai-award.dm.gov.ae/web/default.aspx

በተጨማሪ፤ ዱባይ ኤሚሬት፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች "Dubai Excellence Award" ለተሰኘ ሽልማት ታወዳድራለች። ሌላው ምሳሌ፤ አሜሪካ ውስጥ የሚገኙ ሆስፒታሎች እየተወዳደሩ ብልጫ ያገኙት እውቅና ያገኛሉ። ለዚሁ ሁሉ ግን ተገቢ የሆኑ መስፈርቶችና አስተማማኝ ሥርዓትና አወቃቀር ያስፈልጋል።

ምንም እንኳ ከሙያህ ወጣ ያለ ቢሆንም፤ ባለሞያዎችን ማሰባሰብና ማቀናጀት ስለምትችልና ለሐገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ተግባር ማከናወን የምትችል ስለሚመስለኝ እንድታስብበት፤ ጉዳዩን በአንድ ዘገባ እንዳትተወው አደራ እላለሁ።ያበርታህ!

ኪዳኔ ዓለማየሁ።

ከተቋቋመ የ68 ዓመታት ዕድሜ ያስቆጠረውን የተባበሩት መንግሥታት በፀሐፊነት ያገለገሉ ግለሰቦችን ያውቋቸዋል? ካለወቋቸው እኛ እናስታውስዎት። ለጠቅላላ እውቀትዎ ይጠቅምዎታል።



Gladwyn Jebb
Oct. 24, 1945 - Feb.. 1946
(እንግሊዝ)



Kurt Waldhelm
1972 - 1981
(አውስትሪያ)



Trygve Lie
1946 - 1952
(ኖርዌይ)



Javier Perez de cuellar
1982 - 1991
(ፔሩ)




Dag Hammarskjold
1953-1961
(ስዊድን)



Boutros Boutros Ghali
1992 - 1996
(ግብፅ)



U. Thant
1961 - 1971
(በርማ)



Kofi Annan
1997 - 2007
(ጋና)



Ban Ki-Moon
2007 - እስካሁን በማገልገል ላይ ያሉ
(ደቡብ ኮሪያ)

ታላቅ እና ቁመተ - አጭር

ዓለማችን ካፈራቻቸው አንቱ ለመባል ከበቁ የዓለም እውቅ ሰዎች መካከል ቁመተ አጫጭሮች በማለት ደረጃ ሰጥቶ (ቡክ አፍ ሊስትስ» የተባለው መፅሐፍ የእኛ የሆኑትን አፄ ኃይለሥላሴን በ16ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧቸዋል። አፄ ኃይለሥላሴ «ትላልቆች ግን አጫጭሮች» ከተባሉት እውቅ የዓለማችን ሰዎች 16ኛው ለመሆን የበቁት በ5 ሜማ ከ4 ኢንች ቁመት ነው።

አቤ

እኔ እና አለቃዬ

- **እኔ፡-** የተሰጠኝን ሥራ ለመሥራት ጊዜ ከወሰደብኝ ፣ ቀርፋፋ፣ ደካማ አባለለሁ።
- **አለቃዬ፡-** ያንኑ ሥራ ለመጨረስ ጊዜ ከወሰደበት፣ በጥንቃቄ እና በጥራት ሲሰራ ነው ይባላል።
- **እኔ፡-** ሥራውን ካልሰራሁት ሰነፍ እባላለሁ።
- **አለቃዬ፡-** ሥራውን ካልሰራው ሥራ በዝቶበት ነው ይባላል።
- **እኔ፡-** ሳልታዘዝ አስቀድሜ ሥራውን ባከናውን "አወቅሁ፣ አወቅሁ ባይ" እባላለሁ።
- **አለቃዬ፡-** ለሌላው ተምሳሌት ሊሆን ነው ይባላል።
- **እኔ፡-** ስህተት ብሰራ ደደብ እባላለሁ።
- **አለቃዬ፡-** ስህተት ቢሰራ፣ ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት አይጠፋም ይባልለታል።
- **እኔ፡-** ከቢሮ ወጣ ብል፣ ሊንሸራሸር ነው እባላለሁ።
- **አለቃዬ፡-** በፈለገው ጊዜ ከቢሮ ቢወጣ ለሥራ ጉዳይ ወጣ ብሏል ይባልለታል።

በጠቅላላው ምንም መልካም ሥራ ብሰራ የሚያመሰግነኝ እና የሚያስተውሰኝ የለም። ነገር ግን አንድ ጥፋት ብፈፅም አለቃዬ ለዘለዓለም አይረሳውም። «ኧረ! ምን ይሻለኛል?» አለ ጥልዬ።

ቤተ - ሙሴ / ቨርጂኒያ /

ተስፋ እና ፍቅር

ተስፋ፡- ምኞት አይደለም፣ በራስ መተማመን እንጂ።

ፍቅር፡- እውር አይደለም፣ ልናይ የሚገባንን የሚያሳይ መነጽር እንጂ።

ተስፋ፡- ጨለማን ከመውቀስ ይልቅ ፋኖስ ማብራት የሚያስመርጥ ስሜት እንጂ።

ፍቅር፡- የእውቀት ትክክለኛ የግንዛቤ ውጤት ነው።

ተስፋ፡- በማጣት ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ወደ ማግኘት ለመሸጋገር የሚያገለግም ድልድይ እንጂ።

ፍቅር፡- ርቀት አያግደውም፣ ርቀት ይቀንሳል እንጂ።

በመሆኑም ተስፋ የሌላት ሕይወት ክንፍ እንደሌላት ወፍ እንደምትቆጠር ሁሉ ፍቅር የሌላቸው ደግሞ ጨረቃ እና ከዋክብት እንደሌላው ሠማይ ይቆጠራሉ።

ተስፋ እና ፍቅር ይኑራችሁ።

ቃኝ

እንዲህ ብለው ነበር

«ለልጆች፡- ፍቅርን፣ ሳቅና ሠላምን ስጡ እንጂ ኤድስን አትስጡ፡»

ኔልሰን ማንዴላ

«በእኛ መንገድ መሞት እንጂ መሚደል የለም»

ኢንጂነር ታይሉ ሻውል

«ሴት ልጅ ተዘርታ የምትበቅል ብትሆን ኖሮ ወንዶች ሁሉ ገበሬ ይሆኑ ነበር።»

ናፍቆት

«የዘንድሮው ታዳሚ ወደ ጥሪው ሥፍራ የሚሄደው ድግሳችንን ሊያሟጥጥ ነው» እል ፍኝ

ከዘመኑ ሠርገኞች

«ያለሁበትን ዘመን ከረገምኩ እኔም ተከናኝ ነኝ»

አርቲስት ይልማ ገበረአብ

«ለፈጠራ ያልታደለ አእምሮ የትችት እና የሀሜት ፋብሪካ ነው»

ኮንፊውሽስ

«ሠይፍ የሚያነሱ ሁሉ፣ በሠይፍ ይጠፋሉ።»

ማቴዎስ 26: 52

ዘዴኛው አባት

አንድ እስራኤልን ጎብኝተው እና ኢየሩሳሌምን ተሳልመው ወደ አዲስ አበባ የተመለሱ አዛውንት፣ ከቦሌ ሊቀበላቸው ከመጣው ልጃቸው ጋር የናፍቆት ሠላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ስለአባቱ ጉዞ ጥያቄ ያቀርብላቸዋል።

ልጅ፡- አባዬ ለመሆኑ እስራኤል አገር ምን ይመስላል? ወደድከው?

አባት፡- ኢትዮጵያ እና እስራኤል እኮ አንድ ነው።

ልጅ፡- እንዴት?

አባት፡- እዚያ ናዝሬት አላቸው፣ እኛም ናዝሬት አለን። እዚያ ጽዮን አላቸው፣ እዚህም አክሱም ጽዮን አለ። እዚያ ጎላን ሃይት አላቸው፣ እዚህም ጎላ ሚካኤል አለ። ያው እስራኤል እና ኢትዮጵያ አንድ ነው።

የአሳቸው ብልሃት እንኳን ልጃቸው ነገ እኔንም ላከኝ እና እስራኤልን ልንበኝ በሎ ወጪ እንዳያስወጣቸው ያፈጠሩት መላ ነበር። ተሳክቶላቸዋል።

God & Adam

One day, Adam sat outside the Garden of Eden shortly after eating the apple, and wondered about men and women. So looking up to the heavens he said, "Excuse me God, can I ask you a few questions?"
God replied, "Go on Adam but be quick. I have a world to create."
So Adam says, "When you created Eve, why did you make her body so curved and tender unlike mine?"
"I did that, Adam, so that you could love her."
"Oh, well then, why did you give her long, shiny, beautiful hair, and not me?"
"I did that Adam so that you could love her."
"Oh, well then, why did you make her so stupid? Certainly not so that I could love her?"
"Well, Adam no. I did that so that she could love you."

በስልክ ካነጋገርናቸው ሰዎች የጥቂቶቹ አስተያየት

(አንፃራዊ እይታ)

- ኢትዮጵያ በረዥሙ ታሪኳ ቁልፉን እና ባሕሏን ሳይቀይሩ ያስተዳደሩ ንጉሦቿ እና ንግሥቶቿ ናቸው። ዘውድ አገዛዝ ካልተገረሰሰ ብለን ሁላችንም ፊክሽን፣ የአፍላ ዕድሜያችንንም ለተሻለ ለመሰለን ለውጥ ገበርን። ግን ተሳስተን ነበር። የዘውድ ሥርአት በኢትዮጵያ መገርሰስ ማለት የቀድሞ ታሪኳን መቅበር ማለት ነው። በኢትዮጵያ ዘውድ አገዛዝ ተመልሶ ቦታውን ካልያዘ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም መበጣጠሷ እና ታሪኳም የጠፋ እንደሚሆን አልጠራቀጠርም።
- አህጉራችን አፍሪካ ወደ ጥንቱ ባህላዊው ንጉሥ አገዛዝ መመለስ እና በልምዷ መሠረት ራሷን ማስተዳደር አለባት። የእንግሊዞች ዘውዳዊ አገዛዝ ሲደነቅ የአፍሪካው ለምን ጓሳቀር እንደሚባል አይገባኝም። አፍሪካ እማዘአበሐር የቀባው ለሃገሩ ቀናዒ የሆነ ንጉሥ ያስፈልጋታል። የምዕራባዊያን ባህል የራሳቸው እንጂ የአፍሪካ አይደለም። እንደራሳችን እንጂ እንደጎረቤታችን ልንኖር አይገባንም።
- በቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ ሆኜ ለዘውዱ መገርሰስ ያበረከትኩት አስተዋፀኦ አሁን ወደኋላ ዞሬ ሳስበው ይቆጨኛል። በወቅቱ በእርግጥም የተሻለ ዘመን የተሻለ የኑሮ ደረጃ እና አስተዳደር ይፈጠራል የሚል ግምትም ነበረኝ። ግን በጣም ተሳስቼ ነበር። በእኩልነት ሽፋን አገር እንዲህ ትከፋፈላለች ብዬ ገምቼ አላውቅም።

ከታዋቂ ሰዎች

- «ፖለቲካ ከጦርነት የሚከፋው ከጦርነት ይለቅ በፖለቲካ ብዙ ጊዜ ሞት ስለሚበዛ ነው።»

  ዊኒስተን ቸርቺል

- «ይኽቺ ምድር ከወላጆቻችን ወረስናት ሳትሆን ከልጆቻችን የተበደርናት ናት።»

- «...እኛ የመጣብንን ወራሪ እናሳየዋለን፣ እግሩን ለጠጠር ደረቱን ለጥይት ሰጥቶ አገሩን የሚያድን ሰው አዚህ ያለ እመስልህም? የገዛ ደሙን ጉበሮ ለገዛ አገሩ መሞት ጌጥ እንጂ ሞት አይባልም።»

  አቴን ጣይቱ ብጡል /1882/

የእናት እና የልጅ ጭውውት

ልጅ ፡- እማዬ! ይኼ ባሌ እየደበደበ አስቸገረኝ። ትዳሩን ትቼ አንቺ ዘንድ መጥቼ ልቀመጥ አስቤአለሁ።

እናት፡- ይኽን አባባል ሁለተኛ እንዳልሰማ! እኔ ቤቴን አከራይና እናንተ ዘንድ እቀመጥና ይኼን ባል የምትይውን ለሁለት ቁም ስቅሉን አሳይተን፣ አንቺ ሳትሆኚ እርሱ ራሱ ሻንጣውን ይዞ ውልቅ እንዲል እናደርገዋለን።

ቤተ - መሲ / ከቨርጂኒያ

CLASSIC NURSES

We offer:

* Nurse Aide Course
* Medication Aide Course
* Personal Care Aide &
* AHA Healthcare Providers CPR Certification courses.



የተሻለ ሥራ የሚያገኙበት አጭር ስልጠና ይውሰዱ

Address:
85 S. Bragg St. #103 Alexandria VA 22312
703 658 9575

ተጨማሪ መጣጥፎች

ደብዳቤዎቻችሁ 7
አቦል ቡና 11
ሰላዩ 5
2005 እንዴት አለፈ? 38
Mark's Corner..... 19
እልፍኝ 22
ፖፕ ፓየስ 11ኛ አጼ ኃይለ ሥላሴን ለማስከዳት ስላደረጉት ሙከራ 28
የሸገር ወጎች 16
መጽሐፈ ቤን 32
አራሙቻ /ግጥም/ 35
ቅንጭብ ዜና 35

ዲቃሎቹ ፊደላት

ዲቃሎች የሚባሉትን ፊደላት የሚወልዱት እናቶች :- ላ ማ ራ ሳ ቃ ባ ታ ቻ ና ዳ ጫ ጳ ፋ ሲሆኑ ከነዚህ የሚወለዱት ደግሞ

ኗ ሟ ሯ ሷ ሿ ቋ ቧ ቷ ቿ ኋ ኟ ዟ ዷ ጧ ቈ ኈ ናቸው። አባታቸው ደሞ 'ዋ' አዋላጃቸው ደሞ "ኡ" ናት። ማ ኡ ዋ = ሟ

ዐልቦ አልባው ቁጥራችን

ዜሮ በአማርኛ ዐልቦ ይባላል። ጥንታዊ የምንለው አማርኛ ፊደላችን ያኔ ጥንት ከተፈጠረበት ብዙም አልተለወጠም።ሒሳብ ከኛ ፊደል በሁዋላ ተፈጥሮ፣ዕንፈ ዓለማዊ ቋንቋ ሆኖ በጠፈር ምርምር ለመግባቢያነት የዋለው የዜሮ ወይንም የዐልቦ መኖር ነው። ዐልቦ (ዜሮ) ባይኖር ኖሮ አራቱ የሒሳብ ስሌቶች ዋጋ ቢስ ነበሩ።

እስካሁንም ቁጥሮቻችንን ሕያው አድርጎ ያቆያቸው መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ምዕራፍ ማውጫ ሆነው ያገለግሉ ስለነበር ነው።አሁን ግን አዳዲሶቹ ትርጉሞች ቁጥሮቻችንን በዘመናዊ ቁጥሮች መተካት ጀምረው ዐልቦ አልባው ቁጥራችን ወደ መቃብሩ እየተንደረደረ ነው። ከምሑራኖቻችን ውስጥ ቁጥራችን ላይ ዐልቦን ጨምሮ ቁጥራችንን ማዳን ስንችል ዐልቦ አልባ በመሆኑ ምክንያት ዋጋ ቢስ እየሆነ መጣ።

"ዠ"እየሞተ ያለው ፊደል

በአማርኛ የፊደል ገበታ ውስጥ ሀያ ሁለተኛ ስፍራ ያለው "ዠ"፣ "ጀ" በሚባለው ከአረብኛ በተወረሰው ፊደል እየተተካ መኾገር፣ ጋራዥ፣ ዠለጠ፣ ምንዥላት፣ ዥዋዥዌ፣..ከሚሉት ቃላት በቀር እነ ዦሮ፣ =ጆሮ፤ ዥብ=ጅብ፤ ዠበና=ጀበና፣ ዥራት=ጅራት፤ ዠምበር=ጀምበር፤...እየተባሉ "ዠ" ሞቱን እየጠበቀነው። በሀገራችን ከዚህ ቀደም ብዙ ፊደሎች ቢሞቱም፣ በኛ ትውልድ ለመሞት "ዠ" የመጀመሪያ ነው። ማዳን ይቻል ይሆን? አዎን። "ዠ"ን የሚጠቀሙ ሰዎችን ማብዛት ነው። ጆሮ ከማለት ይልቅ ዦሮ፣ ጅብ ከማለት ይልቅ ዥብ፣... አሊያ "ዠ" በኛ ትውልድ ከፊደል ገበታ ይሰረዛል። እኛም በታሪክ "ዠ" ፊደል የሞተበት ዘመን ሆነን እንመዘገባለን።

አቦል ቡና

ምነው አልቀናህ አለኝ ?

በጣም ትልቅ መቀመጫ ያላት ሴት ላይ በጣም ደስ ይለኛል። ትልቅ ዳሌ ያላቸው ሴቶች እንደምወዳቸው ያቹል ለፍቅር በምጠይቃቸው ጊዜ ፍቃደኛ አይደሉም። እኔ የእነሱን ዳሌ እያየሁ ስከተል፣ እነሱ ሲሸሹኝ ምን እንደማደርግ ቸግሮኛል። ጥበዳ ዳሌ ያላቸው ሴቶች መርፊ የመሰለ ቀጭን ሰው ይወዳሉ ሲባል እሰማለሁ። ምነው በእኔ ላይ ታዲያ ጨከኑ፣ ምንስ ባደርግ ይሻለኛል?

ገዴ - ከሜሪላንድ

አንዳንድ ወንዶች የሴቶችን ከወገብ በላይ ያለውን ደረታቸውን በማየት ያማልላሉ፣ ሌሎች ደግሞ መልክ እና ፀጉር ይማርካቸዋል፣ ጥቂቶች ደግሞ ፉንጋ ሴት ብትሆንም ደመ-ግቡ የሆነች ሴት ደስ ትላቸዋልች። ቁመና እንደ ተመልካቹ ነውና የሴቶች አቋም በወንዶች ዘንድ እንደፍላጎታቸው ይለያያል። ያንተ ግን ግድ የለህም ዕጣ ክፍልህ ከልመጠቹ ጋር ሳይሆን አይቀርም። ምን ባደርግ ይሻለኛል ላልከው ደልዳላ የሆነ ወፍራም ትራስ ተንተርሶ መተኛቱ በመጠኑም ቢሆን ይረዳህ ይመስለኛል። አለበለዘያም ትልቅ መቀመጫ ግዛ። ከዚህ በተረፈ ግን ምናልባት የአቀራረብ ችግር ይኖርብህ ይሆናልና አቀራረብህን ቀይር ወይም አሻሽል። ለሚቀጥለው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ሊረዳህ የሚችል ከሆነ ተጠቀምበት።

እንዴት ላግኛት?

ሙቼም ዕድሜ መቁጠሩ የማይቀር ነውና እንደ ትናንት የወጣትነት ዘመኔ በሴቶች ዘንድ ፈላጊ ወይም ተፈላጊ ለመሆን ራሴን ማስተዋወቁ አልቀረም፣ ግን በለስ አልቀናህ አለኝ። ባሁኑ ወቅት ተረጋግቶ ቤተሰብ መሥርቶ መኖር እመኛለሁ። ጓደኞቼ በአብዛኛው የቤተሰብ ኃላፊ ናቸው። ቀደም ባለው ጊዜ ምንም የማይመስለኝ አሁን በእነሱ መቅናት ጀምሬአለሁ። ታዲያ ለመቀራረብ ጥያቄ ያቀረብኩላቸው ሴቶች ከሁለት ጊዜ በላይ ከእኔ ጋር አይወጡም። ምክንያት እየሰጡኝ ግንኙነቱን ያቋርጣሉ። ይኽ ነገር ተደጋግሙብኝ፣ እኔ ደግሞ ከአንዷ መርጋት እና ቢቻል ቤተሰብ መመሥረት እፈልጋለሁ። ያልተሳካልኝ ምክንያቱ ምን ይሆን። እስቲ መላ አታጡምና ምክር ብጤ እፈልጋለሁ።

ያልቀናው - ከዳላስ

ወዳጆችን የዳላሱ ሰው ለምናልባቱ ያሁኑ ምኞትህ ቀደም ቢል ደግ ነበር። ለምን ብትል ሁሉም በጊዜው ያምራልና። አሁን ጓደኞና ወዳጅችህ በአብዛኛው ቤተሰብ ስለመሠረቱ ከመንፈሣዊ ቅናት በመነጨ ብቻ የምታደርገው የሴት አደን ከሆነ ቶሎ አቁመው። ትዳር ለመያዝ ወይም የጠበቀ የፍቅር ግንኙነት ለማድረግ በቅድሚያ ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። መጀመሪያ ለዚህ ዝግጁ ነኝ ወይ? ብለህ ራስህን ጠይቅ። ዝግጁነትህን ካረጋገጥክ በኋላ ወደ ድርጊቱ ለመግባት ተዘጋጅ።

ካንተ ጥያቄ ለመነሳት ያቹል:- የምትጠይቃቸው ሴቶች ጥያቄህን ተቀብለው ከአንዴም ሁለቴ እንደሚወጡልህ ተናግረሃል። ይኽም ማለት ዕድሉ እና ተቀባይነቱ ስላለህ ተስፋ አለህ ማለት ነው። እንደሚመስለኝ ችግሩ ያለው አቀራረብህ ላይ ሳይሆን አጨራረሱ ላይ ነው።

ሴቶች በተፈጥሮ አክብሮትን ይፈልጋሉ። ይኽ አርቴፊሻልም ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ወንዶች የሚፈልጓትን ሴት እጃቸው እስኪያገቡ የሚጠቀሙበት ዘዴ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ከልባዊ አክብሮት ለሴቶች የሚሰጡት ቦታ ነው።
በቅድሚያ ሴቶችን ስትተዋወቅ ማድረግ የማይገባህ ነገሮች አሉ። ጥቂቶቹን ልንገርህ።

በምንም ዓይነት ለመጀመሪያ ጊዜ ከሴት ጋር ስትወጣ ቤቴን ለምን አታይውም የሚል ሃሳብ እንዳታቀርብ። ይኼ ሴቶችን ከሚያስደነብረው ነገር ዋነኛው ነው። ተጨማሪ ሁለተኛ ዕድል ብታገኝ እንኳን እቤቴ ለምን የሚጠጣ ነገር ይዘን አንሄድም አትበል። ለምናልባቱ እሺ እንሂድ የምትል ብታጋጥምህ እንኳን ከሳሎኑ ውጪ መኝታ ቤቴን ለምን አታይውም የሚል ጥያቄ እንዳታቀርብ። ለዛች ሰዓት ጓደኛ ብቻ ሁናት።

በተለይ ለመጀመሪያ ቀን እሺ ብላህ አብራችሁ ለእራት ብትወጡ እንኳን ምሽቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የ"good night kiss" ስጪኝ ብለህ እንዳትጠይቅ። በተቻለ በመጣችሁበት አኳኃን ከአነሳሃት ቦታ መልሳት። በጨዋታ ጊዜ የንግግር መድረኩን አንተ ላለመያዝ ተጠንቀቅ፣ ለእሷ የመናገር ዕድል ስጣት። የፊለጎቸውን ደቂቃ ወይም ሰዓትም ቢሆን በእሷ ንግግር መሐል እየገባህ አታደናቅፋት።

በአመጋገብ በአኒጋገር ሥነ-ሥርአት አሳይ። እሷ ስትናገር እንደ ትረካዋ በፈገግታ እና በኃዘን አጅበው። ለምሳሌ ስለ ዱሮው ቦይ ፍሬንዷ እንኳን ብትነግርህ እንደ አቀራረቧ እና እንደ ታሪኩ በፈገግታ እና በሳቅ እንጂ ፊትህን የማጨማደድ ሁኔታ አታሳይ። ይኽም ከጅምሩ ባለፈ ነገር ቀናተኛ እንዳልሆንክ ይመሰክርልሃል። አንዳንድ ሴቶች ያለፈ ታሪካቸውን መተንፈስ ይወዱ ይሆናል። ለምሳሌ ስለእናቷ መታመም ወይም ስለ ቀድሞ ቦይ ፍሬንዷ ድንገተኛ ሞት ልታጫውትህ ትችላለች። ጨዋታዋን እንደአቀራረቧ አስተናግደው።

ከትውውቅ በኋላ ከመጀመሪያው ምሽት ጀምሮ ደግሞ መከተል ያለብህ ነገሮች አሉ። ከተቀበልካት ቦታ ስታነሳት ከመኪናህ ቶሎ ውጣና በእሷ በኩል ያለውን በር ከፍተህ አስገባት። ታዲያ አክብሮትህን የቸኮላ እና የግበር ይውጣ አታድረገው። በደንብ መቀመጧን አረጋግጠህ በሩን በጥንቃቄ ዝጋው። ቀጥለህም ወዴት ብንሄድ ይሻላል የሚል ጥያቄ እና ዕድሉን ለእሷ ስጣት። ገና ከመግባቷ ይዘሃት አንተ ወደ መረጥከው ቦታ አትፈርጥጥ።

የምትገቡበት ቦታ ስትደርሱ ቢቻል አቋቋምህ ወይም አገባብህ ከእሷ እኩል ይሁን እንጂ እሷን አታስከትላት ወይም ከኃላ አታድርጋት። ከለበሰችው በላይ የደረበችው ነገር ካለ ተቀበላት። ወንበር ስቦ የመቀመጡን ቅድሚያ ለእሷ ስጥ።

ለምታዙት ነገር ቅድሚያውን ለእሷ ስጥ፣ ምንም አንኳን አንተ ምርጫህን ቀደም ብለህ ብትወስንም እሷን ጠብቃት። በአመጋገብ ወቅት በፍፁም ላጉርስሽ ብለህ እንዳትጠይቅ ወይም እንዳትሞክር። ከቀናህ ወደፊት ያደርስሃል።

ለምታዙት የመጠጥ ዓይነት የእሷን እንጂ የአንተን ምርጫ አትጫንባት። ከእራት በኃላ ወይም በእራት ላይ ጨዋታ ለመጀመር ከፈለክ በፍፁም «ቦይ ፍሬንድ ነበረሽ ወይም አለሽ?» በሚል ጥያቄ እንዳትጀምር። ግድየለሽም መልሱን ሳትጠይቅ ከእሷ መመቻቸት ታገኘዋለህ። ቦይ ፍሬንድ ኖሯችው ሌላ ለመደረብ የሚፈልጉ ሴቶች ያስታውቃሉ። እንደነዚህ ዓይነት «ዋናቸውን ይዘው በትርፍ የሚጫወቱ ሴቶች» የምትሄዱበትን ቦታ ሳይጠየቁ ቀድመው የሚመርጡት እነሱ ናቸው። ከመኖሪያ ሠፈራቸው በእጅጉ ርቀው መሄድ ይፈልጋሉ። ይኽን የሚያደርጉ ከሚያቃቸው ማንኛውም ሰው ለመራቅ እና ላለመታየት ነው።

ለሴት ልጅ ሊሰጥ የሚገባውን አድናቆት አትንፈጋት። ስለቁንጅናዋ እና ስለአቋሟ አጋጣሚ እና አመቺ ጨዋታ ላይ ንገራት። ታዲያ ልትነግራት የፈለከው ነገር ከመጠን እንዳያልፍ ተጠንቀቅ። የቁመና አድናቆትህን አትደጋግመው።

በምንም ዓይነት መንገድ እሷ ማወቅ ፈልጋ ቀድማ ካልጠየቀችህ ስለአንተ የቀድሞው የፍቅር ሕይወት አታንሳ። ጥያቄው ከቀረበልህ ግን ጉራ ከመሳረር ተቆጠብ። ለምሳሌ የቀድሞ ፍቅረኞችህ ብዛትና ቁመና እንደ ከዋክብት አብዝተህ እና ቁንጅናቸውን አጋንነህ አታውራ። «በመጠኑ ነበረኝ፣ ግን አልሰራም» በሚል አጭር ቃል ቋጥረው። በግድ ማወቅ እፈልጋለሁ የሚል ጥያቄ ቢቀርብልህ እንኳን የማያስገምትህ መልስ እና «እሱን ወደፊት አወራሻለሁ» ማለቱን ምረጥ። የተዋወከትን ሴት የምትሰራውን ሥራ እና ያለህን ንብረት መጠን ከመናገር ተቆጠብ።

በስልክ ውይይት ላይ የምትናገረውን እወቅ፣ «ቀንሽ እንዴት ነበር? ሠላም ነሽ?» ከሚሉ ጥያቄዎች አትለፍ። አዲስ ትውውቅ የሚፈጥሩ ሴቶች ብዙ ጊዜ ከአዲሱ ሰው ጋር በየሰዓቱ ማውራት አይወዱም። እነሱ ከደወሉ እስከሚፈልጉት ሰዓት ድረስ ማውራቱ ደግ ቢሆንም በጨዋታ መሐል «ምን ለብሰሻል? አልጋ ላይ ነሽ» የሚሉ ጥያቄዎችን አታንሳ። ሰፍሳፋ መሆንክን ያሳብቅብሃል።

ሴቶች በተፈጥሮ ከወንዶች ይልቅ አእምሮን የማንበብ ችሎታ እንዳላቸው አትዘንጋ። ገና ከተዋወቃቸሁበት ሰዓት ጀምሮ አንተን እና ባሕርይህን እንደሚያነቡ ገምት። ስለዚህ ለአምስተኛው ጊዜ እስክትወጡ ድረስ ጠንቃቃ ሁን። በምንም መንገድ ምን ትሰሪያለሽ ምን ያክል ታገኛለሽ ከሚሉ ጥያቄዎች ራቅ። በምክራችን ተጠቅመህ ከቀናህ በሰርግ ጥሪው ሊስት ላይ መዝግበን።



ይኽ አምድ ስለ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ብርቅ እና ድንቅ ሥፍራዎች ያላቸው እውቅና ውሱን ለሆኑና በውጪው ዓለም ተወልደው ወይም አድገው ስለሀገራቸውን ታሪክም ሆነ ተፈጥሯዊ ውበት በቂ ዕውቀት ለሌላቸው እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን አምዱ ሃገራቸውን መጎብኘት ለሚጓዙ ሁሉ ጥሩ የምርጫ እይታን ያካትታል።

ጥቂት ስለ ዘመን አቆጣጠር

በሳሲና በለጠ

መስከረም ለ2006ኛ ጊዜ ጠባ።

መስ- በግእዙ አለፈ የሚለው ፍቺ ሲኖረው - ከረም ደግሞ ክረምት ማለት ነው። መስከረም ስንል ክረምቱ አለፈ እያልን ነው ማለት ነው። በ6ኛ ቀኗ የተወለዱትን ሁሉ በ4 ዓመት አንዴ ልደታቸውን እንዲያከብሩ የምታስገድደው ጳጉሜ ዘንድሮም 6ኛ ቀኗን ነፍጋ ለ2005ኛ ጊዜ አልፋ ፤ ወንዶች ችቦ ለኩሰው ኢየሃ አበባዬን ሊያዜሙ ሴቶች "አበባዬ ሆይ ለምለም" ሲሉ ፤ ምድርም በአደይ አበባ መኸሰች። የኑሮን ምንቸት ውጣ! የገንፎ ምንቸት ግባ - እንኳን ለ58 ዓመት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በሰላም አደረሳችሁ። (58 ያልኩት ተሳስቼ አይደለም። ልክ ነኝ። ያንብቡትና ይደርሱበታል።)

የራሳቸው የዘመን አቆጣጠር ካላቸው ጥቂት (ምናልባትም 2 ወይም 3) የአፍሪካ ሀገራት አንዷ የሆነችው ሀገራችን ከዓለም ተለይታ በብቸኝነት አዲስ ዘመኗን አከብራለች። ለሌሎች የዓለም ሀገራት ይህ ወቅት አዲስ ዘመንን የሚያስቡበት ጊዜ አይደለም።

ከአምስት ዓመታት በፊት ሺህ ዓመታችንን (ሚሊኒየማችንን) ስናከብር በጃፓኗ አቆጣጠር ጥቅምት 29/30 ቀን 2007ዓ.ም.፤ በጎርጎርዮሳዊው የዘመን አቆጣጠር መስከረም 12 ቀን 2007ዓ.ም.፤ በእስራኤል መስከረም 2፤5768ዓ.ዓ.፤ በጥንት ግብፅ 6243 ዓ.ዓ.፤ በጥንት ሮማን 2760፤ በሒጂራ ሕዳር 2፤1428፤ በቅብጥ(Copt) 03/02/1724፤ በቻይና(ደራጎን) 11/22/216፤ በሒንዱ 06/01/5108፤ በማያ 5126፤ በዓለም አቀፍ የጊዜ መለኪያ አቆጣጠር(ISO) ቀን-7 ሳምንት-45 ዓመት-2007 ነበር። (የዘመኑ ታሪክ፤ ዲ/ን መላኩ አስማማው ቢሰጠኝ፤ ነሐሴ 2000ዓ.ም.፤ ገጽ 8-9) ከአምስት ዓመታት በኋላ ዘንድሮም በፍጥረታት (ጨረቃ፤ ፀሐይ...) ዑደት የተወሰኑ ልዩነቶች ቢኖሩም የእኛ መስከረም አንድ በሌሎች አቆጣጠሮች የተለየ ወር ላይ ያርፋል።

መስከረም ፳፻፭ ዓ.ም — September - October 2012

እሑድ Sunday	ሰኞ Monday	ማክሰኞ Tuesday	ረቡዕ Wednesday	ኀሙስ Thursday	ዓርብ Friday	ቅዳሜ Saturday
		፩ 11 1	፪ 12 2	፫ 13 3	፬ 14 4	፭ 15 5
፮ 16 6	፯ 17 7	፰ 18 8	፱ 19 9	፲ 20 10	፲፩ 21 11	፲፪ 22 12
፲፫ 23 13	፲፬ 24 14	፲፭ 25 15	፲፮ 26 16	፲፯ 27 17	፲፰ 28 18	፲፱ 29 19
፳ 30 20	፳፩ 1 21	፳፪ 2 22	፳፫ 3 23	፳፬ 4 24	፳፭ 5 25	፳፮ 6 26
፳፯ 7 27	፳፰ 8 28	፳፱ 9 29	፴ 10 30			

መስከረም ፩ የዘመን መለወጫ በዓል — September 11 Ethiopian New Year
መስከረም ፳፯ የመስቀል በዓል — September 27 The Finding of the True Cross (Meskel)

የዘመን አቆጣጠርን ደንብ ያዘጋጁ ሰዎች ለአቆጣጠራቸው መነሻ ያደረጓቸው የተለያዩ ጉዳዮችን ነው። የሒጂራ አቆጣጠር (Islamic calendar) መነሻው ነቢዩ መሀመድ ነው። አይሁድ መነሻ ያደረጉት ዘመነ ፍጥረትን ነው። ግሪኮች ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ776 ዓመት የኦሎምፒክ ዓመታዊ ውድድር የጀመሩበትን ዓመት ነው። የጥንት ግብፃውያን ግን ምንም እንኳን ከጥንት ጀምሮ እያንዳንዳቸው በ30 ቀኖች በተከፋፈሉ 12 ወሮችና አምስት ተጨማሪ ቀኖች የተጠቃለሉ 365 ቀኖችን የያዘ ዓመት ቢኖራቸውም እንደሌሎቹ አገሮች ለአቆጣጠራቸው መነሻ የሚሆን አንድ የተወሰነ ምክንያት አልነበራቸውም።

ኢትዮጵያን ጨምሮ የራሳቸው የዘመን አቆጣጠር ያላቸው ሀገራት የባሕረ ሐሳባቸው (Calendar) መሠረት ጥንታዊ አምልኮአቸው ወይም አንዳች የተፈጥሮ ክስተት አልያም ከነዚህ ጋ የተያያዘ ጉዳይ ነው። በተለይ ጨረቃና ፀሐይ በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች አቆጣጠሮች ዑደት ላይ መሠረታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋሉ። የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በፀሐይ ዑደት ላይ የተመሠረተ (Solar) ሲሆን የእስራኤላውያንና የሒጂራ (እስልምና) አቆጣጠር ደግሞ ጨረቃን መሠረት ያደረገ (Lunar) ነው።

ጎርጎርዮሳዊው (የአውሮፓውያን) የዘመን አቆጣጠር ጨረቃንም ፀሐይንም(Luni-Solar) ይጠቀማል። በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር 13 ወራት ሲኖሩ ከጳጉሜ በስተቀር ሁሉም እኩል 30 ቀናት አሏቸው። በአንድ ዓመት ውስጥ 365(በአራት ዓመት አንዴ 366) ቀናት አሉ። አንድ የጨረቃ ዓመት 354 ቀን አለው። የጨረቃ አቆጣጠር ያላቸው ሀገራት ከእኛ እኩል መስከረም አንድ ላይ ዓመታቸውን ቢጀምሩ እኛ ዓመቱን ጳጉሜ 5 ከማጠናቀቃችን በፊት እነሱ ነሐሴ 24 ዓመቱን ጨርሰው አዲስ ዓመታቸውን ይቀበላሉ። የ11 ቀን ልዩነት ይኖራል (ይህ ትርፍ በሊቃውንቱ አጠራር አበቅቴ ይባላል።)

በእስልምና ከረመዳን ወር በኋላ የሚከበረው የኢድ በዓል በጨረቃ እንደሚወሰን ሁሉ የአይሁድ ፋሲካም ኒሳን በተባለው ወራቸው በ14ኛው ቀን በጨረቃ መሰረት ላይ ተመሥርቶ ነው። በፀሐይ አቆጣጠር የምትቆጥረው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንም አብዛኛው በዓላቷ እንደ ፀሐይ አቆጣጠር በማይቀያየሩ ውሱን (Fixed) ቀናት ቢውሉም የትንሣኤን በዓል የምታከብረው ጨረቃ መሰረ ከሆነች በኋላ በሚመጣው እሑድ ነው። ይህም ኒሳን 14 ከሚከበረው የአይሁድ በዓል ጋር በአንድ ቀን እንዳይከበር ቀደምት አባቶች ቀኖና (Canon) ስለሠሩ ነው። የቀጣይ ዓመትን አጽዋማትና በዓላትን ጊዜ ለማስላትም ከላይ የተጠቀሰውን አበቅቴ ትጠቀማለች።

አንድ ዓመት የ12/13 ወራት ዑደት (Cycle) እንደሆነ ሁሉ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ዑደቶች አሉ። የዑደት ጊዜያቸውን ጠበቀው የሚከሰቱ የተፈጥሮ ክስተታትም ብዙ ናቸው። በሥነ ፈለክ (Astronomy) ምርምር ዘርፍ ውስጥ የምትታወቀው የሀሌይ ኮሜት በ76 ዓመት አካባቢ አንዴ ትታያለች። የፀሐይ ግርዶሽም የሚከሰትበት ወቅት አለው። ልክ እንደ ክረምትና በጋ ጊዜያቸውን ጠበቀው ሁሉም ይከናወናሉ። አዲስ ዓመትን ዐውደ ዓመት ብለን የምንጠራው ከዚህ ጋ በተያያዘ ነው። ዐውድ ማለት ዙሪያ፤ ክበብ፤ ከበር እስከ በር፤ ካመት እስካመት ያለ ለታጠረ ለተወሰነ ክበብ ላለው ሁሉ ይነገራል። (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ ኪዳነወልድ ክፍሌ፤ 1948ዓ.ም.፤ ገጽ 687) አንድ ዓመት ዑደቱን በመስከረም ጀምሮ በጳጉሜ ይጨርሳል።

መስከረም አንድ የዑደቱ መጀመሪያ ስለሆነ ዐውደ ዓመት ይባላል። እዚህ ጋ መሬት በፀሐይ ዙሪያ 365 ¼ ቀን ዑደቷን (ዙረቷን-) ማጠናቀቋ ለፀሐይ አቆጣጠር መሠረት መሆኑን መገንዘብ ያሻል። (ለጨረቃ አቆጣጠርም የጨረቃ ዑደት መሠረት ነው።) ዐውደ ዓመት እንደምንለው ዐውደ ዕለት፤ ዐውደ ወርኀ፤ ዐውደ አበቅቴ፤ ዐውደ ፀሐይ፤ ዐውደ ማኅተም፤ ዐውደ ቀመር የሚባሉ አሉ። ዐውደ ዕለት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት ሰባት ቀኖች እየተመላለሱ መምጣታቸውን የሚያመለክት ነው።

ዐውደ ወርኀ ወሩ ራሱ ተመላልሶ የፀሐይ ዓመታትንና የጨረቃ ዓመታትን የሚያገናኝ ዑደት መሆኑን የሚያመለክት ነው። ዐውደ አበቅቴ ማለት 19 ዓመት ነው። ይህም የ19 ዓመት ተመላልሶ መምጣት ማለት ነው። (በ19 ዓመት አንዴ የሚያጋጥም የዕለት፤ ቀን፤ ተፈጥሯዊ ክስተት መገጣጠም እንዳለ ልብ ይሏል።) ዐውደ ፀሐይ የ28 ዓመቶች መመላለስ ነው። ዐውደ ማኅተም የ76 ዓመት ተመላልሶ መምጣት ማለት ነው። ዐውደ ቀመር ደግሞ የ532 ዓመት ተመላልሶ መምጣት ነው። ሥርዓተ ቤተክርስቲያን፤ ሊቀ ካህናት ክንፈገብርኤል አልታዬና ቀሲስ ጌታቸው ደጀኔ፤ የካቲት 2002ዓ.ም.፤ገጽ 146-147) እነዚህ ዑደቶች አስፈላጊ ስሌቶች ናቸው።

በምሳሌ ለማስረዳት ያህል ኢትዮጵያና ምእራባውያን በ19 ዓመት አንዴ ብቻ የትንሣኤን በዓል በአንድ ቀን ሊያከብሩ ይችላሉ። ክርስቲያኑና መስሊመ በ19፤ በ28 ወይም በ76 ዓመት አንዴ ጥምቀትንና ኢድን በአንድ ቀን ሊያከብሩ ይችላሉ። እነዚህንና ሌሎች ክስተቶችን በማስላትና በመተንበይ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ዑደቶቹን ማወቅ ተገቢ ነው። ለምሳሌ የፀሐይ ግርዶሽ የሚከሰተው መች እንደሆነ ከታወቀ በዛች ጊዜ ዐይንን ከጉዳት ለመጠበቅ መነጽር ወይም ሌላ ዘዴን ለመጠቀም መዘጋጀት ይቻላል።

እነዚህን ዑደቶች መሠረት በማድረግ አንዱ የዑደት ዘመን ተጠናቆ ሌላው ሲጀመር እንደ አዲስ አንድ ብሎ ዘመንን መቁጠር የተለመደ ነው። በዐፄ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት የተጻፈ አንድ የከብረ ነገሥት መጽሐፍ "በላሊበላ ዘመን በ409 ዓ.ም. ተጻፈ" ይላል።


YADAM LLC
Wholesale, Import & Export
የሚቀጥሉትን ሸቀጦች እናከፋፍላለን
- ጤፍ
- የይርጋ ጨፌ ቡና
- በርበሬ እና ምጥን ሽሮ
- ኮሰረት
- ከሰል
- ቡላ
- ገብስ
- እጣን
- ጀበና
- ጌሾ
- ሱፍ
- ሰልፍራይዚንግ
- ረከቦት
- ጥቁር እና ነጭ አዝሙድ
- የእንጀራ ላስቲክ
- ኮረሪማ እና ሌሎችም...
6303 Little River Tpke
Suite # 160
Alexandria, VA 22312
Tel: 703 642 3996
Cell: 571 213 9816
በጅምላ ለምትገዙ
ልዩ ዋጋ ስላለን ይደውሉልን

ዐፄ ላሊበላ የነገሠው ከ10ኛው - 13ኛው ምዕት ዓመት ጊዜ በነበረው የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ሲሆን መጽሐፉ "በላሊበላ ዘመን በ409 ዓ.ም. ተጻፈ" ማለቱ ግራ ሊያጋባ ይችላል። ዐውደ ቀመርን (የ532 ዓመት ዑደት) ላወቀ ሰው ግን ግራ አያጋባም። ለዚህ ነው በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ "እንኳን ለ58 ዓመት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በሰላም አደረሳችሁ።" ያልኩት። ይበልጥ ግልፅ እንዲሆን ላስረዳ።

መስከረም ላይ 2006 ዓ.ም.ን መቀበላችን ግልፅ ነው። ከክርስቶስ መወለድ በፊት ያሉትን 5500 ዓመትን ስንደምርበት 7506 ዓ.ዓ.(ዓመተ ዓለም)ን እናገኛለን። (መስከረም ላይ 2006ዓ.ም.ን ወይም 7506ዓ.ዓ.ን ተቀበልን ማለት እንችላለን) 7506ን ለ532 ስናካፍል 14 ጊዜ ይደርስና 58ን ቀሪ እናገኛለን። ይህም ማለት በዘመን አቆጣጠራችን አሥራ አራት 532ቶች አልፈው አሥራ አምስተኛው ከተጀመረ 58 ዓመቱ ነው ማለት ነው። (ዓመተ ዓለም ማለት የዓለም ዓመት (ዕድሜ) ማለት ነው። ዓለም ከተፈጠረችበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጥር ነው።)

ዓመተ ዓለምን በመጠቀም የዘመኑን ስያሜ ማወቅ በሀገራችን የተለመደ ነው። ዓመተ ምኅረቱ ላይ 5500 ደምረው ዓመተ ዓለምን ካገኙ በኋላ ዓመተ ዓለሙን ለአራት በማካፈል ቀሪው አንድ ከሆነ ዘመኑ ዘመነ ማቴዎስ ይባላል። 2 ከሆነ ማርቆስ፤ 3 ከሆነ ሉቃስ ሲባል ምንም ቀሪ ከሌለ ወይም ቀሪው 0 ከሆነ ዘመኑ ዘመነ ዮሐንስ ይባላል። የ2006ን የዘመን ስያሜ ለማውጣት በመጀመሪያ ዓመተ ዓለሙን እናግኝ፤ 2006 + 5500 = 7506፤ በመቀጠል ለ4 ዓመተ ዓለሙን እናካፍለው፤ 7506 / 4 = 1876 ቀሪ 2 ይሆናል። ስለዚህ 2006 ዓ.ም. ዘመነ ማርቆስ ነው ማለት ነው።







ማዕድ

መብላት እንጂ መሥራት ከተሳናቸው

ከዶሮ ጥበስ ለ2 ሰው



ዶሮ ጥበስ ለ2 ሰው

አስፈላጊ ጥሬ ዕቃዎች፡-

1 መካከለኛ ዶሮ
1 መካከልኛ ጭልፋ (150 ግራም) የደቀቀ ነጭ ሽንኩርት
4 ሾርባ ማንኪያ የደቀቀ ሽንኩርት
ግማሽ የሾርባ ማንኪያ በርበሬ
1 የሾርባ ማንኪያ የደቀቀ ሮዝመሪኖ
ግማሽ ሾርባ ማንኪያ የተፈጨ ቁንዶ በርበሬ
6 የሾርባ ማንካ (100 ሚሊ ሊትር) ዘይት

አዘገጃጀት

1. ዶሮውን የፈላ ውሃ ውስጥ ነክሮ ላባውን በማስወገድ ሆድ ዕቃውን አውጥቶ ከጣሉ በኋላ ቆዳውን በወረቀት መለብለብ እና ሲፀዳ በትንሽ ሽሮ ወይም በትንሽ የፉርኖ ዱቄትና በርበሬ ካሹ በኋላ በውሃ ማጠብ፣
2. ቀይ ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ሮዝመሪኖ፣ በርበሬ እና ቁንዶ በርበሬውን አድቅቆ በአንድ የሾርባ ማንኪያ ዘይት በመለወስ የዶሮውን ገላ አሸቶ ማስቀመጥ፣
3. ሁለት ሰዓት ያኽል ካቆዩት በኋላ ብረት ምጣድ ላይ እያገላበጡ ቡናማ እስኪመስል መጥበስ፣
4. ቀሪውን ዘይት በብረት ድስት አግሎ ዶሮውን ከብረት ምጣድ ወደ ብረት ድስት ማጋባት፣
5. በዝግታ በማገላበጥ አብስሎ ለገበታ ማቅረብ፣

በሚጠበስበት ጊዜ ውሃ በዝቶበት ቅቅል እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን፣ በዘይት በሚጠበስበት ጊዜ ዘይቱ ስለሚፈላ ሰውነት ላይ ካረፈ አደጋን ስለሚያስከትል ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

የሸገር ወጎች

የ"ዮሐንስ ራዕይ እና የመለስ ራዕይ" እንዲሁም ለመለስ የተሣፈው አስገራሚ ደብዳቤ!!

አጩሌ - ከሸገር

ዲያፖራው ወዳጄ እንዴት- እንዴት ሠንብተህልኛል? አንተ እዛ በሰው ሐገር የቢል ስትረስ መቆሚያ፣ መቀመጫ አሳጥቶ ሲያሯሩጥህ እኛን ደግሞ ሸገር ላይ የሰውዬው ራዕይ እያሯሯጠን እንገኛለን:: (የትኛው ራዕይ?) ምናምን ብለህ አደራህን ቦተሊካ አታናግረኝ:: ያው አንድ ዓመት ሞላቸው ተብሎ ከተሰባሞ ራዕይ- ራዕይ መሸተት ከጀመረች ሠነበተችልህ::

እኚህ የቤት አከራዬ ወ/ሮ ይርገዱ በቀደም ዕለት ጠዋት ‹‹ይሄ ሰውዬ ሞቶም አይተወንም እንዴ?›› ሲሉ ሠምቼ ጠላትህ ከው ይበል ድርቅ ብዬ ቀረሁልህ:: ይሔ አባባላቸው ‹‹ከሸብርተኝነት አይተናነስም... ምናምን›› ተብለው ሲቀፈደዱ ታይቶኝ በማግስቱ ሌላ የሚከራይ ቤት ፈልጌ እልም አልኩልህ:: ‹‹የአበራሽን ጠባሳ ያየ...›› አሉ አበው:: በስንት ነገር መማረር እያለ እንዴት በራዕያቸው ሠው ያሾፋል? እንዴትስ ይማረራል? መማረር ከፈለገ በፀሐይዋ በምስራቅ መውጣት... በከረምቱ ዝናብ... በሠማይ ቀለም... ኧረ በስንት ነገር መማረር እየተቻለ በእሳቸው ራዕይ? አይደረግም! ቂቂ... ቂ... ቂ...

ወዳጄ መቼም የሸገር ሰው ኑሮ አንጐሉን ሲያዞርለት ኮሜዲያን ወጥቶታል፣ በመፎተት አንደኛ ሆኖልሃል:: ታዲያ ሰሞኑን ሸገር ላይ ስትቀለድ የሠማሁዋትን አውግቼህ ብናልፍስ? ነገርዬዋ ምን መሰለችህ? እኚህ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር (እስከመቼ አዲስ እንደምንላቸው የዲማው ጊዮርጊስ ይወቀው እንጂ) ‹‹ሕገ-መንግስቱን ከማንበብ ይልቅ መፅሐፍ ቅዱስ በማንበብ ጊዜያቸውን ያጠፋሉ›› እየተባሉ ብዙ ጊዜ ይታማሉ:: እንዲያውም ብዙ ጊዜ ‹‹የመለስን ራዕይን!›› ለማለት እየፈለጉ በስህተት ‹‹የዮሐንስ ራዕይን...›› ይላሉ እየተባሉ ይፎገርባቸዋል::

ታዲያ ብዙ ጊዜ በረከት ሥምኦን ወደ ቤተ መንግስት ብቅ ሲል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዮሐንስ ራዕይን እያነበቡ ቢያገኛቸው በብስጭት እንዲህ አለ አሉ:- ‹‹አንተ ሰውዬ የመለስን ራዕይ ስትጨርስ የዮሐንስን ራዕይን ጀመርክልን?›› ብሎላቸሁ አረፈው:: ቅድም እንዳልኩህ የሸገር ሰው መቧለት ይወድ የለ በአንድ ጀምበር ተቀባብሏት ‹‹ራዕይ!›› ሲባል ‹‹የዮሐንስን ነው የመለስን?›› እያለ ሲቀልድህልህ ከረመ::

ዲያስፖራው ወዳጄ አንዱ ለቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የፃፋትን ደብዳቤ ሸገር ላይ ፎቶ ኮፒ እየተደረገች ውስጥ ለውስጥ ስትበተን አግኝቼ አነበብኳት:: ፀሐፊውን ባላውቀውም አንጀቴ ሰፍ... ሰፍ... ሰፍ... ሰፍ ቢልብኝ እስቲ አንተም አንበባት ብዬ እንደወረደች ላኩልህ::

‹‹ይድረስ! ለቀድሞውና ለአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትሬ፣ ድንጋዩን ዳቦ ላደረጉትና የድሆች አባት እንዲሁም ባለራዕይ ለሆኑት መለስ ዜናዊ...›› መቼም አንባቢ ነዎትና በርዕሱ መርዘም አይበሳጩብኝም! ጠመንጃ ተንተርሰው ያነቡ (እቺን ቃል ጠበቅ አድርገው ያንብቢት ጌታዬ ኋላ እንዳይቀየሙኝ) የነበረ ሰው፣ እንዴት ክንድዎን ተንተርሰው ይህቺን ለማንበብ ይሠንፋሉ ተበሎ ይጠረጠራል? እንዲያውም እንደእኔ ስንፍና አሳጠርኩት እንጂ እንደ እርስዎ ብርታትስ ቢሆን ከዚህ ሠባት እጅ በረዘመ ነበር::

... ግን እንዴት አሉልኝ አባቴ? አባቴ የምሎት መልጭ ያልኩ ቺስታ በመሆኔና ‹‹የድሃ አባት›› መሆንዎን ስለሰማሁ ነው:: ‹‹የድሃ አባት መሆንዎን የሠማሁ ቀን እንዴት ነበር የተደሰትኩት! ቀድሞውንም አባቴ ጥሎኝ የሄደው በልጅነቴ ነበር፣ ድህነቴን ሳይንቁ አባቴ መሆንዎን ስሰማ፣ ደስታ መሰሎት የተደሰትኩት... በቃ ጥሎኝ የጠፋው አባቴ እሳቸው ናቸው አልኩ! አባቴ ትቶኝ የሄደው ገና ነፍስ ሳላውቅ ስለነበር፣ ጫኳ ገበቶ ሊሆን እንደሚችል፣ ‹ልጄን› ብሎ ያልፈለገኝ ትግሉ ፋታ አልሰጥ ብሎት እንጂ ጨክኖብኝ እንዳልሆነና እርስዎ ሊሆኑ እንደሚችሉ ጠረጠርኩ::

በዛ ላይ አንዳንድ የሠፈሬ ሰዎች ሲያዩኝ ‹‹ይሔ ልጅ ግን አሳቸውን አይመስልም?›› ሲሉ ስሰማማ ይተውኝ አልኩት... ታዲያ ባለፈው ሰሞን ሌላኛዋ ልጅዎ የሆነችው ‹‹ሰምሃል›› በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንዳስቀመጠች ብሰማ ጊዜ ‹‹እንደሚባለው የድሆች አባት አይሆኑ ይሆን?›› የሚል ከፉ ጥርጣሬ ልቤ ገብቶ ሠላም ሲነሳኝ አልሠነበተም መሰለዎ? ታዲያ መልሱን እራሴ አገኘሁትና ትንሽ እፎይ አልኩ::

‹‹ድንጋይን ዳቦ ያደረጉ መሪ›› እንዴት የደሃም፣ የሐብታምም አባት መሆን ያቅታቸዋል? አልኩ:: ቀድሞውኑም በመጠርጠሬ እራሴን ወቀስኩ:: እራሴው ለራሴ ግለሂስ አውርጄ ከእርስዎም ፣ ከእራሴም ታረቅኩ:: መቼም ሞት ከፉ ነው:: ቢሆንም ሳይፈቅዱ ወሰዶት ብለን ፈቅደን እንዲሞቱ ልናደርግዎ አልወደድንም:: እርስዎ ባንቀላፉበት ቅፅበት ራዕዮን ቀሰቀስነው:: አንዳንድ ‹‹ፀረ-ራዕይ›› የሆኑ ኃይሎች ‹‹ከሳቸው በላይ ራዕያቸው አሠቃየን›› ብለው ቢናገሩ አያዳምጧቸው::

እኛ የእርስዎ ልጆችና ‹‹የራዕዮ ሎሌዎች›› ግን ‹‹ለራዕዮት እኛ አለንሎት›› ማለታችንን አናቆምም:: በተቻለን ሁሉ ሙሉ ሐገሪቷ በእርስዎ ራዕይ እያጠመቅናት ነው:: ለአቅመ-ፖለቲካ ካልደረሰ ትንንሽ ልጆች በፖለቲካ እስከሸመግሉ የፖለቲካ ባለፀጐች ሁሉም ስለራዕዮ እየዘመረ ይኖኛል:: ሰሞኑን ደግሞ እንደሚያዩት የእርስዎ ሐገራቸን አረንጓዴ የማድረግ ራዕይ ተከትለን (ያው የእርስዎን ነገር መከተል ልማዳችን ነው ያውቁታል) በችግኝ ተከላ ተጠምደንሎታል:: ይሄው በምሠራበት መስሪያ ቤት (ራዕይ ቤት ቢባል ደስታዬ ወደር የለውም) እንኳን ይሄን ሙሉ ሳምንት አረንጓዴ ‹‹ቲሸርት›› እንድንለብስ ታዘን ወደ ሥራ እንድንገባ ሆኗል::

አይ እርሶ ተዓምረኛ እኮ ነዎት! የሞቱ ሠሞን ጥቁር አለበሱን:: አሁን በሙት አመትዎ ደግሞ አረንጓዴ አለበሱን:: እንደው በሚቀጥለው ዓመት ምን ያለብሱን ይሆን? በእርግጥ እንዳንድ ሃሳዊ ፖለቲከኞች ‹‹ኖረውም፣ ሞተውም ማቅ ያለብሱን›› ሲሉ ያደምጡ ይሆናል:: በተለመደው ይቅር ባይነትዎና ትግስትዎ ይተውአቸው ጌታዬ! እኛው ራዕዮትን ተገን አድርገን እንዋጋቸዋለን::

‹‹ለራዕያችን ይፈሳል ላባችን›› የሚል ጠንካራ አቋማችንን ያወቁታል መቼስ? ‹‹ለራዕያችን ይፈሳል ደማችን›› የማንለውም የጠላቶቻችንን ደም ልናፈስ እንጂ ደማችን ሊፈስ እንደማይችል በሕይወት ሲኖሩ ያወቁታል በሚል እምነት ነው:: ውይ! ‹‹ሲኖሩ ያውቁታል›› አልኩ እንዴ ጌታዬ? መቼ ሞቱና ነው ሲኖሩ ያወቁታል የምለው?! እባክዎ ይቅርታ ያድርጉልኝ::

እንደው ግን የሥማይ ቤት ኑሮ እንዴት ይዘዎታል አባቴ? ይሄውልዎ... እርሶ ‹‹መኖሪያዎን የቀየሩ›› ሰሞን እንዳንድ በጥላቻ የታወሩ አናዳጅ ሰዎች:‹‹እኔ ብቻ ልግዛ ነውና ነገሩ ሥማይ ቤትም ሄደው እንዳያስቸግሩ›› ብለው ለአፄ ቴዎድሮስ የተገጠመን ግጥም ለእርስዎ አላደረጉትም መሥልዎት? የስንቱን እጅ ከቀረጠ ጉጉስ ጋር የሚያወዳድሩዎት እኮ በዘጠና ሰባት የቆረጡአቸውን ‹‹ጥቂት ጣቶች›› አስታውሰው ነው::

አሁን እስቲ ጣት የቆረጠ እጅ ከቆረጠ እኩል ሊዳኝ ይገባዋል? ደግሞ እርስዎ ጣት ቢቆርጡ አላርፍ ያለች ጣትን እንጂ የእንደኔ አይነቱን አርፎ የተቀመጠ ጣት መቼ ቆረጡ? ያው በዚያን ግዜ ሰይጣን አሳስቶኝ ‹‹የባለጣቶቹ›› ደጋፊ እንደመሆኔ ጣቱን ሊቆርጡ ይችሉ ነበር:: በመሃሪነቶ ማሩኝ:: እኔም ውለታውን አልረሳምና ከመቆረጥ ባተረፉልኝ ጣቶቼ ይህንን ልዕፍልዎ በቃሁ::

እርሶ ‹‹እጅ እንነሳለን›› እንኳን ሲሉ እንደ አዜው አልነበረም አይደል? ቢሆንም በእርስዎ ያምራል ለነገሩ... በሣቅም፣ በጥይትም ሲገሉ ማን እንደርስዎ? በምድር ላይ ሳሉ ታምረኛ ነበሩ:: እዛስ እንዴት ነዎት አሁን? በእርስዎ እንደምትዘጋጅ ሳይነግሩኝ (ሳይነግሩን ስንት ነገር ሠርተውልን ይሆን?) ያዘጋጅዋት በነበረችው ‹‹አዲስ ራዕይ›› መፅሄት ስለእርስዎ ብቻ ባወራችበት አትሚ ምን አለች መሰልዎ?...

‹‹እንደማንኛውም በአካዳሚ የመጠቀ ሰው ለራሱና ለግሉ የሚያስብ ቢሆን ኖሮ በወር 6ሺ ብር ደሞዝ ብቻ እየበላ የሚኖር ሰው ባልሆነ ነበር›› (ገፅ 46)

በእርግጥ አንዳንዶች ይሄን ‹‹ሞዴል ቀልድ›› አድርገው ሊያስቡት ይችላሉ:: እኔና ‹‹የራዕዮ ሥር ሎሌዎች›› የሆንን ታማኞች ግን፣ ለዓመታት አብረው ውለው ያደሩ የባለቤትዎ ምስክርነት አለንና እናምናለን (እንኳን እቺን ስንቱን ሲነግሩን አምነን የለ? አለመሞትዎንም አምነናል እንኳን...)

ምንም እንኳን በቀን ሶስቴ ባልበላም በመፅሄቱ ‹‹መለስ! በቀን ሶስቴ ሙበላትን ያሳካ መሪ›› የሚለውን ያነበብኩ ጊዜ በሙሉ ልቤ አምኖለሁ:: በእርግጥ የዚህ ስኬትዎ እንቅፋት ላለመሆን በቀን አንዴ እበላው የነበረ ምግቤን ሶስት ቦታ ከፍዬ በቀን ሶስቴ አደርገው ጀምሬያለሁ::

በኪራይ ቤት የምንከራተት ከርታታ ቤት አልባ ብሆንም ቅሉ ‹‹መለስ! ቤት አልባነት እንዲያከትም ፊር የቀየሰ መሪ›› በሚለውም አምናለሁ:: ምንአልባትም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ‹‹እሳቸው ናቸው የሰጡኝ›› ብዬ የአከራዮቼን ቤት እንደምጠቀልላት ተስፋ አለኝ:: ምን ሕዝቡ እንደው ሁሉ ነገሩን ለእርስዎ ሲል መተው ጀምሮ የለ? (ያለህን ነገር ጥለህ ተከተለኝ ብለው ነበር እንዴ ግን?)...

ዲያስፖራው ወዳጄ! የዚህ ባለራዕይ ደብዳቤ እንዲህ በቀላሉ የሚልቅ ስላልሆነ ለቀጣይ ወር የደብዳቤውን የመጨረሻ ክፍል እና እስከ ወር ደግሞ ሸገር ላይ የተባለ... የተነገረ... የታሰበውን አወጋሃለሁ::
ቸር ቆዮኝ!

ይቀጥላል.....

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!

የናፍቆት ኢትዮጵያ መጽሔት የሚገኝባቸው መደብሮች

	PHONE #
VA	
Abay Market	703-998-5388
Meaza Resturant & Market	703-820-2870
Mena Market	703-869-7842
Azewa Market & Carry Out	703-212-6740
Dama Market & Carry Out	703-920-3559
Lideta Lemariam -Twahido curch	703-618-4479
Nazreth Baltna Market	703-635-7843
Tena Adam Market	703-933-6038
Tsedey Grocery and carry out	703-461-9420
Wubu Market	703-820-0889
Enat Kitifo	703-642-3628
Mark Computer & Tax Service	703-256-9113
DC	
Abesha Market & Carry Out	202-232-1919
Fasika Resturant	202-722-0999
Gee Market	202-829-5505
Liya Market	
Selam International Market	202-722-2792
Mark Computer & Tax Service	202-541-7979
Markie Unisex Salon	202-541-7979
MD	
Addisu Gebeya	
Weder Gebeya	301-562-5901
Boston, MA	
Ethio-African Art	
Mulat Mengistu	978-652-8259
Habesha Restaurat	
Atlanta, GA	
Merkato Mart	404-320-9777
Denver, CO	
Merkato Market	303-399-6116
Dallas, TX	
Maru Grocary	214-373-6278
Star Mart	972-530-6039
Markato International	469-879-3051
Columbus, OH	
Addisu Market	614-235-2727
Markato Market	513-386-7754
Los Angeles, CA	310-407-9559
Gudaye Demessie	
Beachside Café	
Rahel Veggie Cuisine	
Addis-Ethiopian Restaurant	
Awash Ethiopian Restaurant	
Mesob Ethiopian Restaurant	
Chicago, IL	
Kukulu Market	773-262-3169

Mark's Corner



Mekuria Negia
Alexandria, VA

እኛና ኑሮአችን

የ«ማርክ ኮርነር» ጽሑፍ የሚያተኩረው በታክስና ከታክስ ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች በንግድ ዘርፍ ላይ ሆኖ፣ በተለይ ባለንበት ሃገር ሕግ እና ደንብ አብሮ በምን መልክ መጓዝ እንዳለብን የሚጠቁምና መልካሙን የአድጎት ጉዳና ለወገኖቼ ለማሳየት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ባለፉት ተከታታይ ፅሑፎቼ ላይ በተለይ በንግዱ መስክ ለተሰማሩ ወገኖቼ በተሰማራንባቸው የንግድ መስኮች የገቢ ምንጮችና ገቢዎችን ምን መሆን እንዳለበትና ለወደፊቱ በምን መልክ በቀላሉ ልናደራጀውና ትርፍም ልናገኝበት እንድምንችል በተለያየ መልኩ ለማስነበብ ሞክሬአለሁ፣ በዚህም ምክር የተጠቀሙ አያሌ ወገኖች በስልክ እና በአካል በምክሩ ያገኙትን ጥቅም አውግተውኛል።

እኛና የዕለት ከዕለት ኑሮአችን እየቀጠለ ባለበት ሁኔታ ለኑሮአችን የምናወጣው ወጭና የምናገኘው ገቢም እንደዚሁ ቀጣይ ይሆናል። ከዚህም በተያያዘ ከጠቅላላው ገቢዎችን ላይ በአበላጫው ወጪአችንን ሸፍነን ገቢያችንን ለማሣደግ እንጥራለን። ታዲያ በግል ስራ የምንተዳደር ከሆነ ካለዕቅድ ወይም ባለሙያን ሳናማክር በነሲብ እና በሞራል ብቻ የምንጥር ከሆነ እንደበለስ (እድል) ሆኖ እንደ ሎተሪ ካልቀናን በስተቀር ኪሣራው ከመሬት እንዳንነሣ እና ዳግም እንዳናንሰራራ ከማድረጉም ባሻገር ለወደፊቱም ልንሞክረው ወይም ልንሰራው ላሰብነው የንግድ ሥራ እንቅፋት እና ሳንካ ይሆናል።

አንድን የንግድ ሥራ ለመጀመርም ሆነ የጀመርነውን አትራፊ ለማድረግ በቅድሚያ ሀሳብን ሰብስብ በማድረግ በዕቅድ ከጅምሩ በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ ለማድረግ መቻል ብልህነት ከመሆኑም ሌላ ወደፊት ሊደርስ ከሚችለው የተዝረከረከ ሥራ ያድነናል።

የሀገሬ ሰው "ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጪት" የሚለው ያለምክንያት ያለመሆኑን መገንዘብ ያለብን እዚህ ላይ ነው። ሁሉም ነጋዴ መሆን ይፈልግ ይሆናል። ግን እንደ ሌሎቹ የንግድ ቤት ባለቤት መሆኑን እንጂ ያለዕቅድ ንግድ መጀመሩን አይገነዘብም።

ለዚህ እንዲሆነኝ አንድ ምሳሌ ላቅርብ፡- አንድ ግለሰብ ወደ ቢሮዬ ብቅ ይልና እባክህን የንግድ ሥራ ለመጀመር አፈልጋለሁ እድሜዬን በሙሉ ሀገሬም እያለሁ የኖርኩት በንግድ ሥራ ነው ይለኛል። ግን ይኽ ለንግድ ከፍተኛ ፍቅርና ፍላጎት ያለው ግለሰብ በካፒታል ደረጃ ያለው $50,000 ሲሆን ሌላ ንብረትም ሆነ በአበዳሪዎች የሚመዘንበትም የክሬዲት ታሪክ የለውም፣ በአሜሪካም የኖረው ለአጭር ጊዜ ነው። እሱ ሊሰማራበት የሚፈልገው የንግድ ዘርፍ ግን የ $300,000 ዋጋ የሚጠይቅ የንግድ ፍሬንቻይዝ ማድረግ ነው።

ሀሳቡ እና በትልቁ መመኘቱ መልካም ሆኖ ለአበዳሪው ክፍል ግን ምን ይዞ እንደሚቀርብ የተገነዘበ አልነበረም። ባንኮች ገንዘብ ያበድራሉ፣ ግን ለሚያበድሩት ገንዘብ ጥሩ መያዣ ወይም መልካም የብድር ታሪክ ይፈልጋሉ።

ከዚህም በመነሳት ለዚህ ወገኔ ልመክር የምችለው ቢኖር ይኽን ሃሳቡን አጎልብቶ አብሮት ሊሰራ የሚችል ተመሳሳይ ፍላጎት ያለው ሰው እንዲፈልግ ወይም የንግዱን ስፋት መጠኑን እና ካፒታሉ ዝቅ ያለ ዘርፍ እንዲመርጥ ማድረግ ነው። አብሮት የሚሰራ ሰውም ሲመርጥ በመተማመን ላይ በመመሥረት ሳይሆን በሕጋዊ ውል እና ተዓማኒነቱንም መመዘን ወደፊት ሊመጣ ከሚችለው ከወገን ጋር ከሚደረግ ጭቅጭቅ ያድነዋል።

በአለንበት በአሜሪካ ምድር እንደየስቴቱ የንግድ ሕግና በንግድ ሥም የምንጠይቀው ብድር መጠኑ ይለያያል። ሁሉም የንግድ ዘርፍ የሚጠይቃቸው ዋናዎቹ በቂ ካፒታል እና የስራ ልምድ ወይም ጥረት ናቸው።

ለዚህም የምመክረው ቢኖር በመጀመርያ እባካችሁ ወገኖቼ $50,000 ይዛችሁ የ$300,000 ዋጋ ያለውን ንግድ በማሰብ ራሳችሁን አታስጨንቁ የሚል ነው። አንድን ንግድ በትንሹ ጀምሮ ማስፋፋት እየተቻለ በሌለ ካፒታል የማይሞከረውን ማሰብ ከምኞት አያልፍምና። ለምሳሌ፡- የ50,000 ንግድ ስናስብ $100,000 ቢኖረን በተዝናና መልክ የምንጅምረውን ንግድ አትራፊ ማድረግ እንችላለን።

አንደኛ የያዝነውን በተረጋጋ መንፈስ አስበንበት በዕቅድ ተማክረን መሰረቱን አሳምረን ከጀመርነው ትርፍን እንጂ ኪሳራ እንደማይገጥመን እርግጠኛ መሆን እንችላለን።

ሌላው እድሜያችን ወደ ጡረታ ተቃርቦ እያለ 365 ቀናት ዓመቱን ሙሉ እረፍት ወደማይሰጠውን የቸርቻሮ ስራ መግባት ውጣ ውረድና ጭንቀት በራሳችን ላይ ከመፍጠር ሌላ ጥቅሙ ብዙ አይታይም። እድሜንም ማሳጠር እንዳይሆን መጠንቀቅ ነው።

በተጨማሪም ቅዳሜና እሁድን ከቤተሰብ ጋር ማሳለፍና የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳይ ላይ ሲያሳልፍ የኖረ ሰው በ60 አመቱ ተነስቶ የቸርቻሮ ንግድ ውስጥ ቢግባ ቅዳሜም ሆነ እሁድ ቤተሰብና ማህበራዊ ጉዳይ የማይታሰቡ መሆኑና በቅድሚያ መገንዘብ አለበት። ትናንሽ የንግድ እና የቸርቻሮ ስራ ባለቤቱ በቅርብ ክትትል ካላደረገ በጥናት እንደተረጋገጠው ኪሳራ እንጂ የሚጠቅም ትርፍ አስመዝግቦ አይታይም። አንዳንዴም ከባለቤቱ ይልቅ ተቀጣሪው ሰራተኛ ንግድ ቤቱን ሲወርሰው ታይቶአል። ሊወርሰው ይችላል ስንል ከፍተኛ ተጠቃሚው ተቀጣሪው ይሆናል ማለታችን ነው።

በዛሬው ምክሬ ማስገንዘብ የፈለኩት ፍላጎታችንን፣ አቅማችንን እና ልምዳችንን ካለን ካፒታል ጋር በማገናኘት በእቅድ እንኑር ማለቴ ነው።

ያገሬ ሰው " ታሞ ከመማቀቅ አስቅድሞ መጠንቀቅ " ያለው ያለምክንያት አይደለምና።

የዚህ ምክር አቅራቢ አቶ መኩሪያ ነጊያ የንግድ ሥራን በተመለከተ የተሳካ የንግድ ሥራ እንዲሰሩ በመምከር ማኅበረሰቡ በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ አትራፊ እንዲሆን የሚረዳ ባለሙያ ነው።

ድረ-ገፃችንን ይጎብኙ

ለናፍቆት ኢትዮጵያ መጽሔት አንባቢያን እና ቤተሰቦች

የናፍቆት ኢትዮጵያ መጽሔት የዝግጅት ክፍል አዲሱ የኢትዮጵያውያን ዓመት የደስታና የብልጽግና እንዲሆንላችሁ እየተመኘ፣ በአዲሱ ዓመት ከመጽሔታችን በተጨማሪ የድረ-ገጽ በመክፈት ለማኅበራዊ መገናኛ ማብቃቱን ሲገልጽ በታላቅ ኩራት ነው።

ይኽ ድረ-ገጽ በቪዲዮ የተለያዩ ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሃገራችንን ሙዚቃዎችን እንዲሁም፣ የእውቅ ገጣሚዎችን ሥራ በአውዲዮ ከፍሉ ሲያካትት፣ በናፍቆት ኢትዮጵያ አማካኝነት እስካሁን የታተሙ መፃሕፍትን በቀጥታ ከድረ-ገፁ ላይ ማግኘት እና መግዛት የሚችሉበትን መንገድ አመቻችቷል። እስካሁን ድረስ መፃሕፍቶቹን በስልክ በመጠየቅ በፓስታ እንድላክላቸው የሚጠይቁ አንባቢያን ቁጥራቸው ቀላል ባለመሆኑ ይኽ አጋጣሚ ችግሩን ሙሉ በሙሉ ያስወግደዋል ብለን እናምናለን።

ከዚህም በተጨማሪ ማኅበራዊ ምክሮችን እና ከቀድሞው አምዶቻችን ላይ የተወሰዱ ፅሑፎችን በአምደኛች መስኮት ላይ እንዲቀርቡና አንባቢያን የሚመለከቱበትን ዕድል ከፍተናል።

ድረ-ገጹ በየጊዜው መሻሻል እንዲያሳይ በቅርቡ ጥረት የምናደርግ ሲሆን የጎብኚዎችም አስተያየት ለዚሁ ቁልፍ ሚና ይጫወታል የሚል እምነት አለን።

ድረ-ገጹን ለመጎብኘት

www.nafqotethiopia.com

ሙሉውን ድረ-ገጽ በመጎብኘት በአቅርቦታችን መዝናናት፣ መማር እና እውቀት መቅሰም ይችላሉ ብለን እንገምታለን።
ድረ-ገፁን ከጎበኙ በኋላ መሻሻል ወይም ሊጨመሩ የሚገባቸውን ነገሮች እባክዎ ያካፍሉን።





መልካም አዲስ

መስከረም ጀሺጌ Sep - Oct 2013

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
			፩ 11	፪ 12	፫ 13	፬ 14
፭ 15	፮ 16	፯ 17	፰ 18	፱ 19	፲ 20	፲፩ 21
፲፪ 22	፲፫ 23	፲፬ 24	፲፭ 25	፲፮ 26	፲፯ 27	፲፰ 28
፲፱ 29	፳ 30	፳፩ 1	፳፪ 2	፳፫ 3	፳፬ 4	፳፭ 5
፳፮ 6	፳፯ 7	፳፰ 8	፳፱ 9	፴ 10		

ጥቅምት ጀሺጌ Oct - Nov 2013

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
					፩ 11	፪ 12
፫ 13	፬ 14	፭ 15	፮ 16	፯ 17	፰ 18	፱ 19
፲ 20	፲፩ 21	፲፪ 22	፲፫ 23	፲፬ 24	፲፭ 25	፲፮ 26
፲፯ 27	፲፰ 28	፲፱ 29	፳ 30	፳፩ 31	፳፪ 1	፳፫ 2
፳፬ 3	፳፭ 4	፳፮ 5	፳፯ 6	፳፰ 7	፳፱ 8	፴ 9

ህዳር ጀሺጌ Nov - Dec 2013

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
፩ 10	፪ 11	፫ 12	፬ 13	፭ 14	፮ 15	፯ 16
፰ 17	፱ 18	፲ 19	፲፩ 20	፲፪ 21	፲፫ 22	፲፬ 23
፲፭ 24	፲፮ 25	፲፯ 26	፲፰ 27	፲፱ 28	፳ 29	፳፩ 30
፳፪ 1	፳፫ 2	፳፬ 3	፳፭ 4	፳፮ 5	፳፯ 6	፳፰ 7
፳፱ 8	፴ 9					

ታህሳስ ጀሺጌ Dec - Jan 2013/14

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
		፩ 10	፪ 11	፫ 12	፬ 13	፭ 14
፮ 15	፯ 16	፰ 17	፱ 18	፲ 19	፲፩ 20	፲፪ 21
፲፫ 22	፲፬ 23	፲፭ 24	፲፮ 25	፲፯ 26	፲፰ 27	፲፱ 28
፳ 29	፳፩ 30	፳፪ 31	፳፫ 1	፳፬ 2	፳፭ 3	፳፮ 4
፳፯ 5	፳፰ 6	፳፱ 7	፴ 8			

ጥር ጀሺጌ Jan - Feb 2014

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
				፩ 9	፪ 10	፫ 11
፬ 12	፭ 13	፮ 14	፯ 15	፰ 16	፱ 17	፲ 18
፲፩ 19	፲፪ 20	፲፫ 21	፲፬ 22	፲፭ 23	፲፮ 24	፲፯ 25
፲፰ 26	፲፱ 27	፳ 28	፳፩ 29	፳፪ 30	፳፫ 31	፳፬ 1
፳፭ 2	፳፮ 3	፳፯ 4	፳፰ 5	፳፱ 6	፴ 7	

የካቲት ጀሺጌ Feb - March 2014

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
						፩ 8
፪ 9	፫ 10	፬ 11	፭ 12	፮ 13	፯ 14	፰ 15
፱ 16	፲ 17	፲፩ 18	፲፪ 19	፲፫ 20	፲፬ 21	፲፭ 22
፲፮ 23	፲፯ 24	፲፰ 25	፲፱ 26	፳ 27	፳፩ 28	፳፪ 1
፳፫ ፴ 2	፳፬ 3	፳፭ 4	፳፮ 5	፳፯ 6	፳፰ 7	፳፱ 8

ሰ ዓመት ይሁንልን



መጋቢት ጀሚጌ March - Apr 2014

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
9	፩ 10	፪ 11	፫ 12	፬ 13	፭ 14	፮ 15
፯ 16	፰ 17	፱ 18	፲ 19	፲፩ 20	፲፪ 21	፲፫ 22
፲፬ 23	፲፭ 24	፲፮ 25	፲፯ 26	፲፰ 27	፲፱ 28	፳ 29
፳፩ 30	፳፪ 31	፳፫ 1	፳፬ 2	፳፭ 3	፳፮ 4	፳፯ 5
፳፰ 6	፳፱ 7	፴ 8				

ሚያዚያ ጀሚጌ Apr - May 2014

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
			፩ 9	፪ 10	፫ 11	፬ 12
፭ 13	፮ 14	፯ 15	፰ 16	፱ 17	፲ 18	፲፩ 19
፲፪ 20	፲፫ 21	፲፬ 22	፲፭ 23	፲፮ 24	፲፯ 25	፲፰ 26
፲፱ 27	፳ 28	፳፩ 29	፳፪ 30	፳፫ 1	፳፬ 2	፳፭ 3
፳፮ 4	፳፯ 5	፳፰ 6	፳፱ 7	፴ 8		

ግንቦት ጀሚጌ May - June 2014

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
					፩ 9	፪ 10
፫ 11	፬ 12	፭ 13	፮ 14	፯ 15	፰ 16	፱ 17
፲ 18	፲፩ 19	፲፪ 20	፲፫ 21	፲፬ 22	፲፭ 23	፲፮ 24
፲፯ 25	፲፰ 26	፲፱ 27	፳ 28	፳፩ 29	፳፪ 30	፳፫ 31
፳፬ 1	፳፭ 2	፳፮ 3	፳፯ 4	፳፰ 5	፳፱ 6	፴ 7

ሰኔ ጀሚጌ June - July 2014

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
፩ 8	፪ 9	፫ 10	፬ 11	፭ 12	፮ 13	፯ 14
፰ 15	፱ 16	፲ 17	፲፩ 18	፲፪ 19	፲፫ 20	፲፬ 21
፲፭ 22	፲፮ 23	፲፯ 24	፲፰ 25	፲፱ 26	፳ 27	፳፩ 28
፳፪ 29	፳፫ 30	፳፬ 1	፳፭ 2	፳፮ 3	፳፯ 4	፳፰ 5
፳፱ 6	፴ 7					

ሐምሌ ጀሚጌ July - Aug 2014


እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
		፩ 8	፪ 9	፫ 10	፬ 11	፭ 12
፮ 13	፯ 14	፰ 15	፱ 16	፲ 17	፲፩ 18	፲፪ 19
፲፫ 20	፲፬ 21	፲፭ 22	፲፮ 23	፲፯ 24	፲፰ 25	፲፱ 26
፳ 27	፳፩ 28	፳፪ 29	፳፫ 30	፳፬ 31	፳፭ 1	፳፮ 2
፳፯ 3	፳፰ 4	፳፱ 5	፴ 6			

ነሀሴ / ጳጉሜ ጀሚጌ Aug - Sept 2014

እ S	ሰ M	ማ T	እ W	ሐ T	አ F	ቅ SA
				፩ 7	፪ 8	፫ 9
፬ 10	፭ 11	፮ 12	፯ 13	፰ 14	፱ 15	፲ 16
፲፩ 17	፲፪ 18	፲፫ 19	፲፬ 20	፲፭ 21	፲፮ 22	፲፯ 23
፲፰ 24	፲፱ 25	፳ 26	፳፩ 27	፳፪ 28	፳፫ 29	፳፬ 30
፳፭ 31	፳፮ 1	፳፯ 2	፳፰ 3	፳፱ 4	፴ 5	፩ 6

ምንም እንኳ በተሟላ መልኩ ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ባይሆንም፤የሩቅም ሆነ የቅርብ ጊዜ የታሪክ መዝገብ ቢገለጥ፤ በተለያዩ የመ·ያ መስክ ተሰማርተው ለአገራቸውና ለወገናቸው ያላቸውን ዕውቀት፤ ጉልበትና አቅምያለ ስስት የሰጡ የበርካታ ኢትዮጵያውያን አሻራ ማግኘት መቻሉ የሚያከራክር አይደለም፤ በመሆኑም በዚህ ዓምድ በወታደራዊ፤ ዲፕሎማሲያዊ፤ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዘርፍ የዚህ አሻራ ባለቤት የሆኑ የሩቅም ሆነ የቅርብ ጊዜ ሰዎችን ለማስተዋወቅ እና ለማስታወስ ጥረት እናደርጋለን::

ታላቁ የታሪክ ሊቅ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት



ዛሬ በህይወት የሌሉ አንድ አንጋፋ የታሪክ ሊቅና በህይወት በነበሩባቸው ዘመናት አያሌ ተግባራትን አከናውነው ያለፉ ሰውን እናነሳለን:: እ'ኚህ ታላቅ ሊቅ ፕሮፌሰር ታደሠ ታምራት ናቸው:: ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት የተወለዱት አዲስ አበባ ሲሆን፤ አባታቸው አቶ ታምራት ጉበረየስ ሲባሉ፣ እናታቸው ደግሞ ወ/ሮ ብርሐኔ ሙሉነህ ይባሉ ነበር:: የፕሮፌሰር ታደሰ ወላጆች የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ከመሆናቸው በተጨማሪ በቤተ ክርስትያኒቱ ውስጥ በልዩ- ልዩ የኃላፊነት ቦታ ላይ የሚሰሩ ነበሩ::

ለምሳሌ:- አባታቸው የመንበረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ቤተ- ክርስቲያን መስራችና እንዲሁም በወቅቱ ለነበሩት ፓትሪያርክ የቅርብ ረዳት ሆነው ሲሰሩ የነበሩ ናቸው:: ፕሮፌሰር ታደሠ ሀሁ ፊደልን የቆጠሩት በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነው:: ከዚያም ወደ ቅድስት ስላሴ ሄደው መደበኛ ትምህርታቸውን መቀጠል ጀመሩ:: በቅድስት ስላሴ መማራቸውም ለኢትዮጵያ ቅርስ እና ታሪክ መተዋወቂያ መድረክ እንደፈጠረላቸው በአንድ ወቅት ተናግረው ነበር:: ከዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በኮከበ ፅባህ ትምህርት ቤት ተምረዋል:: በመቀጠልም በሐረር መድኃኒአለም ሁለተኛ ደረጃ ተምረው አጠናቀዋል::

ፕሮፌሰር ታደሰ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ወስደው በጊዜው ‹‹ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ›› ተብሎ ወደሚጠራው ዩኒቨርስቲ ተቀላቀሉ:: በዩኒቨርስቲ ቆይታቸውም በመጀመሪያ ዲግሪ ለመመረቅ በቁ:: ፕሮፌሰር ታደሠ ለጥንታዊው የኢትዮጵያ ታሪክ እንዲሁም የመካከለኛውን የኢትዮጵያን ታሪክ በመመርመር እና በማጥናት ሠፊ ጊዜያቸውን ወስደዋል:: ያላቸውን እውቀት የበለጠ ለማስፋት ከነበራቸው ምኞት አንዱ በዓለም አቀፍ ደረጃ መማር ነበር:: በዚሁ የተነሳ እንግሊዝ ሐገር የትምህርት እድል አግኝተው ወደ ለንደን አቀኑ:: በዛ ቆይታቸውም ከጥንታዊ የአፍሪካ ጥናት ተቋም (School of oriental and African Studies) ወይም በምህፃረ ቃሉ (SOAS) እ.ኤ.አ በ1968 ዓ.ም. የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በታሪክ ትምህርት ተቀበሉ::

ፕሮፌሰር ታደሠ ከትምህርታቸው በኋላም ወደ ሐገራቸው መጥተው በታሪክ ትምህርት ከፍል ረጅም አመታትን ሲያስተምሩ ቆይተዋል:: በዚህም ታላላቅ የታሪክ ምሁራንን እንዳፈሩም ይነገርላቸዋል:: እ'ኚሁ ምሁር ከፃፏቸው ሥራዎቻቸው መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስላቸው "Church and state in Ethiopia 1270-1527" የሚለው ነው::

ይህን መፅሐፋቸውን በተመለከተ አያሌ የታሪክ ልሒቃን በሚፅፏቸው ፅሁፎች እንደ ምንጭ የሚጠቀሙበት የታሪክ ሰነድ ነው:: ‹‹የኢትዮጵያን ታሪክ ለመፃፍ የሚነሳ ሁሉ ይህን መፅሐፍ ሳይጠቀምበት ወይም ሳያነበው ታሪክ የሚፅፍ ሰው የለም›› እየተባለ ይነገራል::

በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የተፃፉ የታሪክ ፅሁፎችን ማለትም የዲግሪ ፣ የማስትሬት እና የዶክትሬት መመረቂያ ፅሁፎች፣ እንዲሁም የጥናትና የምርምር አርቲክሎችን የመረመረ ባለሙያ እንደተናገረው ከሆነ፡- ‹‹የፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት መፅሐፍ በአብዛኛዎቹ ፀሐፊያን ዘንድ እንደ ሪፈረንስ ተጠቅሷል፡፡

ስለዚህ መንግስትና ቤተ ክህነት ለኢትዮጵያ / Church and state in Ethiopia/ የተሠኘው መፅሐፋቸው በታሪክ ትምህርት ውስጥ እጅግ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ መፅሐፉ የመካከለኛውን ዘመን ማለትም ከ1270 ዓ.ም. እስከ 1527 (እ.ኤ.አ) ያለውን የታሪክ ሁኔታ ነው የሚያሳየው፡፡ ይህን የፕሮፌሰር ታደሠን መፅሐፍ በተመለከተም የተለያዩ ምሁራን አስተያየት ይሠጡበታል፡፡ ለምሳሌ፡- ‹ፕሮፌሰር ማሪላይን ኢ. ሐልድማን› የተባለው ምሁር 'African Zion: The sacred Art of Ethiopia' የተሠኘው መፅሐፍ ደራሲ እንደገለፁት በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ በክርስትናው አለም ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆነችውን ኢትዮጵያን በሚገባ የሚተነትን፣ ወይም የሚያሳይ መፅሐፍ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በለንደን ዩኒቨርስቲ የእስልምና ሃይማኖቶች ጥናት ተቋም ውስጥ የሚያስተምሩት ቻርለስ ኤፍ ቤኪንግሃም ስለዚሁ መፅሐፍ በሰጡት አስተያየት፡- መፅሐፉ የኢትዮጵያን መንግስትና የክርስትናውን ሃይማኖት በሰፊው የሚሰበክባትን ኢትዮጵያን ለማወቅ ትልቅ የታሪክ ማጣቀሻ መሆኑን መስክረዋል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በዚሁ Church and state in Ethiopia በተሠኘው መፅሐፍ ላይ ቅሬታ የተሠማቸው አካልም አሉ፡፡ ከእነዚህ አንዱ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም ናቸው፡፡ ፕሮፌሰር በቅርብ ባሳተሙት ‹‹መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ›› በሚለው መፅሐፋቸው ውስጥ ከሚያብጠለጥሏቸው የታሪክ ምሁራን መካከል ፕሮፌሰር ታደሠ ታምራትም ይገኙበታል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ገለፃ ፕሮፌሰር ታደሠ የፃፉት ፈረንጆች ለራሳቸው እንዲመቻቸው አድርገው የሠሩት ታሪክ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ በመፅሐፉም ምርር ብለው ተችተዋል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ግን መፅሐፉ ትልቅ የታሪክ ማጣቀሻ ሆኖ ለረጅም ጊዜ አለ፡፡ በተከታታይ ቢታተምም አያለቀ እንደገና ይታተማል፡፡ ገበያ ውስጥ በእጅጉ የሚፈለግ፣ ነገር ግን በቀላሉ የማይገኝ በጣም ውድ የሚባል መፅሐፍ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ታደሠ ታምራትን በቅርብ የሚያውቋቸው ሰዎች እንደሚገልፁት በሐገርኛ እውቀት እና ጥበብ የበለፀጉት ኢትዮጵያን ማየት ህልማቸው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡



በተለይ የኢትዮጵያ ታሪክ ሲፃፍ የውጭ ሐገር ሠዎች ከሚፅፉት የሐገር ውስጥ የታሪክ ምሁራን እንዲፅፉት ምክርና ተግሳፅ ይሰጣሉ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በማስተማርና በመመራመር ረጅም ዓመት የቆዩት ፕሮፌሰር ታደሠ ታምራት ከሚጠቀስላቸው ተግባራቸው አንዱ የኢትዮጵያን ጥናትና ምርምር ተቋም እንዲመሠረት አስተዋፆኦ ካደረጉ አካላት መካከል አንዱ እርሳቸው እንደሆኑ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኋላ ወደ አሜሪካ ያቀኑት ፕሮፌሰር ታደሰ ረጅም ጊዜ ማለትም እስከ ህልፈተ ህይወታቸው ድረስ እዚያው ነበሩ፡፡ በቆይታቸውም የካበተው የታሪክ እውቀታቸውን በልዩ- ልዩ ዩኒቨርስቲዎች ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- በካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ፣ እንዲሁም የክብር ተጋባዥ መምህር ሆነው ኖርዝ ዌስተርን ዩኒቨርስቲ እና ኤሊኖን ዩኒቨርስቲ ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ በጥናቶቻቸውም ታላቅነት አለም አቀፍ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ ከሠሯቸው ጥናቶችና ፅሁፎች መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡-

- Some notes on the fifteenth-century stephanite heresy.
- Persecution and religious controversies.
- S short note on the traditions of pagan (14th and 15th centuries)
- Church and state in Ethiopia the early centuries.
- A short note on the Ethiopian Music.
- Hagiographies and the reconstruction of medival Ethiopian history.
- The Mateb
- The abbots of Dabrahayq 1248-1535

እኚህ ታላቅ የታሪክ ሊቅ ግንቦት 15 ቀን 2005 ዓ.ም በተወለዱ በ78 ዓመታቸው ያረፉ ሲሆን፤ ስርዓተ ቀብራቸውም በቺካጐ ከተማ ተፈፅሟል፡፡



ይህንን ጽሑፍ ማንበብ ከቻሉ ደስ ይበልዎት! !
እጅግ በጣም ጥሩ የሆኑ ጠቃሚ የአማርኛ መጻሕፍት
በነፃ ሊያገኙ እንደሚችሉ ያውቃሉ?
ወደ www.good-amharic-book.com ይሂዱ!
እዚያው ላይ እያሉ ሊያነቡ ይችላሉ፣
ወደ ኮምፒውተርዎ ሊወስዱ ይችላሉ፣
ፕሪንት አድርገው ሊጠቀሙ ይችላሉ።
ጥያቄ ወይም እስተያየት ካለዎት
texlap@juno.com Brad Lapsley ን ያነጋግሩ።

የቃላት ሠንጠረዥ ጨዋታ

በሰንጠረዡ ውስጥ ተደብቀው ያሉት ቃላቶች ከታች የተዘረዘሩት ናቸው። ከላይ ወደታች፣ ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራም ሆነ በአግዳሚው ቀጥታ ወደታችም ሆነ ወደ ላይ እያነበባችሁ፣ ያገኛችኋቸውን ቃላት ከነዚህ ውስጥ ካሉ አስምሩባቸው።

ጨረቃ
ባህላዊልብስ
ዓለም
ፋሲል
አልኮል
መሠረት
የላምበረት
እረኛ
መንገድ
መድረክ
ብርትኳን
ህብረተሰባዊነት
ስነፅሁፍ
አቢሲንያ
አመለኛ
ደብረብርሀን
ፖስታ
ብርሀን

አ	መ	ለ	ኛ	በ	ት	ክ	ድ	ሰ	ጀ	ቀ	ወ	ሰ	ት	ፋ	የ
ት	ሸ	ደ	በ	ህ	ረ	ሸ	ድ	በ	አ	ታ	ሮ	ፕ	ና	ሁ	ም
ነ	ለ	ስ	ብ	ከ	ብ	ው	ደ	ፋ	ል	ደ	ስ	ፈ	ፈ	ወ	ራ
ዊ	ረ	ፖ	ል	ረ	ሜ	ል	ዳ	ሹ	ኮ	አ	የ	ፖ	ኬ	ቲ	ላ
ባ	ኬ	ሲ	ሸ	ስ	ብ	ር	ባ	ሪ	ል	ት	ረ	በ	ም	ላ	የ
ሰ	ፋ	ል	ም	ር	ሚ	ር	ማ	ና	ያ	እ	ም	ክ	ቨ	ና	ስ
ተ	አ	ደ	ት	ፈ	ክ	ፍ	ሀ	ቶ	ስ	ን	ረ	ል	ማ	ግ	ብ
ረ	ው	ኳ	ረ	ጣ	ል	ፍ	ም	ን	ሉ	ፕ	ሲ	ኛ	ር	ራ	ል
ብ	ን	ፊ	ሠ	ጣ	ሁ	ቴ	ብ	ዋ	ሩ	ፋ	ስ	ቢ	ክ	ሜ	ዊ
ህ	ላ	ቨ	መ	ፅ	ፍ	ቃ	ረ	ጨ	ፋ	ደ	በ	ል	አ	ር	ላ
ዝ	ት	ድ	ነ	ር	መ	ን	ገ	ድ	ር	እ	ቃ	ፍ	ተ	ከ	ህ
ላ	ረ	ስ	ብ	ቀ	ጥ	ብ	ስ	ኖ	ዳ	ዮ	ጀ	ፈ	ር	ና	ባ
ክ	ፒ	ብ	ው	ማ	ፋ	ሯ	ዓ	ለ	ም	እ	ሳ	ም	ፍ	ፋ	ት

ለመጀመሪያ ጊዜ ያወጣነው የሠንጠረዥ ጨዋታ ብዙም የማያስቸግር በመሆኑ ሁላችሁም እንድትሞክሩት
ስናበረታታ፣ ሙሉ በሙሉ ሙሌቶቹን ላገኘ ተሳታፊ አንድ መፅሐፍ በአድራሻው እንልካለን።

መልሱን በሚቀጥለው እትም ላይ እናቀርበዋለን።

ፖፕ ፓየስ 11ኛ አጼ ኃይለ ሥላሴን ለማስከዳት ስላደረጉት ሙከራ

ኪዳኔ ዓለማየሁ

እንደሚታወቀው፤ ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን ለሁለተኛ ጊዜ በወረሩበት ዘመን፤ በዓለም-አቀፍ ሕግ በተከለከለ፤ በብዙ አውሮፕላኖች በተነሰነሰ የመርዝ ጋዝ በመጠቀም ጭምር፤ ለጊዜውም ቢሆን ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግሱ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ወደ እንግሊዝ ሐገር ተሰደው ለጥቂት ጊዜ አዚያ በመጠለል ትግላቸውን ቀጥለው ነበር።

በዚያን ጊዜ፤ ሥልጣናቸውን ለኢጣልያን መንግሥት እንዲያስረክቡና በሚቸራቸው ገንዘብ የተንደላቀቀ ኑሯቸውን እንዲቀጥሉ ብዙ ጉትጎታ ኢጋጥሟቸው ነበር። በዚህ ጽሑፍ የሚተኮርበት ልዩ የነበረ ጉትጎታ፤ የቫቲካን፤ በተለይ በጊዜው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪ በነበሩት፤ የፖፕ ፓየስ 11ኛ ሙከራ ነው። ለዚህም ዋናው ማስረጃ፤ "Ethiopia Under Mussolini (Fascism and The Colonial Experience), 1985; በተሰኘው መጽሐፉ፤ አልቤርቶ ስባኪ (Alberto Sbacchi) ከእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መዝገብ በመጥቀስ እንደሚከተለው ያተተው ነው፤

".....Father Cyril C. Martindale, the Jesuit scholar representing the Pope, confirmed that the secretary of state at the Vatican, Eugenio Cardinal Pacelli (later Pope Pius XII), offered Haile Selassie 1 million (Sterling Pounds) on behalf of Italy in return for his abdication." P 123

ትርጉም፤ የፖፑ ወኪል የነበሩት ጀስዊቱ ምሑር፤ አባ ሲሪል ሲ. ማርቲንዴል፤ ባረጋገጡት መሠረት የቫቲካን መንግሥት ዋና ጸሐፊ፤ ዩጂኒዮ ካርዲናል ፓቼሊ (በኋላ ፖፕ ፓየስ 12ኛ) ኃይለ ሥላሴ ሥልጣናቸውን እንዲለቁ በኢጣልያን መንግሥት ስም አንድ ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ አቅርበውላቸው ነበር።

ከላይ ለተጠቀሰው ሐተታ፤ ጸሐፊው (ስባኪ) ያቀረበው ማስረጃ ምንጭ፤ "FO 401/1937/XXIX/ No.45" ነው።

በተጨማሪ፤ ሌላው አስደናቂ ጉዳይ ይኸው ጸሐፊ (ስባኪ) ተመራምሮ ያገኘው ማስረጃ፤ የተፈፊ መኮንን (በኋላ አጼ ኃይለ ሥላሴ) አሠልጣኝ የነበሩት የካቶሊክ ጳጳስ አንድሬ ማሪ ኤሊ ጃሮሶ የፈጸሙት ተግባር ነው። ጸሐፊው እንዳተተው፤

"Bishop Andre Marie Elie Jarosseau, Haile Selassie's former tutor and a man who had influence over him, also invited the exiled ruler to recognize Italian sovereignty over Ethiopia. By submitting to Italy he could rule with Italian consent." P. 124

ትርጉም፤ የኃይለ ሥላሴ የቀድሞ አሠልጣኝና ተሰሚነት የነበራቸው ጳጳስ፤ አቡነ አንድሬ ማሪ ኤሊ ጃሮሶ፤ ስደተኛው መሪ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ገዢነት እንዲቀበሉ ጋብዘው ነበር። ለኢጣልያ ተገዢ ከሆኑ በኢጣልያ ፈቃድ ሊገዙ ይችላሉ።

ለዚህም ሐተታ፤ ስባኪ ማስረጃው የሚገኝበትን ምንጭ እንደሚከተለው አቅርቧል፦

"Times (London), 29 April 1938; Le Petit Parisien, 22 August 1939; La Garonne, 22 August 1939; Bernoville, Monseigneur Jarosseau et la Mission des Gallas, p. 360" p. 127

በነገራችን ላይ፤ በአቶ ዘውዴ ረታ "የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት" መጽሐፍ፤ ጃሮሶ፤ ምንም ማስረጃ ሳያቀርቡ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ፋሺሽቶችን አውግዘዋል ማለታቸው ተገልጿል።

እውነቱ ግን፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ፋሺሽቶችን የባረኩ መሆናቸውን ያረጋገጠው ማስረጃ፤ ኢ.ኤ.አ የካቲት 13፤ 1937 ዓ/ም (February 13, 1937) በታዋቂው በኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጣ (New York Times) ላይ እንደሚከተለው ተዘግቦ ይገኛል፦

"Earlier today the Pontiff (Pope Pius XI) had given his recognition of Italian sovereignty over Ethiopia by bestowing his apostolic benediction upon Victor Emmanuel as "King of Italia and Emperor of Ethiopia."

ትርጉም፤ ቀደም ብሎ፤ ዛሬ፤ አቡኑ (ፖፕ ፓየስ 11ኛ) ቪክቶር ኢማኑኤልን "የኢጣልያ ንጉሥና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት" በማለት ባርከው ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ሥልጣን አረጋግጠዋል።

እርምት የሚያስፈልገው ሐተታ፤

ከዚህ በላይ በተጠቀሱትና እንዲሁም ከዚህ ቀጥሎ በሚቀርቡት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች መሠረት፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛና ቫቲካን ከሙሶሊኒና ከፋሺሽቱ መንግሥት ጋር እጅና ጓንት በመሆን በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው የጦር ወንጀል ተጠያቂ ስለ መሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም። ነገር ግን "የኃይለሥላሴ መንግሥት" በተሰኘ መጽሐፋቸው፤ የቀድሞ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ተጠያቂ አለመሆናቸውን (ገጽ 295-315) በመጻፋቸው አንዳንድ ሰዎች እየተወናበዱ ነው።

ለምሳሌ፤ ሚያሚ፤ ሚኒያፖሊስ፤ ጀኒቫና አዲስ አበባ ከሚኖሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የመጽሐፉን አባባል ዋጋ በመስጠት ለዚህ ጸሐፊ እስከ መደወል የደረሱ አሉ። ማስረጃ ከቀረበላቸው፤ አዩዘውዴ ራሳቸውን ማረም ፈቃደኛ መሆናቸውን ቢገልጹም፤ ከአስተማማኝ ምሑራንና ከታሪክ ድርሰቶች የቀረቡላቸውን ማስረጃዎች ባለመቀበል ተገቢውን እርምጃ አልወሰዱም። ሐሳባቸውን መግለጹ መብታቸው መሆኑ ቢታወቅም፤ መጽሐፉን የሚያነቡ አንዳንድ ሰዎች ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ደራሲው የእርምት መግለጫ እንዲያወጡ በተስፋ እየተጠበቁ ነው። ሌሎችም ቢጽፉ ይጠቅማል። የኢጣልያው ተወላጅ፤ አልቤርቶ ስባኪ፤ ቫቲካንን ሲያጋልጥ ከኢትዮጵያውያን የበለጠ አይጠበቅም?

የፖፕ ፓየስ 11ኛና የሙሶሊኒ/የፋሺሽቶች ሕብረት፤ የነዚህ ሁለት መሪዎች ሕብረት በኢትዮጵያ ላይ እጅግ አስቃቂ የሆነ መከራና አልቂት አስከትሏል፤

1ኛ/ በመርዝ ጋዝ፤ በቦምብ፤ በጥይት፤ በስቅላት፤ ወዘተ፤ አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈዋል። ከነዚሁ ውስጥ፤ በሶስት ቀኖች፤ አዲስ አበባ ብቻ 30 000 ሰዎች ተገድለዋል፤ እነአቡነ ጴጥሮስና ሌሎች ብዙ ጀግኖች ተሰውተዋል፤

2ኛ/ 2000 ቤተ ክርስቲያኖችና 525 000 ቤቶች እንዲሁም 14 ሚሊዮን እንስሶች ወድመዋል፤

3ኛ/ እጅግ ብዙ የኢትዮጵያ ንብረቶች ተዘርፈዋል፤ ለምሳሌ፤ ከ500 በላይ የሆኑ ሰነዶች በቫቲካን እጅ ይገኛሉ፤ "ፀሀይ" የተሰኘች የኢትዮጵያ አውሮፕላን በኢጣልያ አየር ኃይል ቤተ መዘክር ትገኛለች።

ከላይ የተዘረዘረው የጦር ወንጀል አልበቃ ብሎ፤ በቅርቡ ደግሞ፤ ባለፈው ነሐሴ 2004 ዓ/ም፤ አፈሌ በምትሰኝ የኢጣልያ ከተማ፤ "የኢትዮጵያ ጨፍጫፊ" በመባል ለሚታወቀው ለሮዶልፎ ግራዚያኒ፤ የቫቲካን ካሕን በተገኙበት፤ የመታሰቢያ ኃውልት ተቋቁሞለታል።

ስለ ፖፕ ፓየስ 11ኛና ፋሺሽቶች ሕብረት ብዙ ተጽፏል። ከዚህ ቀደም ከተጻፉት ውስጥ የሚከተለውን በመጠቆም መመልከት ይቻላል፡-

http://www.ethiolion.com/Pdf/10212012Evidence_of_pope_Pius_X.pdf

አንዳንድ ነጥቦችን ለማስታወስ፤

1ኛ/ አቬሮ ማንሒታን፤ "The Vatican in World Politics" በተሰኘ መጽሐፉ (ምእራፍ 9፤ ለማንበብ፤ www.globalallianceforethiopia.org ይመልከቱ)፤

(ሀ) እ.ኤ.አ ከ1922 በፊት፤ ቫቲካንና ፋሺሽቶች ተጻራሪዎች ነበሩ። ከዚያ ዓመት ጀምሮ ግን፤ ቫቲካንና ፋሺሽቶች (ፖፕ ፓየስ 11ኛና ሙሶሊኒ) መቀራረብና መወዳጀት ጀመሩ። በዚሁ መሠረት፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ፤ "የካቶሊክ ፓርቲ" የተሰኘውን የፖለቲካ ድርጅታቸውን ደመሰሱ።

(ለ) እ.ኤ.አ. በ1926 "Mussolini is the man sent by Providence" (ትርጉም፤ ሙሶሊኒ በፀጋ የተላከ ሰው ነው።) በማለት ፖፕ ፓየስ 11ኛ ሙሉ ድጋፋቸውን በይፋ በመግለጽ የኢጣልያን ሕዝብ የፋሺሽቱን ፓርቲ እንዲደግፍ አመቻቹ።

(ሐ) እ.ኤ.አ. በ1928፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛና ሙሶሊኒ Lateran "ላተራን" የተሰኘውን ውል ተዋዋሉ። ውሉ ሲፈረም የሚያሳየውን ፎቶግራፍ ከዚህ በታች መመልከት ይቻላል። ስለዚህ ውል በManchester Guardian (February 12, 1929) የሚከተለው ተነቦ ነበር፤

"Pope Pius XI is credited with much admiration for Mussolini. That the Italian clergy as a whole are pro-Fascist is easy to understand, seeing that Fascism is a nationalist, authoritarian, anti-liberal, and anti-Socialist force."

(ትርጉም፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ለሙሶሊኒ ስላላቸው ክፍተኛ አድናቆት ይነገርላቸዋል። የፋሺሽት ሥርዓት አምባገነናዊ፤ ብሔርተኛ፤ ፀረ-ዲሞክራሲና ፀረ-ሕዝባዊ ኃይል ስለ ሆነ የኢጣልያ ካሕናት በአጠቃላይ የፋሺሽት ደጋፊ መሆናቸውን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።

(መ) ቫቲካን ከላይ የተጠቀሰውን ውል በመፈረሟ፤ ከፋሺሽቶቹ መጠነ-ሰፊ ገንዘብ ያገኘች ሲሆን በተጨማሪም፤ ሕጋዊ ሉዓላዊነት ተፈቀደላት። አቬሮ ማንሒታን እንደ ጻፈው፤

"It was the alliance of these two men, Pius XI and Mussolini, that influenced so greatly the social and political pattern, not only of Italy, but also of the rest of Europe in the years between the two world wars."

(ትርጉም፤ የዘሀ የሁለት ሰዎች፤ የፖፕ ፓየስ 11ኛና የሙሶሊኒ ሕብረት ነበር በኢጣልያ ብቻ ሳይሆን በቀረው የአውሮፓ ክፍል ላይ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መሀል በነበሩት ዓመቶች የማሕበራዊና የፖለቲካ ይዘት ከፍተኛ አጽንኦት ያሳደረው።) በዚህ መሠረት፤ በሙሶሊኒ የተመራው የፋሺሽት ፓርቲ፤ በፖፕ ፓየስ 11ኛ ያልተቆጠበ ድጋፍ፤ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ለፈጸመችው የወረራና የጦር ወንጀል ምን ያህል እንደ ጠቀማት መገንዘብ አያዳግትም። አቬሮ ማንሒታን በተጨማሪ እንደ ገለጸው፤

"Thus the Church became the religious weapon of the Fascist State; while the Fascist State became the secular arm of the Church."

(ትርጉም፤ ስለዘህ፤ ቤተ ክርስቲያኗ (የካቶሊክ) የፋሺሽቱ መንግሥት ሃይማኖታዊ መሣሪያ ስትሆን፤ የፋሺሽቱ መንግሥት ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗ ዓለማዊ ክንድ ሆነ።)

(ሠ) ቫቲካን የፋሺሽቱን ጦር መባረኳ የሚይጠረጠር ሐቅ ነው። ካቶሊኩ ካሕን ጦሩን ሲባርኩ የሚያሳየውን ፎቶ ከዚህ በታች መመልከት ነው፤

(ለ) ሌላው ታዋቂ ምሑር፤ እርሳቸውም፤ በቅርቡ፤ "The Symphony of My Life" በተሰኘ አርእስት ስለ ሕይወታቸው ታሪክና ስለ ኢጣልያን ወረራ መጽሐፍ የደረሱት፤ ዶር. ሥዩም ጉበረ እግዚአብሔር፤ ከላይ የተጠቀሰውን በፖፕ ፓየስ የተገለጸውን የደስታ መልእክት ካረጋገጡ በኋላ፤ ከዚህ በታች የቀረበውን መልእክት ላኩልኝ፤

"From my book you can note, how one of the Catholic priests took the personal responsibility to entice me to be a priest! How we the seminarians marched outside Harar in a heavily Moslem country protected by Fascist military to attend church every week! Picture P 63 . This was a clear policy of the Catholic church in support of Fascism. The establishment of "Collegio Ethiopico" within the vatican compound was to train and indoctrinate Ethiopian seminarians. We were then told that if we become good potential priests, we will be eligible to go to Rome for further education (indoctrination"! There was a definite crusade to propagate Catholicism in Ethiopia with the help of fascism based on Apartheid policy I had faced on my way to priesthood!



የቫቲካኑ ካሕን የፋሺሽቱን ጦር ሲባርኩ



በፖፕ ፓየስ ዘኛ ስም ካርዲናል ጋስፓሪና ሙሶሊኒ "ላተራን" የተሰኘውን ውል እ.ኤ.አ. በ1929 ሲፈራረሙ

(ትርጉም፤ ከመጽሐፈ ማየት እንደምትችለው፤ አንድ የካቶሊክ ካሕን እኔን ወደ ቅስና ለመሳብ የግል ኃላፊነት ይዞ ነበር።

ገጽ 63 ላይ ባለው ፎቶግራፍ እንደሚታየው፤ ከሐረር ወጣ ባለ፤ እስላሞች በሚበዙበት (ክፍለ) ሐገር፤ ተማሪዎቹ፤ በፋሺሽት ወታደሮች እየታጀቡ፤ በየሳምንቱ ይሰለፉ ነበር። ይህም፤ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፤ ለፋሺሽዝም ያላትን ድጋፍ በግልጽ የሚያሳይ ፖሊሲ (መርሆ) ነበር። በቫቲካን ግቢ የተቋቋመው "ካሊጂዮ ኢትዮፒኮ" ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን ለማሠልጠንና ለማሳመን ነበር። በዚያን ጊዜ ተነግሮን የነበረው፤ ጥሩ የቅስና አዝማሚያ ካሳየን፤ ወደ ሮም ተልከን፤ ለቀጣይ ትምሕርት (ማሳመን) እጩ እንድንሆን ነበር። ወደ ቅስና በምጓዝበት፤ ባጋጠመኝ፤ በዚያ በዘረኛ (በ"አፓርቴይድ") መርሆ፤ በፋሺዝም እርዳታ፤ በኢትዮጵያ፤ የካቶሊክ እምነትን ለመስበክ ዘመቻ መካሔዱ የተረጋገጠ ነበር።)

ስለ "የዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ" ዓላማ፤ በእንግሊዝኛ Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause የተሰኘው ድርጅታችን ዓላማዎች፤

1ኛ/ ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤ 2ኛ/ የኢጣልያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተገቢ ካሣ እንዲከፍል፤

3ኛ/ የኢጣልያ መንግሥትና ቫቲካን የተዘረፉትን የኢትዮጵያ ንብረቶች እንዲመልሱ፤

4ኛ/ ለጦር ወንጀለኛው ለግራዚያኒ የተቋቋመው መታሰቢያ እንዲወገድና፤


5ኛ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመውን የፋሺሽቶች የጦር ወንጀል በመዝገቡ እንዲያውል ነው።

ጉዳዩ የሐገር መብትንና ክብርን የሚመለከት ስለ ሆነ ዓለም-አቀፋዊ ድጋፍ እያገኘ ነው። ለምሳሌ፤ ድረ-ገጻችን፤ www.globalallianceforethiopia.org ላይ ያለው አቤቱታ እስካሁን ድረስ ከ30 ሐገሮች በላይ በሚኖሩ 4818 ሰዎች ተፈርሟል። ይህንን ጽሑፍ የሚያነቡ፤ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች ቢፈርሙት መልካም ነው።

ቸሩ የኢትዮጵያ አምላክ፤ የውድ ሐገራችንን መብትና ክብር ለመጠበቅ ያብቃን።

የዚህን ጽሑፍ ረቂቅ ተመልከተው እጅግ ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶቻቸውን ላበረከቱልኝ ለልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ፤ ለአምባሳደር ዓለማየሁ አበበና ለዶር. ሚካኤል ወሰን ጥልቅ ምሥጋናዬን እገልጻለሁ።









መነባበብ የሚገባው

መፅሐፈ ቤን

አይቼው በቃና

ምዕራፍ አንድ
አውደ ውሻ

ውሻ የነተኩላ ዘር ማንዘር፣ የነቀበሮ ቤተሰብ ነው። ታዲያ ቤተሰቦቹን ትቶ እንዴት ከተማ ከተመ?

የዛሬ 10000 ዓመት ገደማ ውሻ ሰውን የለመደው፣ ሰው ያቆሰለውን አውሬ ማግኘት ደከሞት ትቶት ሲሄድ ውሻ ያንን የወደቀ መልቀም ጀመረ። በተለይ ሰው በዋሻ መኖር ሲጀምር ስጋውን የበላለትን አጥንት ሲወረውርለት ነገሩ ለውሻ እየቀለለለት መጣ። ሰው ያቆሰለውን ከመፈለግ፣ የሚወረወርለትን አጥንት የመጠበቅ ትዕግስትን ተላበሰ። ሰው ያቀጣጠለውን እሳት መሞቁና ሌሎች ለሎሌነቱ ለሚከፈለው ድርጎ ሲል መጠጋቱን አውደ ውሻ ይናገራል።

ዛሬም ድረስ ውሻ ሆዱን እስከቻሉትና መጠጊያ እስከሰጡት ድረስ ከሰው ስር አለመጥፋቱ የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ ብሎ ይመስለኛል። ውሻ እንሆንም ያሉት እነ ቀበሮና ተኩላ ግን ለሆዳችን አናድርም ሰርተን እንበላለን ብለው ወሰኑ። ውሻ ግን በአጥንት ተገዝቶ ወገኖቹን ከዳ። ለዚህም ነው መሰል "...ዉሻ በበላበት...." እየተባለ የሚተረተው። ውሻ አሳዳሪው መጥፎ ሆነ ጥሩ ለሱ አጥንት እስከጣለለት ድረስ ይጮህለታል። የዉሻን ባሕሪ ሁሉ ብዘረዝር አንዳንዶች ታሪኩ ከቤንጋ ሊመሳሰልባቸው ይችላልና ልተወው።

አውደ ውሻን ያላነበቡ አንዳንዶች ቤን ወያኔ ነው፣ ቤን ጋዜጠኛ ነው ይሉ ይሆናል። እኔ ደሞ እረ ሁለቱንም አይደለም እላለሁ።

ቢንያም ከበደ በየነ ለምን እንደተወለደ አላቅም፣ አስተዳደጉንም እንዲያው፣ ግን በኬሚስትሪ ተመርቆ፣ በፋርማሲ ቅመማ ይሰራ እንደነበረ አውቃለሁ። "እንዴት ወደ ጋዜጠኝነት ገባህ?" ብዬ አልጠየቅኩትም ምክንያቱም ጋዜጠኛ ነው ብዬ አስቤ አላቅም። ምናልባት አወቅኩሽ ናኩሽ ይሆናል። እኔ መፃፍ እወዳለሁ እንጂ ደራሲ ነኝ ብዬ አላስብም። ወይ ጉድ ቤን ግን ጋዜጠኛ ነኝ ብሎ ያስባል። ታድሎ!! ልጅ እያለሁ የተመድ ፕሬዜዳንት ነኝ ብዬ አስብ እንደነበረው ማለት ነው። አንዳንድ ሰው ግን አደጉም አያረጅም መታደል ነው።

ቤን ከፈላደልፊያ ቤቱም እንዴት ወደ አዲሳባ እንደቀየረ ፈጣሪ ነው የሚያውቀው። ከዓመት በፊት ግን በቶሮንቶ አውሮፕላን ማረፊያ ቤን ከተፍ አለ። ዘመድ ወዳጆቹ መቀበያ ጋ ሲጠብቁት ብቻውን አልመጣም ከኃላው አንዲት ወረገብ ልጅ እግር ብቅ አለች።

የልጅቷን እርጉዝ መሆን ያየ ቤን የልጅ ልጅ ሊያይ ነው ያሉ አሉ። ቤን ለአባትነት እንዳልበቃ አውቃለሁና። አያት እንደማይሆን እርግጠኛ ነበርኩ። ቤኒሻ ከኔ የኮረጃት ነገር ቢኖር እሽት መውደዱ ነው። ሰው ሁሉ እንዴት እኩያውን አያገባም ሲሉ፣ እኔ በዚህ አልወቀስኩትም። እኔም እሽት ስሸመጥጥ ቤን አጠገቤ ሆኖ አይቶ ነው።

ቤን አዲሳባ እንደደረሰ " ... እኛ እንዘግባለን እናንተ ፍርድ ስጡ።" የሚል ፕሮግራም ጀምሮ ነበር። ዛሬ ግን ይኼ ድረ ገፁ መግቢያ ላይ የቀረ የግድግዳ ጥቅስ ሆኗል። አሁን ግን እነሱ ይዘግቡለታል እሱ ፍርድ ይሰጣል። እኛ አርፋችሁ ቁጭ በሉ ተብለናል።

አሰረጅ ቁጥር አንድ ፡ -መንግሥት በፕሬስ ላይ አዲስ ሕግ ሲያወጣ እልል ብሎ ያጨበጨበው ቤን ነው። እዚህጋ ሕጉ ልክ ነው ወይንስ አይደለም ሳይሆን ቤን "ጋዜጠኛ" ነኝ ብሎ ያስባልና ከፕሬስ ነጋ ሊቆም ሲገባው፣ እሱ ዘግቦ ራሱ መፍረድ የጀመረው ያኔ ነው።

ቤን በድረ ገፁ "ደሴ በሽብርተኞች ላይ በቁጣ ተነሳ" ብሎ ያወጣቸው



አይንህ ያረፈባት ወይንስ የተቆጣች ቆንጆ?



ቤን ለቀስተኞች ቀብር ላይ እያለቀሱ ነው አይደል?


እኔ ቤንን የታዘብኩት በልጅቷ ሳይሆን ልጅቷ በሆዷ በያዘችው ልጅ ነው። ከዓመታት በፊት ቤን አበበ በለውን ለማሳጣት ሲል "ኢትዮጵያ የሚኮሩባት ሀገር ናት" እያለ ሲሰብከን የነበረው፣ የሱ ልጅ ኢትዮጲያዊ እንዳይሆን ካናዳ ሊያስወልደው መጣ። ከሁለት ዓመት በፊት የሚኮራባት ኢትዮጵያ፣ እነ አበበ በለው የተሰደቡባት ኢትዮጵያ፤ ዛሬ ምን መጣና በሕይወት እስካለሁ ልጄ ኢትዮጵያ አይወለድም ለማለት ደረሰ? በሁለት ቢላ ሊበላ?!!!!

አሰረጅ ሁለት፡- የአረጋዊ በርሔን እና የኪራይ ቤቶችን ውዝግብ፣ አሸቃበጠበት ስንት ኢትዮጵያዊ በቤት ጉዳይ እየተጉላላ። አረጋዊን ጠልፎ ለመጣል ዝርጠጣው ላይ መተባበሩ ነው።

አሰረጅ ሶስት፡- የደሴው ሼህ ተገደሉ አለና የገደሏቸው የድምፃችን ይሰማ አባላት መሆናቸውን የነገረን እሱ ነው። እንዴት እዛ ድምዳሜላይ እንደደረሰ የነገረን ነገር የለም። ብቻ የሁለት ሙስሊሞች ፎቶግራፍ አስቀምጦ ታሪኩን ከጀሐዳዊ ሐረካት ጋር አቀናብሮ ብይን ሰጥቶ ቁጭ አለ።

ይሄ እንኳን አዳኝ የማይገባበት ጥሻ ውስጥ ውሻውን እንደሚልከው አይነት ነው።

በሳምንቱ "ሼሁን የገደለው ቤን ራሱ ነው።" የሚል ቡድን ተነሳ። ቡድኑ ማስረጃ ያደረገው፣ ወንጀሉ ሲፈፀም የከተማው መብራት በጠቅላላ መጥፋቱን ቤን ደብቋል፤ ሚሊዮን ሕዝብ፣ ሕፃናትንኳ በጥይት አረር በሚወድቁባት ሀገር ከአዲስ አበባ ደሴ ለቅሶ ለመድረስ ምን አስኬደው? ቃለመጠይቅ አደረግኩ የሚለው የሚችን ቤተሰቦችና የመንግሥት አካላትን፣ ደሴ በቁጣ ተነሳች ብሉ ሥዕላዊ ዜና ያቀረበው ላይ የቤተሰብ የቀበር ስነ ስርዓትንና ቤን በመንገድ ስትሔድ የወደዳት ባለሂጃብ ሙስሊም፣ በቀበሌ እንዲወጡ የታዘዙ ሰልፈኞች ቀበሌ 07 የሚል ባነር እንደያዙ፣ .... ግን ደሞ እሱ ሼሁን ማን እንደገደላቸው ፈርዷልና እኛ እንደታዘዝነው አርፈን ቁጭ ነው።



ቀበሌ 07 ታዘው ነው የወጡት? ደሴ ሲቆጣ የከት ልብሱን ለብሶ ነው እውነትም ትንሹ ልጅ በጣም ተቆጥቷል።

በኢትዮጵያና በኤርትራ ጦርነት ሳቢያ የተከፈተው "ኢትዮጵያ ፈርስት" ወይንም "ኢትዮጵያ ትቅደም" ስም ይዘ መለመኛ አቁማዳው አደረገው አልኩ፣ አውደ ውሻን ያነበቡ ደግሞ መቻል ቦቢ፣ ችሎ እንጂ እንዴት ኢትዮጵያ ትቅደም የሚባል ስም ይወስዳል? አሉ። ይሄ ነገር የባላምበራስ ምትኩን ገድል አስታወሰኝ፡


የአልታዬ አባት፣ ባራምበራስ ምትኩ፣ የአቶ ቅጣውን ውሻ ገለሀል ተበለው የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ቀረቡ። አልካዱም፣ የቅዱስ ዮሐንስ በሬ ከታረደው ቅርጫ ሳምባ ወስጄ ፣ የተቃጠለ አምቡል ሰባብሬ ከሳምባውጋ ቀላቅዬ ለቅጣው ውሻ ሰጠሁት አሉና በራሳቸው ላይ መሰከሩ። " ነገሩ ሲጣራ አቶ ቅጣው ለውሻቸው ሚኒሊክ የሚል ስም ስላወጡ ባላምበራስ ሆዬ እንዴት ውሻ በአምዬ ምኒሊክ ስም ይጠራል? ብለው በሽምቅ ውጊያ ውሻውን ገለው በዳኞቹ ፊት ሲያቅራሩ አብዲሳ አጋን ይመስሉ ነበር።

ይህ መፅሐፍ በቤን "ጓደኛ" የተፃፈ ነው። ምናልባት ይህን መፅሐፍ አንብበው ሲጨርሱ እንዴት ጓደኛው ሆነህ ትሰድበዋለህ? ይሉ ይሆናል። እንደኔ እንደኔ፣ አህያን አህያ ማለት ስድብ አይደለም። "እርግጥ"ነው አህያዋን ቤን ብያት ቢሆን ኖሮ ተሰደብኩ ብላ ሊያናድዳት ይችል ይሆናል። ለቤን ግን ስድብ አይደለም።

ሆኖም ስንት ጠላት እያለው አንተ ለምን ከወዳጅህ ትቃቃራለህ? የሚል ሰው አይጠፋም፤ ነገሩ ግን እንዲህ ነው። ቤን አጠፋ፣ አለቅጥ አበዛው። ይህንን ያልኩት እኔ ነኝ፤ እኔ ብቻ አይደለሁም፤ ወዳጆቹም ጠላቶቹም ሁሉ ያም ያም ይሉም "ልክ አይደለም" አሉ፣ አልን። እና ማን ተው ይበለው? ሲባል፣ ሞትም በዕጣ ቢሆን ለኔ ነውና ቀድሞ የወጣ እኔ ላይ ወጣ። "ሽረ ተዉ እኔ ላይ ነገር ይመርብኛል ብል አጣፍጠህ ጣፈው አሉ። በዘራችን እድሜ ረጅም የለምና አንተ ዕድሜህ አጭር ነው ይህንኳ ሰርተህ ሙት ብለውኝ በቃ ሰማዕት ልሁን ብዬ የባራምባራስ ምትኩን ፈለግ ለመከተል ብዕሬን ሰበቅሁ።

ወይንም በቤን አባባል "እኔ ዘገብኩ እሱ ይፍረድ"

በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የታላቁ ኢትዮጵያ የሙዚቃ አባት የተስፋዬ ለማ መጽሐፍ ለንባብ ቀረበ



መጽሐፉ በውስጡ ያካተታቸው፡-

- የኢትዮጵያ የባሕል የሙዚቃ መሣሪያዎች አፈጣጠር፣
- የኢትዮጵያ ሙዚቃ መሠረታዊ አመጣጥ
- ትውልድ ሊወርሰው የሚገባ የኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ፣
- በየዘመኑ የተፈጠሩ የኢትዮጵያ የሙዚቃ ባለሙያዎች እና ያበረከቷቸው ሥራዎች

- ይኽ መጽሐፍ ጋሽ ተስፋዬ ለማ ዕድሜውን ሙሉ የደከመበት እና እስካሁን በሃገራችን የሙዚቃ ታሪክ ያልተነገሩትን ይዳስሳል።
- ይኽን መጽሐፍ የተሟላ ለማድረግ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ የተሳተፉትን ሁሉ ውለታቸውን ሳይዘነጋ፣ ተግባራቸውን እና የፎቶግራፍ ምስላቸውን ያካተተ ነው።
- መጽሐፉ ከንባብ ባሻገር ለሃገራችን የወደፊት የሙዚቃ ታሪክ መነሻ መሠረት እና ዋቢ በመሆን በመዘክርነት የሚቀመጥ ሃብት ነው።

አሳታሚ ናፍቆት ኢትዮጵያ

ዲ.ሲ እና አካባቢዋ፡- ማርክ ኮምፒውተር እና ታክስ

Tel: 703-256-9113, 202-253-4414, 773-746-9513

ወይም በድረ-ገፃችን www.nafqotethiopia.com ላይ በቀጥታ መግዛት ትችላላችሁ።



በታሪክ፣ በሃገር ጉዳይ፣ በሥነ-ልቡና፣ በመዝናኛ፣ በማኅበራዊ እና
በአጠቃላይ እውቀት ላይ የምታተኩር ወርሃዊ መጽሔት

መስከረም / ጥቅምት ፪ሺ፮ ዓ.ም ፯ኛ ዓመት ቁጥር ፷
September / October, 2013 7th Year No. 60

Editor in Chief **Girma Zegeye**
ሞና አዘጋጅ **ግርማ ዘገየ**

Associates:- Mekuria Negia
Kassahun Maru

አምደኞች:- ክንፈ ገበየሁ ዶ/ር
ዳንኤል ክብረት ዲ/ን
ሠላዩ
አፈቱሌ
አናንያ
አርቲስት ማርታ ቀፀላ
ኑረዲን ኢሣ
የዙሪያው ልሣን
መኩሪያ ነጊያ
ጎሊና በለጠ

ጽሑፍ አስተዋፅኦ:- አስፋው ዘ. አልጌና
ቤተ ሙሴ
ብሩክ ከበደ /ብሬመን ጀርመን/
ኪዳኔ ዓለማየሁ

ተባባሪ ሪፖርተር:- ፍቃዱ ማኅተመወርቅ አ/አ (ዕንቁ)

Cover Design Ezana Film and Music

Contact Information:-

Nafqot Ethiopia Magazine
P.O. Box 409214
Chicago, IL 60640

Email: girmazegeye@yahoo.com
editor.nafqotethiopia@yahoo.com

Visit our Website @ www.nafqotethiopia.com

773-746-9513, 773-253-5110

D.M.V area:- 703 - 256 - 9113
202 - 253 - 4414
703 - 628 - 5716

"አራሙቻ"

አርቲስት ማርታ ቀፀላ / ዲ.ሲ./

ዓይን ያለው ማየቱ...ጆሮ ያለው መስማቱ፣
የታወቀ ቢሆንም...
ትዝብቱን ወደኋላ በመተው፣
...ግዴታዬን ልንገረው
ወግ እና ባህል ያለገደብ ሲንሸራተት
ያለ አግባብ ሲሆን ማየት፣
ቋንቋው ከሌላው ተዳቅሎ ...
...ከነበረበት አጋድሎ፣
ቦታውን ሲለቅ! «ዋው! ዋው!» ሲሆን አባባሉ
...የማድነቂያው ኃይለ-ቃሉ፣
«ግሩም ነው» መባባል ሲቀር...
...በተውሶ ቃል ሲቀየር፣
እያለን እንደሌለን...ብንናገር የሚያሳፍረን...
...ሳንቸገር ሳያንሰን፣
ምነው? ምነው?...እራሳችንን መገመት ተሳነን!
ባዕድ ቃላት እንደ ቅመም...
...እንደ አራሙቻ ሲረባረብ፣
"Father, Mother" ሆኖ መጠሪያው፣
መች ይኸ ብቻ...ሌላም ሌላም፣
....ሁሉን መዘርዘር ባያሻም፣
«እናቴ፣ አባቴ» ያልንበት. ..
...በፍቅር የጠራንበት፣
ያ! የጥንቱ የጠዋቱ የት ደረሰ...
...መሠረቱ ተከላለሰ፣
እናት አባትስ ምን ይሰማቸው?
ባለመዱት ቃል ሲጠሯቸው፣
'Yes" ይበሉ ወይስ አቤት?
...ጉራማይሌ ሲገባበት፣
ማንነት ተዘንግቶ...በሌላ ዓለም ውስጥ ገቡቶ፣
ወለምታው እየገፋ...ስብራቱ እየነላ፣
ወጌሻ ከመፊለግ...እራሳችንን እንወቅ፣
መኖር ካለብን እንዳገሩ...ሥነ-ቃሉን መናገሩ፣
ቢሰባበርም ሳይፈሩ፡
ለመግባባት ይበጃል...ተገቢም ነው ያስኬዳል፣
አንዳንዴም ቃላት የማይገኝለት..
...ሳይንሳዊ ይዘት፣ መተኪያ የሌለው
ያለው አማራጭ እንደሰጡን መጠቀም ነው፣
ካልሆነ ግን ...ውሃ ሲወስድ አሳስቆ፣
እንዳንሰምጥም ተጠንቅቆ ነውና፣
ሥር ሰዶ ባሕል ሳያፈነግጥ...
ለነገው ትውልድ ማቆየቱ፣
ያለብንን ኃላፊነት መወጣቱ...
...ቅይጥይጡን ማጥፋቱ
ከወቀሳ ያድናል እላለሁ...
...ጎሊናችን እንደሚያርፍም አምናለሁ።





ከዲ/ን ዳንኤል ክብረት

"ጴላጦስ"

ከዱባይ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ላይ ነኝ። ሻርጂያ በተባለው ከተማ አንድ ኢትዮጵያዊ የጠየቀኝን ጥያቄ አወጣለሁ፣ አወርዳለሁ። በወቅቱ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ዘንድ፣ *'ሰሙነ ሕማማት'* የሚባለው ነው። የአስራ አምስቱ ስቅለት ሚያዚያ 17 ቀን፣ ከሁለት ቀናት በኋላ ደግሞ የትንሣዔ በዓል ይከበራል።

ያ ኢትዮጵያዊ ወዳጄ፣ *«መስፍን ጲላጦስ ክርስቶስን ለምን አሳልፎ ሰጠው?»* የሚል ጥያቄ ነበር ያነሳልኝ። ለጊዜው ይሆናል ያልኩትን ማብራሪያ ሰጠሁት። በኋላ ግን እኔው ራሴ በነገሩ ማንሰላሰሌን ቀጠልኩ።

ጴንጤናዊው ጲላጦስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ጊዜ *(በ34 ዓ.ም.)* በኢየሩሳሌም የሮምን ንጉሥ በመወከል የይሁዳ መሥፍን ነበር፣ ክርስቶስ በፊቱ ተከስሶ የቀረበውም ከዚህ ሥልጣኑ የተነሳ ነበር። በዘመኑ ይደረግ እንደነበረው ተከሳሹን አስቀርቦ ጠየቀ፣ እርሱን ያስረዳሉ የተባሉ የከሳሽ ምስክሮችንም ጠየቀ፣ ነገር ግን እየሱስ ክርስቶስን *«ወንጀለኛ»* ሊያሰኝ የሚችል ምንም ነገር አጣ፣ ሚስቱም በሕልሟ ያየችውን ሥቃይ በመግለፅ ርቱዕ ፍርድ እንዲሰጥ አሳሰበችው።

እነዚህ ሁሉ ተደማምረው መስፍን ጲላጦስ ክርስቶስን፣ *«ለምት የሚያበቃው ቀርቶ የሚያሳስረው ጥፋት አላገኘሁበትም»* ሲል ደመደመ። አይሁድ ይኽን ሲሰሙ *«ይኽን ካደረግህ የቄሣር ወዳጅ አይደለኽም!»* የሚል ፖለቲካዊ ተቃውሞ በከረረ ሁኔታ መሰንዘር ጀመሩ። ጲላጦስ ነገሩን ለማብረድ በማሰብ፣ *«ኢየሱስ ክርስቶስን ዝፈ ልስቀለላቸሁ፣»* የሚል አማራጭ ሃሳብ አቀረበ። ከሳሾቹ አይሁድ ግን፣ *«ሞቶ ካለነው አንተ የቄሣር ወዳጅ አይደለኽም፣»* ብለው ነገሩን አጠነከሩት። በመጨረሻም መስፍኑ ጲላጦስ ተሸነፈ እና ይሙት በቃ ፈረደ።

የተከሰሰው እና በፍርድ አደባባይ የቆመው ክርስቶስ ምንም ጥፋት እንዳላጠፋ ዳኛው አውቋል። ማወቅ ብቻም ሳይሆን በአንደበቱ መስክሯል፣ ሕጉም ንጹሕ የሆነ ሰው ከተከሰሰበት ነገር ነፃ እንዲሆን እና እንዲሰናበት ያዝዛል። ታዲያ ጲላጦስ ይሕን ሁሉ እያወቀ ለምን የተዛባ ፍርድ ፈረደ።

አንድ ነገር ማወቅ፣ በጉዳዩም ማመን እና ላመኑበትም እውነት እስከ መጨረሻው በጽንዐት መቆም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ጲላጦስ የዕውቀት ችግር አልነበረበትም። በዘመኑ በነበረው የፍርድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት መሠረት የከሳሾቹን ምስክሮችም ሆነ ተከሳሹን በፊቱ አቁሞ ጠይቋል። በዚህም ክርስቶስ ምንም ወንጀል የሌለበት መሆኑን አውቋል። ነፃ መሆን እንዳለበትም አምኗል። ይኽ ዕውቀቱን እና እምነቱን በተግባር እንዳያውል ግን አንድ ነገር ከለከለው - የሚያጣው ጥቅም።

ክርስቶስ የተከሰሰበት አንዱ ወንጀል፣ *«ራሱን ከቄሣር ጋር በማስተካከል ንጉሥ ነኝ ይላል፣»* የሚለው ነው። በመሆኑም ክርስቶስን ነፃ ቢለቀው *«ከቄሣር ሌላ ንጉሥ አለ ብሎ ያምናል»* ተብሎ ሊወነጀል፣ በኋላም ሥልጣኑን ሊያጣ ሆነ። ጲላጦስ እውነትን ተቀብሎ፣ ለእውነት መስዋዕትነትን ከፍሎ ሥልጣኑን ከሚያጣ እውነትን ሰውቶ በሥልጣን መቆየት መረጠ። ያመነው ነገር፣ የተናገረው ነገር እና የፈረደው ፍርድ ተለያየ።

አንዳንድ ሰዎች የሚናገሩት፣ የሚያምኑበት፣ በየመድረኩ የሚደሰኩሩት፣ አጠናን ብለው የሚተነትኑት፣ ከልብ ጓደኞቻቸው ጋር ሲያወጉ የሚዘገዝቱት፣ *«ቢሆን መልካም ነው»* የሚሉት እና በቦታው ላይ ሆነው የሚፈጽሙት የሚለያየው ለእውነት መቆም የሚያስከፍለው ዋጋ ስላለ ነው።

አንድ ዳኛ የሚተቸው፣ የሚተነትነው፣ በኅሊናው የሚያምንበት እና በልቡ የሚያመላልሰው ከሚሰጠው ፍርድ ጋር ከተጋጨ፣ አንድ ባለ ሥልጣን እውነት ነው ብሎ የተቀበለው እና ትክክል ነው ብሎ የወሰነው ከተለያየ፣ አንድ ባለሞያ የጥናቱ ውጤት እና እርሱ ለአለቃው ያቀረበው ውጤት በእጅጉ ከተቃረነ ወይም ከተለያየ እንዳያጡት የሚፈሩት ጥቅም አለ ማለት ነው።

በስብሰባ ተቀምጠው አለቆቻቸውን ወይም የሚመጣውን መከራ ፈርተው አንዳች ነገር የሚወስኑ፣ ነገር ግን በልቡናቸው የተቀበሉት እውነት ከወሰኑት ጋራ የሚጋጭባቸው ሰዎች ይኽን በሽታ የሚያስታግሱት፣ *«ምን ይደረግ ብለህ ነው፣ በግድ ሳናምንበት፣ አስፈራርተው፣ ሃሳባቸንን ሳይቀበሉ ቀርተው የማይሆን ነገር ወሰኑ»* እያሉ ለሚቀርባቸው ሰው በማውራት ነው የውስጡን ግጭት በወሬ ነው የሚያስተነፍሱት።

ከወዳጆቻቸው ጋራ ሲቀመጡ የተቹትን፣ የነቀፉትን እና የተቃወሙትን ነገር በቦታው ሲሆኑ ግን *«የጠሉት ይወርሳል፣ የፈሩት ይደርሳል»* የተባለው ደርሶባቸው እነርሱ የባሱ ሆነው ይገኛሉ። አንዳንድ ጊዜ በሚያምኑበት ነገር እና በሚሰጡት መግለጫ መካከል ቅራኔ ሲያጋጥማቸው በረዥም ዓረፍተነገሮች፣ *«ኧ...ኦ...ኧ..»* በሚል የሚያታክት የነገር ጉተታ ወይም ደግሞ *«አበረታች ነው፣ አስደናቂ ነው፣ ልዩ ነው፣ ብሩህ ነው»* በሚሉ የማይለኩ ነገሮች ሊያስታግሱት ይሞክራሉ።

ሁለት እና ሁለት ሲደመር አራት መሆኑን እያወቁ፣ ጠረጴዛቸው ላይ በሚገኘው ወረቀት ይኽንኑ እየሞነጫጨሩ፣ ድምሩ ከስሌቱ ውጪ፣ *«አምስት ነው»* ብለው ለማሳመን ሲሉ የማርስን እና የጁፒተርን ልምድ የሚጠቅሱት ኅሊናቸው እና ንግግራቸው ሲጋጭባቸው ነው።

«የእንጀራ ጉዳይ ነው፣ ልጆቼን ላሳድግ ብዬ ነው፣ ከለው ጋር ሲኖሩ ምኝ ሆኖ አህያን ሲጭኑ ሦስት ሆኖ ሰለሚባል ነው፣ ከፉ ቀንን እና ቅዝምዝምን ጎንበስ ብሎ ማሳለፍ ሰለሚገባ ነው፣ ብቻዬን ለውጥ ላመጣ ሰለማልችል ነው፣...» የሚባሉት ማብራሪያዎች ሁሉ ከነመሰሎቻቸው የዚህ ጲላጦሳዊ ችግር መገለጫዎች ናቸው።

ሰው በመኖር ብቻ ሳይሆን በመሞትም ያሸንፋል። ሰዎችን ከእንስሳት የሚለዩአቸው ነገሮች አንዱ ሰዎች በሞት ሊገታ የማይችል አሸናፊነት ሊኖራቸው ስለሚችል ነው። እነ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ እነ ማኅተመ ጋንዲ፣ እነ በላይ ዘለቀ ተገድለዋል፣ ነገር ግን አሸንፈዋል። እነዚህ ሰዎች ለሰማዕትነት እንዲበቁ ያደረጋቸው የሚሠሩት ሥራ ከሚያምኑበት ጋራ እንዲቃረን ባለመፍቀዳቸው ነው።

የተማረው እና የሚያምንበት ሌላ ሆኖ ጥቅም ብቻ በሚያስገኘለት ክሊኒክ የሚሰራ፣ ጥቅም ብቻ ባለበት ትምህርት ቤት የሚያስተምር፣ የግል ጥቅም ብቻ ባለበት የቢዝነስ እና ፋይናንስ ሥራ ላይ የተሠማራ፣ ጥቅም ብቻ በሚገኝበት የጋዜጠኝነት መስክ የሚኳትን ስንቱ ነው!!! ውሎ አበል፣ የተሻለ ክፍያ፣ የውጭ ዕድል፣ ሥልጣን፣ የወንበር አበል፣ መኪና፣ የሪሴፕሽን ግብዣ፣ ያማረ ቢሮ እና የተደላደለ ቤት ይቀርብኛል ብሎ የማያምንበትን የሚሠራው ስንቱ ነው?

ጲላጦስ ውሳኔውን ወስኖ ክርስቶስ ከተሰቀለ በኋላ በሠራው ሥራ መፀፀት ጀመረ። የውስጡ እምነት እየገፋ፣ ኅሊናውንም ዕረፍት እየነሳው መጣ። ያ ሠዓት ግን ምንም ሊያደርግ የማይችልበት ሰዓት ነበር። የእርሱ ፍርድ ተፈፃሚ ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሏል። በታሪክ እንደሚነገረው ጲላጦስ እስከ ዕድሜው ፍፃሜ በሠራው ሥራ እንደተፀፀተ፣ ኅሊናውም ሠላም ላያገኝ ነው የኖረው።

ነገር ካለቀ በኋላ ከመፀፀት እና የኅሊና ሰላም ከማጣት ከሚያምኑት እውነት ጋራ መቆም እጅግ የተመረጠ ነው። ጦርነቱ ሲያበቃ፣ ፖለቲካው ሲቀየር፣ አስቸጋሪው ዘመን ሲያልፍ፣ ችግሩ ጊዜ ሲጠናቀቅ፣ *«እንዲህ ብዬ ነበር፣ እንዲህ ማድረግ አልነበረብኝም፣ ይሽን ያደረግሁት ተገድጄ ነው፣ ተፅዕኖ ነበረብኝ፣ ለታሪክ ምስክርነት ለመትረፍ ብዬ ነው፣ በሠራሁት ሥራ አዝናለሁ፣ ተሰምቶኛል፣...ወዘተ»* ማለት ለችግሩ መፍትሔ አይሆንም።

የሞተው አይነሳም፣ የደኸየው ሃብት አያገኝም፣ የተነጠቀው አይመለስም፣ ትዳሩን የፈታው አያገባም፣ ያለቀ ዕድሜ አይተካም፣ ያመለጠ ዕድል አይገኝም። እናም ውስጣዊ ሠላም ይጠፋል፣ ጸጸት እንደ እግር አሳት ይበላል።

በስታዲየሙ ዙሪያ ተሰብስቦ መተቸት፣ ሐሳብ መስጠት፣ *«ለምን አልገባም»* ብሎ መውቀስ፣ ኅል ሲገባም መጨፈር፣ አሠልጣኝ እና ተጨዋችን መሳደብ እጅግ በጣም ቀላል ነው። ከአስራአንዱ ተጫዋቾች አንዱ ሆኖ ውጤት የሚያመጣ ጨዋታ መጨወት ግን ከባድ ነው።

የጨዋታ ጊዜው ሲጠናቀቅ፣ *«ይሽ ቢደረግ ለንዲህ ይሆን ነበር፣ ያ ለንዲህ ባያደርግ ግቡ ይቆጠር ነበር፣ ለገሌ ይሽን ሊሰራ ሊይገባም ነበር።»* እየተባለ ይተነተናል። እንዲህ ያለው ነገር ለወደፊቱ ጠቃሚ ልምድ ይገኝበት ይሆናል። ያን ጨዋታ ግን አይቀይረውም። የገባው ጉበቷል፣ የተሳተውም ተስቷልና።

እናም ነገር ካለቀ በኋላ እንዲህ የሆነው እንዲህ ስላልሆነ ነው ከማለት በወቅቱ ማድረግ ያለብንን ነገር መፈፀም ነው ቁምነገሩ። *«ለገራችን በባዕድ መያዝ የለባትም!»* ብለው ያመኑበትን እምነት በተግባር ለመግለጥ በዐድዋ ዘመቻ መሥዋዕትነት የከፈሉት ጀግኖቻችን ኢትዮጵያን በነፃነት ለማቆየት ችለዋል፣ ነገር ግን፣ *«ከጣሊያን የምናገኘው ጥቅም ይበልጥብናል፣»* ብለው ባይዘምቱ ኖሮ ታሪክ በተቀየረ ነበር። ታዲያ ዛሬ እነዚያ ዘማቾች ያልዘመቱበትን ምክንያት ቢያስረዱን እንኳን የዐድዋን ድል ሊተካው አይችልም። በከፉ ቀን በጦርነት ሜዳ የተወለዱት ጀግኖች አባቶቻችን ግን መስዋዕት ሆነው በሞታቸው ወራሪን አሸንፉ።

« . . . ሰው በመኖር ብቻ ሳይሆን በመሞትም ያሸንፋል። ሰዎችን ከእንስሳት የሚለዩአቸው ነገሮች አንዱ ሰዎች በሞት ሊገታ የማይችል አሸናፊነት ሊኖራቸው ስለሚችል ነው። እነ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ እነ ማኅተመ ጋንዲ፣ እነ በላይ ዘለቀ ተገድለዋል፣ ነገር ግን አሸንፈዋል። እነዚህ ሰዎች ለሰማዕትነት እንዲበቁ ያደረጋቸው የሚሠሩት ሥራ ከሚያምኑበት ጋራ እንዲቃረን ባለመፍቀዳቸው ነው። . . . »

ከስብሰባ ሲመጡ፣ ነገር ሲያልቅ፣ ጨዋታው ሲያበቃ፣ መከራው ገሸሽ ሲል ሺሕ ጊዜ ከማውራት፣ *«ጀግና የሚወለደው በጦር ሜዳ ነው፣»* ብሎ እዚያው ላይ ላመኑበት መሟገት ነው ሞያ ማለት።

ስለ ለሊት ወፍ *«አፈጣጠር»* የሰማኩትን እዚህ ላይ ባነሳው መልካም ነው። በጥንት ጊዜ የለሊት ወፍ የሚባል ነገር አልነበረም አሉ። አንድ ጊዜ ግን ወፎች ተሰብስበው የሚወዳድቀውን ጥራጥሬ አይጦች እየበሉ ጠማቾችን ስላሳደሩን አይጦችን የሚከታተል፣ መልኩ አይጥ የሚመስል የወፍ ዘበኛ እንቅጠር ብለው ማስታወቂያ አወጡ። በዚህ ጊዜ ጉድጓድ ውስጥ መኖር የመረራት አይጥ ከንፍ አሰፍታ፣ *«ወፍ ነኝ»* ብላ ቀረበች። ምንም እንኳን ዘመዶቿ፣ *«አይጦች ጥራጥሬ መብላት የለባቸውም፣»* የሚሉትን ብትቃወምም ለመኖር ስትል ግን ለዘበኝነቱ ተሰማማች፣ ጥርሷን አይተው እንዳያባርሯትም በድንጋይ ሰብራ አረገፈችው። ለብዙ ዘመን በዘበኝነቱ ፀንታ የገዘ ዘመዶቿ የሆኑትን አይጦች ስታስበረግግ ኖረች። እየቆዩ ግን ጥርሷ እያደገ፣ ፀጉርዋም እየታወቀ ሄደ፣ ለመደበቅ ብትሞክርም አልተቻላትም። ወደ ቀደመው ኑሮዋ እንዳትመለስ አይጥነቱን ረስታዋለች። ያደረገችው ነገር እየፀፀታት ስለመጣ ከሁሉም ለመራቅ ስትል በለሊት ብቻ መንቀሳቀስ ጀመረች ይባላል። *የለሊት ወፍ አይጥም ወፍም* ሆና የኖረችው በዚህ ጠባይዋ ነው ይባላል።

ትናንት የሰሩት ነገር *« ጥርሱ እየበቀለ፣ ፀጉሩ ብቅ አለ»* እያስቸገራቸው ስንቶች ወጥኛ መከራ እያዩ ነው። ውስጣቸው አይጥ ሆኖ ላያቸው ወፍ እየሆነ፣ እንደ አይጥ እያሰቡ፣ እንደ ወፍ ሊሰሩ እየሞከሩ፣ መጨረሻቸው በጸጸት ጨለማ ውስጥ መሰወር ይሆናል።

የእስክንድርን ታሪክ የፃፈው የግብፁ ንጉሥ በትሊሞስ እንዲህ ይተርክልናል። በአንድ ትንሽ ጦርነት የእስክንድር ጦር እዙ ጉዳት ደርሶበት አሸነፈ። የዚህ ጦርነት ጉዳት ያንገበገበው አንድ ወታደር፣ *«የአመራር ድክመት ባይኖር ኖሮ ይሽን ጦርነት ለማሸነፍ ይሽን ሁሉ መሰዋዕትነት መክፈል አያስፈልግም ነበር»* ብሎ በመተቸቱ ተከስሶ እስክንድር ዘንድ ቀረበ። *«ይሽ ዓይነቱ ሐሳብ ጦሩን ያዳክማል፣ ጠላትን ያስደስታል፣ መደፋፈር ያመጣል፣ ለሌሎች ከፉ አርአያ ይሆናልና ወታደሩም ይቀጣ፣ ሐሳቡም ስህተት መሆኑ ይነገር»* ብለው ጀኔራሎቹ እስክንድርን ወጥረው ያዙት።

ታላቁ እስክንድርም ፣፣ «እንደ ንጉሥነቴ ይሽ ሰው ጥፋተኛ ነው፣ የሰነዘረውም አስተያየት ስህተት ነው፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ደግሞ ይሽ ሰው ትክክል ነው፣ እኛ ጥፋተኞች ነን። እኔ ደግሞ እንደ ንጉሥነቴ ስሆን እንደ እውነቱ ፈርጃለሁ፣» ብሎ ተናገረ። እኛስ?

፳የ፫ እንዴት አለፈ?

አናንያ-ከአዲስ አበባ

ባሳለፍነው የኢትዮጵያ 2005 የፊረንጆቹ 2013 ዓ.ም በሐገር ውስጥ በርካታ የመነጋገሪያ እና በተለያዩ የሐገር ውስጥ፣ እንዲሁም የውጭ መገናኛ ብዙኃን ትኩረት የሰጡባቸው ዓበይት ጉዳዮች ነበሩ። ከእነዚህም ውስጥ ‹‹አንኳር ነበሩ›› ካልኳቸው ሁነቶች የተወሰኑትን መርጬ ለናፍቆት ኢትዮጵያ አንባቢያን ማበርከት ወደድኩ።



ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኑ

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ መለስ ዜናዊ ሕይወታቸው ያለፈው በ፪ሺ፭ ዓ.ም ማብቂያ ላይ ቢሆንም በታቸው ከፍት እንደሆነ እስከ ፪ሺ፮ ዓ.ም ድረስ ቆይቶ ነበር። ቦታቸውን በጊዜው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበሩት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ሸፍነው ቢይዙትም በፓርላማ ቀርበው ቃለ-መሐላ ያልፈፀሙ ከመሆናቸው አንፃር የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ማን ሊይዘው ይችላል? የሚለው ጥያቄ ለብዙዎች ከመላምት እና ከግምት ውጪ የዘለለ ምላሽ አልነበራቸውም።

በዚሁ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ግን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ለዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ለአቶ ደመቀ መኮንን በማስረከብ በይፋ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነው ቃለ መሐል የገቡበት እና በይፋ መሾማቸው ለሕዝብ የገለፀው በዚሁ ባሳለፍነው ፪ሺ፭ ዓ.ም. እንደነበር አይዘነጋም።




ጁነዲን ሳዶ ኢህአዴግን ከዱ

በገዢው መንግሥት አሮሚያ ተበሎ በተሰየመው ክልል አፋሲ ለተወለዱትና በተለያዩ የሚኒስቴርነት ቦታዎች እንዲሁም የአሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት በመሆን ላገለገሉት አቶ ጁነዲን ሳዶ 2005 ዓ.ም ጥሩ ዓመት አልነበረም። ባለቤታቸው ‹‹ሕገ-ወጥ በሆነ ድርጊት›› ተሳትፈዋል ተብለው በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ተከትሎ ‹‹ባለቤቴ ንፁህ ናት። እንዲህ አታደርግም›› ሲሉ በተለያዩ የማል ጋዜጦች ላይ ምላሽ መስጠታቸውን ተከትሎ ከአውራው ፓርቲ ከኢህአዴግ ጋር ቅራኔ ውስጥ የገቡት ጁነዲን በሂደት ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ሆነዋል።

ባለቤታቸው ወ/ሮ ሀቢባ መሐመድ ከሳዑዲ አረቢያ ኤምባሲ ብዛት ያላቸው ቁርአኖችንና 50 ሺ ብር ይዘው ሲወጡ እጅ ከፍንጅ መያዛቸውን ተከትሎ አቶ ጁነዲን በፃፉት ደብዳቤ የእናታቸውን ኑዛዜ ለማስፈፀም /መስጊድ ለማሠራት/ እርሳቸውም ‹በሌላ ደብዳቤ› ከተለያዩ ኤምባሲዎች የብር ድጋፍ ሲጠይቁ መቆየታቸውን አምነው ነበር።

አቶ ጁነዲን ባለቤታቸው ከታሰሩና እርሳቸውም ከስልጣን መነሳታቸውን ተከትሎ ወደ ኬንያ መሰደዳቸው እየተዘገበ ቢሆንም ‹‹ወደ ኬንያ ሲያመሩ ተገድለዋል›› የሚል አሉባልታም በስፋት እየተናፈሰበት ዓመት ነበር።



የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት አባቶች እሰጣ ገባ በአሜሪካና ኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን አባቶች መካከል ተፈጥሮ የነበረው አለመግባባት የተካረረ ደረጃ ላይ ደርሶ ከነበረባቸው ጊዜያቶች ውስጥ አንዱ 2005 ዓ.ም ነበር። ኢህአዴግ አዲስ አበባን መቆጣጠሩን ተከትሎ በስደት ወደ አሜሪካ በተጓዘው ‹ሲኖዶስ› እና የአቡነ ጳውሎስ ሹመት ተከትሎ የታዋቀረው አዲሱ ፓትሪያርክ ያለምንም መግባባት ከ20 ዓመታት በላይ ከቆየ በኃላ ለአዲሱ የተጋጋለ ውዝግብ መነሳት ምክንያት የሆነው የአቡነ ጳውሎስን እረፍት ተከትሎ ነበር።

ከአቡነ ጳውሎስ በኃላ ቤተ ክርስቲያኒቱን የመምራት ኃላፊነቱ ቀደም ሲልም ያለአግባብ ለስደት የተዳረጉት አቡነ መርቆሬዮስ መሆን አለባቸው ከሚሉት በተጓዳኝ ምርጫው እንደአዲስ መካሄድ አለበት በሚሉ ሁለት ወገኖች መካከል ተፈጥሮ የነበረውም ውዝግብ የጅማ ሐገረ ስብከት ፓትሪያርክ የነበሩት አቡነ ማቲያስን 6ኛው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ፓትሪያርክ አድርገው በመምረጥ ተጠናቋል።

የሁለቱን ሲኖዶሶች ውዝግብ አስመልክቶ ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ሁለቱ ወገኖች እርቅ እንዲያወርዱ የሚጠይቅ ደብዳቤ ጽፈው የነበረ ሲሆን ‹መንግስት በዚህ ጉዳይ ጣልቃ ሊገባ አይገባም› የሚሉ ወገኖች በመነሳታቸው ደብዳቤያቸውን መሠረዛቸውን ገልፀዋል።

አክሰስ እና ኤርሚያስ አመልጋ



እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ የተለያዩ የቢዝነስ ውጥኖችን በመያዝ ከሚኖሩበት አሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት አቶ ኤርሚያስ አመልጋ ሠማይ ነክቶ የነበረው ስማቸውና ቢዝነሳቸው ዶማ አመድ የሆነበት አመት ነበር፤ 2005 ዓ.ም. ። ከአነስተኛ የዘይት ፋብሪካ አንስቶ እስከ ዘመን ባንክ ብሎም እስከ አክሰስ ሪል ስቴት የዘለቀው የአቶ ኤርሚያስ ቢዝነስ መንኩታኮት የጀመረው የዘመን ባንክ ፕሬዝዳንት ከመሆን መነሳታቸውን ተከትሎ ነው የሚል አስተያየት የሚሰነዘርባቸው ሲሆን ከአንድ አመት ከ6 ወር ባልበለጠ ጊዜ ገንብቼ አስረክባለሁ ሲሉ በአክሰስ ሪል ስቴት ስም የሠበሰቡት ከ1.3 ቢሊዮን ብር በላይ የት እንዳዳረጉት ሳይታወቅ አሳቸውም ሐገር ለቀው ተሰደዋል።

የ5 ልጆች አባት የሆኑት አቶ ኤርሚያስ በአገር ውስጥ የተቀሰቀሰባቸውን ተቃውሞ ተከትሎ ወደ አገር ቤት እንደሚመለሱ ሲገልፁ ቢሰነብቱም የውሃ ሺታ ሆነው ከቀሩ እነሆ ወራት እየተቆጠሩ ነው።

የአባይ አቅጣጫ መቀየር፤ የግብፅ ዛቻ እና የኢትዮጵያ መንግስት ቁጣ




እለተ ማክሰኞ ግንቦት 20/2005 ዓ.ም በይፋ የተከናወነው እና ለታላቁ የህዳሴ ግድብ መሠረት ነው የተባለለት የአባይ ግድብ አቅጣጫ የማስቀየስ ተግባር ለኢትዮጵያውያን ተስፋ፣ ለግብፃውያን ደግሞ ተስፋ አስቆራጭ ነበር።

የግብፅን ከፍተኛ ባለስልጣናት ያስቆጣው ይኼ የአቅጣጫ ማስቀየስ ሥራ በግድብ ሥራ ወንዝ መቀልበስ ወይም River Diversion በጣም ወሳኝ ከሆኑ ሥራዎች አንዱ ሲሆን፤ ይህንን ለማሳካትም ዲዛይን ለውጥ በማድረግ ክረምት ከቢጋ ግድቡ አካባቢ መስራት በሚያስችል ሁኔታ የተሠራ ሲሆን፤ የማስቀየሻ ካናሉ እስከ 14700 m3/5 ውሃ የማስተላለፍ አቅምም ይኖረዋል። ከግድቡ ሥራ ጋር በተያያዘ እስካሁን በአጠቃላይ ከ6 ሚሊዮን ሜትር ኩብ በላይ የደረሰ ሲሆን፤ በግራና በቀኝ ያሉ የኃይል ማመንጫ ቤት ቁፋሮም እስከ 1.7 ሚሊዮን ሜ/ኩብ ደርሷል።

ይህን ተከትሎ የግብፅ ሚኒስቴሮች ካቢኔ ፕሬዝዳንቱን ጨምሮ አስቸኳይ ስብሰባ ያደረጉት እና ‹‹የኢትዮጵያ ግድብ የጦርነት አዋጅ ነው›› ለማለት ወሰኑ። ይሄ ስብሰባ በመጀመሪያ ‹‹ቡቴሊቪሽን ይተላለፋል›› የተባለ ሲሆን በመቀጠል እንዳይተላለፍ ቢወሰንም እስካሁን ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ መሉ ስብሰባው ቡቴሊቪሽን ሊተላለፍ የቻለ ሲሆን፤ በስብሰባቸውም ላይ ‹‹የኢትዮጵያን የህዳሴ ግድብ በጦር ጀት መምታት፣ አሸባሪዎችን እና ተቃዋሚዎችን በመደገፍ ሐገሪቷን ማስበጥበጥ፣ ግብፅ ዘመናዊ የጦር ጀቶችን እየገዛች ነው በማለት ማስወራትና ማስፈራራት እንዲሁም የግብፅን የደህንነት ኃይል በመጠቀም ግድቡን ማፍረስ›› የሚሉ ዋና-ዋና አቅዶቻቸውን ሲወያዩ በስህተት ቡቴሌቪሽን ሊተላለፍ በቅቷል።

በስተመጨረሻ የግብፅ ባለስልጣናት ‹‹በስህተት የተላለፈ ፕሮግራም እና የግብፅን ሕዝብና መንግስት አቋም የማይወክል አባባል ነው›› ቢሉም ጉዳዩ የኢትዮጵያን መንግስት ያስቆጣ ሆኗል። የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ የሚገኙትን የግብፅ አምባሳደር ጠርቶ ያነጋገር ሲሆን፤ በአስቸኳይ የሐገራቸውን አቋም እንዲያሳውቁም ጠንከር ያለ ትዕዛዝ ያስተላለፈው በዚሁ ባሳለፍነው ዓመት ነበረ።

ሙሠኞቹ ባለስልጣናት



‹‹አንቱ›› የተባሉት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አመራሮች አቶ መላኩ ፈንታ እና አቶ ገ/ዋህድ ገ/መድህን ባላሰቡትና ባልጠበቁት ሰዓት ከቢሯቸው ተገፍትተው ካቲና የገባላቸውና ወደ እስር ቤት የተወሰዱት ባሳለፍነው 2005 ዓ.ም ነበር። ሁለቱ አመራሮች ሕዝብና መንግስት የሰጣቸውን ኃላፊነት ለግል ጥቅማቸው በማዋልና ከሌሎች ባለሐብቶች ጋር በመመሳጠር የሐገርና የሕዝብ ገንዘብ ሲቦጠቡጡ መከረማቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ፍ/ቤት ያቀማቸው የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ‹‹እስካሁንም የዘረፉትን ለቅሜ አልጨረስኩም›› ሲል የጊዜ ቀጠሮ እየጠየቀባቸው ይገኛል።

በተለይ አቶ ገ/ዋህድ ለእስር የተዳረጉት ብቻቸውን ሳይሆን ከባለቢታቸው ኮሎኔል ሃይማኖት፣ እንዲሁም ከእህታቸው ጋር በጎበረት ነው። በአጠቃላይ በእነ አቶ ገ/ዋህድ የክስ መዝገብ ከ60 ያላነሱ ተከሳሾች ሲኖሩ እስከዛሬ በአገራቱ ከተወሰዱ የሙስና የክስ ሂደቶች በትልቅነቱ የሚጠቀስም ሆኗል።



ኃይሌ ገ/ስላሴ እና ፖለቲካ

በ5 ሺ እና 10 ሺ ሜትር የሩጫ ውድድሮች ለተከታታይ ዓመታት የራሱንና የአገሩን ስም ሲያስጠራ የቆየው ኃይሌ ገ/ስላሴ ባለፈው 2005 ዓ.ም ደግሞ በሌላ አጀንዳ መነጋገሪያ ለመሆን በቅቷል።

እ.ኤ.አ በ2010 በጉልበቱ ላይ ያጋጠመውን ሕመም ተከትሎ ከሩጫ ራሱን እንዳገለለ ሲነገር ቢቆይም ቆየት ብሎ በተሰማው መረጃ የኃይሌ ከሩጫ ራሱን ማግለል ዋነኛ ምክንያቱ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን ካለው ፅኑ ፍላጐት መሆኑ ተረጋግጧል።

በቀጣይነት በሚካሄድ ፕሬዝዳንታዊ ውድድሮች ላይ ተሳታፊ ለመሆን እቅዱ እንዳለው የሚናገረው ኃይሌ የበርካቶችን ድጋፍ ሊያገኝ እንደሚችልም ታምኖበታል። ኃይሌ፡- ኤደን፣ ሜላት፣ ቤቲ እና ናታን የሚባሉ የ4 ልጆች አባት ሲሆን፣ በስሩ በሚያስተዳድራቸው ድርጅቶች ከ600 በላይ ሠዎች ይተዳደራሉ።



ቤቲ እና ቢግ-ብራዘር አፍሪካ

‹‹ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን አዋርዳለች›› በሚል ታላቅ የድረ-ገፅና የሚዲያ ተቃውሞን ከቀሰቀሱና የ2005 አስገራሚ ክስተቶች ውስጥ የሚጠቀሰው የቤቴልሔም አበራ የቢግ ብራዘር ከራሞት ነበር። በደቡብ አፍሪካ በሚካሄደው የ2012 ቢግብራዘር አፍሪካ ላይ ኢትዮጵያን ወክላ የተሳተፈችው ቤቲ ፕሮግራሙ ቡቲሊቨሽ›ን እንደሚተላለፍ እያወቀች ‹‹እርቃኗን ለዓለም ታይታለች። ወሲብም ፈፅማለች› መባሉ ነበር ትልቅ ውዝግብ የቀሰቀሰው።

ለ91 ቀናት በሚቆየው ‹የሪያሊቲ ሾው› ላይ ለ29 ቀናት የቆየችው ቤቲ ‹‹ለ2 ጊዜያት ያህል በግልፅ ወሲብ ፈፅማለች›› ብትባልም እሷ ግን ‹‹ፕሮግራሙ የሪያሊቱ ሾው በመሆኑ አስመሰልኩ እንጂ አልተወንኩም›› ስትል እርስ በርሱ የሚቃረን መግለጫ ሰጥታለች። በኤም.ኤት የሚተላለፈው የቢግ ብራዘር አፍሪካ ውድድር ከ12 አገሮች የተውጣጡ ተወዳዳሪዎች ተሳትፈውበት ነበር።



ጋሽ ተስፋዬ ለማ


አንዳንዶች የኢትዮጵያ የባሕል መዝሙ አባት የሚል ስም ሲሰጡት ብዙዎች ደግሞ የኢትዮጵያን አጠቃላይ የመዝሙ ዘርፍ ሕይወት የዘራበት ታላቅ የመዝሙ ሰው ይሉታል። ጋሽ ተስፋዬ ለማ ገና በአፍላ ዘመኑ «አርኪስትራ ኢትዮጵያ» የተባለውን የመጀመሪያውን የመዝሙ ባንድ የመራና በኃላፊነት ለታላቅ ደረጃ ያበቃ በኢትዮጵያ የመዝሙ ዓለም ታላቁን አሻራ ተክሎ ያለፈ ሰው ነበር።

ጋሽ ተስፋዬ የቀድሞውን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአሁኑን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የመዝሙ ባንድ በመራባቸው ዓመታት፣ የኢትዮጵያ የባሕል መዝሙ በአጠቃላይ የጎበረተሰቡንም ሆነ የሌሎች ተቀባይነት እና ተሰሚነት ማስገኘት ባስቻሉ ሥራዎቹ ይወደሳሉ። ጋሽ ተስፋዬ ለማ ከአርኪስትራ ኢትዮጵያ በኋላም በተለያዩ የመዝሙ ተቋማት ባከናወናቸው ሥራዎቹ፣ ባፈራቸው ታዋቂ ድምፃውያን እና እንዲሁም ጥላሁን ገሠሠን ጨምሮ ለገናና ድምፃውያን በፃፋቸው የመዝሙ ድርሰቶቹም ይታወቃል።

2005 ካሳጣን ታላቅ ሰው ማንባር ቀደሙ የነበረ የጥበብ ሰው ሲሆን፣ በሕይወት እያለ ለ12 ዓመት ተኩል በቆየበት በነርሲንግ ሆም ሲደክምበት የነበረው የ«ኢትዮጵያ መዝሙ ታሪክ» የሚለው መጽሐፉ ከእሱ ሕልፈተ ሕይወት በኋላ ለኅትመት በቅቷል።

የጋሽ ተስፋዬን መጨረሻ ከሁሉም ለየት የሚያደርገው በባሕላችን እንደማንኛውም ሰው ወዳጅ ዘመዶቹ ባሉበት ለቀብር ያለመብቃቱ ነው። በብዙዎች አእምሮ ውስጥም ይኸ ሰው ያለምክንያት ሬሳው እንዲቃጠል ኑዛዜ አልተወም የሚል ጥያቄ ያጭራል።

በእርግጥ ጋሽ ተስፋዬ ሬሳው እንዲቃጠል የተናዘዘው በሕይወቱ እያለ በወገኖቹ ላይ ባየው ቅሬታ ነው ወይስ ሌላ ምክንያት አለው? ባልተለመደ መንገድ ይኸን ኑዛዜ ጥሎ ያለፈው ጋሽ ተስፋዬ ለማ በሕይወቱ እያለ ለምን በሥርዓት መቀበር እንዳልፈለገ እና ምክንያቱን በራሱ እጅ ጽሑፍ እና ፊርማ ጥሎ አልፎ ይሆን? ይኸ ኑዛዜ ካለስ በማን እጅ ይገኛል? ለሁሉም 2005 ዓ.ም የጎልፈቱ መጨረሻ ቢሆንም ዘመን የማይዘነጋውን ሥራውን ግን ጥሎልን አልፏል።



የድምፃዊ አበበች ደራራ እና እዮብ መኮንን ድንገተኛ ሕልፈት

ለኪነ ጥበብ አፍቃሪያን 2005 ዓመት እጅግም ብዙ አስደሳች አልነበረም፡፡ ሐገር ውስጥ ባለመኖሯና ቀብሯ በውጭ ሐገር በመፈፀሙ በሐገር ውስጥ ብዙ የሚዲያ ሽፋን ባይሰጠውም ታዋቂዋ ድምፃዊት አበበች ደራራ ያረፈችበት ዓመት ይሄው እያነሳነው ያለው 2005 ዓ.ም. ነበር፡፡


በሐገር ውስጥ ከፍተኛ ድንጋጤና ለበርካቶች ሐዘን የነበረው የድምፃዊ እዮብ መኮንን ሳይታመም፣ ሳይተኛ በድንገተኛ ሁኔታ በስትሮክ በሽታ ከሞት የመለየቱ ዜና ነበር፡፡

በአድናቂዎቹ ዘንድ ‹‹እዮብ ቦብ›› እየተባለ የሚጠራው መዚቀኛ እዮብ መኮንን የመጀመሪያ አልበሙ የሆነውን ‹‹እንደቃል›› የተሠኘውን አልበም ካወጣ በኋላ በበርካታዎች ዘንድ ተስፋ የተጣለበት እና በአጭር ጊዜም ዘፈኖቹን ለትውልድ መገንቢያ እና መቅረጫ እንዲሁም መልካም ተግባራትን ማወደሻ በማድረግ መስራት የጀመረ እና ተወዳጅ ባህሪ የነበረው ድምፃዊ ነው፡፡



እዮብ መኮንን ነሐሴ 7 ቀን 2005 ረፋዱ ላይ የእህቱን ልጅ ትምህርት ቤት አድርሶ ወደቤቱ በመመለስ የበሩን መጥሪያ እየደወለ ሳለ በድንገት ራሱን መሳቱን ተከትሎ ወደ ቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ቢወሰድም ህመሙ ‹ስትሮክ› የተባለው በመሆኑ ከሐገር ውጪ ህክምና መውሰድ እንዳለበት በመታወቁ በሐገሪቱ ያሉ ግሞ ይህን አገልግሎት የሚሰጥ ‹‹የአውሮፕላን አምቡላንስ›› ባለመኖሩ ከኬንያ ተጠርቶ ወደዚያው በማምራት ህክምናውን እንዲከታተል ተስፋ ተደርጉ የነበረ ቢሆንም እዮብ ኬንያ ከደረሰ በኋላ ነሐሴ 12/2005 ዓ.ም. ሕይወቱ ልታልፍ ችላለች፡፡


ድምፃዊ እዮብ መኮንን በወጣትነት እና ብዙ መስራት በሚችልበት ዕድሜው ነሐሴ 14/2005 ዓ.ም. አድናቂዎቹ፣ ወዳጆቹና ቤተሰቦቹ በተገኙበት በመንበረ ቅድስተ ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ስርዓተ ቀብሩ ተፈፅሟል፡፡



የታላቁ የታሪክ ሊቅ ሕልፈት

በተለይ የኢትዮጵያ ታሪክ ሲፃፍ የውጭ ሐገር ሠዎች ከሚፅፉት የሐገር ውስጥ የታሪክ ምሁራን እንዲፅፉት ምክርና ተግሳፅ ይሰጣሉ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በማስተማርና በመመራመር ረጅም ዓመት የቆዩት ፕሮፌሰር ታደሠ ታምራት ከሚጠቀስላቸው ተግባራቸው አንዱ የኢትዮጵያን ጥናትና ምርምር ተቋም እንዲመሠረት አስተዋፆኦ ካደረጉ አካላት መካከል አንዱ እርሳቸው እንደሆኑ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኋላ ወደ አሜሪካ ያቀኑት ፕሮፌሰር ታደሰ ረጅም ጊዜ ማለትም እስከ ህልፈተ ህይወታቸው ድረስ እዚያው ነበሩ፡፡ በቆይታቸውም የካበተው የታሪክ እውቀታቸውን በልዩ- ልዩ ዩኒቨርስቲዎች ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- በካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ፣ እንዲሁም የክብር ተጋባዥ መምህር ሆነው ኖርዝ ዌስተርን ዩኒቨርስቲ እና ኤሊዮን ዩኒቨርስቲ ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ በጥናቶቻቸውም ታላቅነት አለም አቀፍ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ ከሠሯቸው ጥናቶችና ዕውፎች መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡-



የፕሬዝዳንት ግርማ ወሰኪና የሽንጥ ሥጋ

እስቲ ወደ መጨረሻው ትንሽ ፈገግ ብለን ዕውቆችንን ብንቋጭስ?

በከባድ የሚታለል ወንጀል፣ ሥልጣን አላግባብ በመጠቀምና በሌሎች አምስት ወንጀሎች ተጠርጥረው ክስ የተመሠረተባቸው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር ሊቀመንበር ሊቀ ትጉሃን አስታጥቁ አባተ መከሰሳቸውን ተከትሎ እጃቸው እንዲያዝ ትዕዛዝ መውጣቱን ተከትሎ ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ አንድ አስደናቂ ደብዳቤ ፃፉ፡፡ የደብዳቤው ይዘት ከሞላ ጎደል እንዲህ የሚል ነበር፡- ‹‹ተከሳሹ ለሐገራቸው ለዐላዊነት በጹር፣ በገደል ያደረጉት ተጋድሎ ታሳቢ ሆኖላቸው ፋይሉን እንድትዘጉ›› የሚል ነበር፡፡ ይህን የሰሙ የፍትህ ሚኒስቴር ሠዎች ያኔ መሳቅ የጀመሩ አሁንም አላቆሙም እየተባለም ይነገራል፡፡

የፕሬዝዳንቱ ጥያቄ ውድቅ ከሆነ በኋላ አንድ አስደንጋጭ መረጃ ለህዝብ ይፋ ሆነ፡፡ እሱም ለክቡር ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ አመት በዓልን ምክንያት በማድረግ ሙሉ ሽንጥ ሥጋ እና ችቭዝ ውስኪ ተከሳሽ ግለሰቡ ከሚመሩት ድርጅት ወደ ቤተ መንግስት ይሄድ እንደነበር ወጪውም አግባብነት፣ ግልፅነት የጎደለው መሆኑን በማስረጃ የሚያሳይ ነበር፡፡

ይታያችሁ ፕሬዝዳንቱ የበሉበትን ወጪት ሠባሪ ላለመሆን ‹‹ሠወየው አይታሰሩ›› አሉ ግዴለም የእሳቸው ይሁን! ‹‹መንግስት ፕሬዝዳንቱን እንኳን መመገብ አቃተው እንዴ?›› ሲሉ ሚዲያዎች መንግስትን ወረፍ ያደረጉባት አዝናኝ የዓመቱ ታሪክ ነበረች፡፡

መጪው ዘመን ሰላም፣ ፍቅር፣ መተሳሰብ አምጥቶልን ደግሞ ለዓመቱ ቸር ወሬ ያሰማን!!

ጎና ጤና

ይኽ ገፅ ለጎበረተሰቡ በእጅጉ ሊጠቅሙ የሚችሉ ጤና ነክ የሆኑ ፅሁፎች የሚቀርቡበት ሲሆን ገፀ ለሙያው ቅርበት ያላቸው መሉ ተሳትፎ የሚደረገበት ነው::



ክንፈ ገበየሁ (ዶ/ር)
kgebeyehu@comcast.net

አንደበት ሲፈተን

አንደበት

ቢያሰሉት ቢመረምሩት
ቢተቹት ቢገነዘቡት፣
ቢያነሱት ቢጥሉት
ቢከፋፍሉት ቢሸነሽኑት፣
ይቻላል ወይ ሊረዱት
ሊደርሱበት ሊያውቁት።

ለምን አንዱ ትሁት፤ ሰው አፍቃሪ ሆነ
ለምንስ ለሰው መብት ትክክል በየነ
ለምን ያኛው ደግሞ በሰው ላይ ጨከነ ?

ይሄኛው ሲነደው የተበደለ ሲያይ
ጊዜ አጥቶ ፍርድ አጥቶ ተቆራኝቶት ስቃይ፣
የዚያኛው አንደበት ለምን ይሳነዋል
ትክክል አይደለም ማለት ይጨንቀዋል።

ገንዘብና ስልጣን ጊዜ እሚያፈራቸው
ለበዙት ግብ ሆነው ቀድሞም ያለሚቸው፤
ለጥቂቶች ደግሞ ሰብአዊ ግባቸው
የሌሎችን ችግር መፍቻ መሣሪያቸው።

መሆኑ ለምን ነው ንገሩኝ ልረዳ
አንዱ አፍቃሪ ቸሪ ለመብት የሚጎዳ
ሌላው የማያየው የወንድሙን ፍዳ።
ለምን ይሆን አንዱ ሁሉ ተሳክቶለት
ሃብቱ ወሰን አጥቶ ካብ በካብ ሆኖለት:

እንዲኖረው ሌላም፤ ችግር እንዳይገጥመው
ሁሌ ተስተካክሎ ሜዳው መጋለቢያው፣
ኧረ ለምን ይሆን ? ያኛው መቆርቆዙ
ሃብትስ ይቅር ይቆይ፤ መጥፋቱ ደም ወዙ።

መጠጊያ ተስኖት በብርድ ሲንገላታ
ተስፋው መሚጠጡ የጨጋው አለኝታ።

ባለንበት ዘመን ዓለም ተቀራርቧል
አንዱ ያንዱን ችግር መፍታትም ጀምሯል፤
ሲባል የነበረ፤ ነው ወይ ለይስሙላ
እንዲያው ለማስመሰል ችግር መፍቻ መላ።

ካፈጣጠር ይሆን ወይስ ካስተዳደግ
ወይስ ካካባቢ ካልበቀለበት ደግ፣
ወይስ ከመምሕሩ ቀድሞ ካመኑበት
አመዛዝኖ መቅሰም በሚያስቸግርበት
ወይስ ከመጻፉ አንበበው ካወቁት
ግንዛቤ አልባ አምነው ካጸደቁት፣
አያስቸግራችሁም ፍርድ ሲገማደል ?
ተፈጥሮ ያስገኘው በሰው ሲከለከል።

የሰው አንደበቱ መዘበራረቁ
ስልጣኑን ገንዘቡን ከቢጤው ማድነቁ፤
እስቲ እንመራመር ምን ፈጠረው ይሄን
ከጽንስ ካስተዳደግ ካካባቢስ ይሆን ?

ግጥሚን መንደርደሪያ ካደረግን እስቲ አንደበትን ሊወስኑ ይችላሉ ብለን የምንገምታቸውን አንዳንዶቹም ላይ በዛ ያለ የሳይኮሶጂ ጥናት የተደረገባቸው በመሆናቸው ልናምንባቸው ስለቻልናቸውም ጭምር ገባ ብለን እንመልከት:-

አንደበት አእምሮ ወይም አንጎል ማለት ብቻ እንዳልሆነና በተለይም የስሜት የፍርድ አሰጣጥና የሚዛናዊነትን ተግባር የሚያካትተው የአእአምሮ ክፍል አሠራር መዳበርና አለመዳበርን አጠቃሎ የሚይዝ፤ የችግርን አፈታት በብዙ አቅጣጫ ለመመልከት የሚያስችል የአእምሮአችን ረቂቅ አስተሳሰብ ነው። የትም ይወለዱ፤ ወይም ይደጉ በዓለማችን ብዙዎች ሰዎች የተመሳሰለ ወይም የተቀራረበ የአንደበታዊ ተግባር አመራር አላቸው።

ለምሳሌ መንገድ ይዘው ተቻኩለውም ቢሆን የሚጓዙ ተላላፊዎች አንዲት በምርኩዝ የሚያዘግሙ አዛውንት ከፊታቸው ቢወድቁ፤ ተጣድፈው ለማንሳትና ለመርዳት ለማረጋጋት የማይሞክሩ እጅግ ጥቂቶች ናቸው። ከአዛውንቷ ኋላ አንደኛና ሁለተኛ የሆኑት ሮጥ ብለው እርዳታ በመስጠት ፊንታ ተራምደው ቢያልፉ ያንደበት ሚዛናዊ ተግባራቸው መጓደሉን ገላጭ ነው። ራቅ ብለው በስተኋላ የነበሩት ደግሞ ቆም ብለው መልከት ሳያደርጉ አዛውንቷ መረዳታቸውን ሳያጣሩ እነሱም ቢያልፉ እንዲሁ ሊፈረጁ ይችላሉ። አየት አድርገው ሌሎች የሚረዳ መሆናቸውን ተገንዝበው የነሱ አስተዋጽኦ የማያስፈልግ ነው ብለው አምነው እንደሆን ያለፉት መፈረጃቸው ሊያውክ ይችላል።

እንግዴህ ይህን ቀለል ያለ ያልተመሳቀለ ሁኔታ ለመግቢያ በምሳሌ እንውሰድ እንጂ መልካም አንደበት በዛ ያለ አንዳንዴም ብዙዎች የተሳሰሩ ሁኔታዎች ሲገጥሙ መፍቻ ስሜቶችን ነን ለነን በማስቀመጥ የፍርድ ሚዛንን አስተካክሎ ለመውሰድ ለአመራረጡ ብቁ የሚያደርግ የአእምሮ ብስለት ነው። የአንደበት አለመዳበር ለየግል ሰዎችም ሆነ በማሕበር ላይ፤ በግልም ሆነ በህብረት አሠራር፤ በሐገር አመራር፤ በዓለም ደረጃ ደግሞ የዓለም ቤተሰብነት ስሜት መስፈንና አለምስፈን በሚታዩ ውጤቶች ሊለካ ይቻላል። መልካም ያንደበት አሠራር የሌሎችን ጉዳት፤ ችግር፤ ፍርሃት፤ ጭንቀት፤ ስቃይ ፤ ብቸኝነት፤ ለመፍታት ያስችላል። የተዛባ ወይም የተጓደለ ያንደበት ብስለት ደግሞ ለነሺህ ለተዘረዘሩት በሰው ላይ ለሚደርሱ ችግሮች የስሜት መፍቻ ቁልፉ ቅርብ አይደለም።

ያንደበት ብስለት ማጸጽ ሰብአዊ ተግባር ከስልጣንና ከጥቅም ጋር የሚሻኩት ወይም የሚቃረን ከሆነ ከግንዛቤ እንዳይወሰድ ያስደርጋል። በዓለማችን ታሪክ አንበጋን የተረዳናቸው በሰው ልጅ በደረሱ የጭካኔ ተግባራት የተገለጹ ማስረጃዎች ብዙዎች እንዳሉ እናውቃለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ መወለድ ምክንያት የስልጣን መቀማት አስተሳሰብ ያሸነፈው ንጉሥ ሔሮድስ ሁለት ሺ ሕጻናት ማስፈጀት ፤ በዓለም ታሪክ የሂትለር ያልመሰሉትን ሁሉ በጭካኔ መፍጀት፤ የሙሶሊኒ በመርዝ ጋዝ ፍጀ በኢትዮጵያ ይዘታን ማስፋፋት ሙከራ፤ ባገራችንም ቀደም ያለ ታሪክ የየዲት የእልቂት ተግባር ወደአእምሮ መታወክነት ፍንጭ ቢሰጡም፤ የተቀነባበረ የተቀናጀና ለወራትና ለዓመታት በስልት ሌሎችንም በማሳመን በማስገደድም በምሪት የሚፈጸሙ የጭካኔ አሠራሮች "ሳይኪፓት" በሚል ከተጠያቂነት በማያደን ሁኔታ የተጠመዱ ይሆናሉ ያሰኛል። የአእምሮ (የተዘበራረቀ ያስተሳሰብ) በሽታም በመጠኑ አልፎ አልፎ በሌላው ላይ አስከፊ ሁኔታዎችን ሊያስደረግ ቢችልም ልዩነቱ ይሄኛው በሃሳብ ተቀነባብሮ አድራጎቱና ውጤቱ ለሚያስገኘው ውጤት ታቅዶ ሳይሆን የድምጽም ሆነ የእይታ ስሜት አንዳንዱም ሊጎዳኝ መጣ በሚል በተሳሳተ አስተሳሰብ ሊደረግ የሚችል ነው።

የሁለቱን ልዩነት ከሞላ ጎደል መለየት በተለይ ለአእምሮ ባለሙያዎች ላይከብድ ይችላል። የአእምሮ መታወክ ባለሙያዎች እነዚህን በመለያየት ለፍርድ አሰጣጥ እንዲረዱ ብዙ ጊዜ ይጠየቃሉ። የአርአስታችን ትኩረት ከነዚህ ደረጃም ሳይደርስ የሕብረሰቡ አካል በመሆን እጅግ በሚበዛው በሕብረሰብ የሚጠበቀው ሰብአዊ፣ ቅንና ሚዛናዊ የሆነ አፈጻጸም የሚጎድላቸውንና ይህ የአንደበት አሠራር ጉድለት በተለይም ሁኔታዎች ሲለወጡ እንደተዳፈነ እሳት የሚፈነጣቸውን ነው። ይህ እንግዴህ በሐገርና በአሕጉራት በድርጅትም ሊደርስ የሚችል ቢሆንም በየግልና ባንስተኛ በአለታዊ የኑሮ አመራር በሃይማኖታዊም ድርጅቶች ሳይቀር ሲከሰት ኖሮአል፤ ይኖራልም።

የበሰለና ጠንካራ አንደበት ሸልማትም ሆነ ቅጣት ሊያወላዳውና ሊያንገራግረው ያውከዋል። ያንደበት ብስለት ማነስ ወይም አለመኖር በትንሹ ለጥቅም ሥርአትንና የተጠበቀ ኃላፊነትን ያለምንም አድልኦ የሌላውን ጉዳይ መፈጸምን ከጎን ለማድረግ ያስመኛል ያሳስባል ያስፈጽማልም። ከባድ ወይም የረቀቀ ያንደበት ብስለት ደግሞ ከአለታዊ ሚዛናዊ አሠራርና ፍርድ አሰጣጥ ጀምሮ ለራስ ለቤተሰብ ለሐገር መስዋእትነትን እስከመውሰድ ያስደርሳል። በሐገራችን የጣልያንን አገዛዝ ባለመቀበል በዱር በገደሉ ተሰቃይተው አምስት ዓመት የተዋጉ አርበኞቻችን፤ የዚያ ቁንጮ በመሆን ደግሞ፤ ለምኾት፣ ለሹመት፣ ለሽልማት፣ አልገዛም በማለት ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡትን እንደ አቡነጴጥሮስ ሐገሬን አላሳልፍም ብለው የሞቱትን በዛ ደረጃ ለማስቀመጥ ያስችለናል።

እንግዴህ ያንደበትን መበሰልና አለመበሰል በምሳሌ ልንለያይ ጥረት ካደረግን ለዘህ ልዩነት መከሰት ምንና ምን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችሉ ይሆን የሚለውን እንዳስስ፤-

የአንጎል ወይም የአእምሮ ማደግና መዳበር ከእለተጽንስ ጀምሮ ሲሆን በጀን ሊወራረዱ የሚችሉ የአእምሮ እክሎችም እንዲሁ ጽንሱን የእክሉ ወራሽ ሊያደርጉ ይችላሉ ማለት ነው። በተጨማሪ ከመጀመሪያውም ጀምሮ በተለይ እስከ ሦስት ወር ጽንስ ከዚያም በላይ እርግዝና፤ ልዩ ልዩ ለማደጉ እክል ሊሆኑ የሚችሉ መድኃኒቶችና የሱስ እጾች (ኮኬን፤ ሄሮዊን፤ ማሪዋና፤ አልኮል፤ አንዳንድ የሚታዘዙና ያለትእዛዝም የሚወሰዱ መድኃኒቶች) በልዩ ልዩ የጽንስ አካል አንጎልንም ጨምሮ የማደግና የመዳበር እክል ሊፈጥሩ ይችላሉ። ጽንሱ የቫይረስ ወይም የጀርም ኢንፌክሽንም አግኝቶት ከሆነ አንጎልም ሊካካ የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ። ይህም ባይሆን በርግዝና ጊዜ በቂ ለሰውነት እድገትና መዳበር ተፈላጊ የሆኑ የምግብ ዓይነቶች በዛ ላለ ጊዜም ሳያገኝ ቢቀር፤ በመውለድ ጊዜ ሊገጥሙ በሚችሉ ችግሮችም የአእምሮ መዳበር ችግሮች መነሻ ሊፈጠር ይችላል።

ይህ እንዳለ ሆኖ እጅግ የሚበዛው የአንደበት መዳበርና አለመዳበር መፈተኛ ጊዜው ግን ልጅ ከተወለደ በኋላ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ዓመታት በተስተካከለ አመጋገብ፤ የበሽታ መከላከል፤ የቤተሰብ ወይም ያሳዳጊ ፍቅርና መልካም አመራር ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ ሕጻኑም ያለፍርሃት ያለመሸማቀቅ የወላጆቹ አለኝታነትና ሙሉ እምነት እየዳበረበት ያደገ ከሆነ ለመልካም የፍርድ ሚዛን ሰጪነት ብቃት ይኖረዋል። ከዚያም እስከሰባት ዓመት ዕድሜ ይዤው የቤተሰብ ፍቅር ሳይለይ በደረጃ ሃላፊነትን የማስገንዘብ፤ ችግርን መፍታት በመጫጨህ ፣በመወቃቀስ፣ በጠብና በኃይል አለመሆኑን በምሳሌነት በማሳየት፤ ከቤተሰቡና ከትምሕርት ቤት ጓደኞች ጋር የመከባበርና መብትና ግዴታን መጠባበቅ ሰብአዊ ግዴታዎች መሆናቸውን እያወቁ ማደግ ለአንደበት መዳበር መሠረታዊ ግዴታዎች ናቸው።

ልጆች እያደጉ ሲሄዱ በተለይ እቤታቸው ውስጥ እምነትና ፍቅር የሌለ ከሆነ የጓደኞችን መሪነት መከተል የማይቀሬ ነው። አንዱ የአንደበት በመልካም ዳኝነትና በሚዛናዊ አስተሳሰብ አለመዳበር በዚህ ሁኔታ ያደጉ፣ ወጣት የልጆች መሪዎችን የመከተል ግዴታን መቋቋም ያስቸግራቸዋል። ቤተሰብ ታዳጊ ልጆቻቸውን አንደበት በሚዳብርበት አስተዳደግ እየመሩ ቢያሳድጉም ከፍ ከፍ ብለው ከጓደኞች ሊመጡና ሊለውጧቸው ከሚሞክሩ ሁኔታዎች በመከላከል በመርዳቱ የተጉም ሊሆን ይገባል።

ይህ አባባል ልዩ ልዩ አስከፊና ጎጂ ጠባዮችን እንደ መጠጥ፤ የሱስ እጽዋት መውሰድና በነሱም ኃይል የሌሎችን መብት መድፈርን እራስንም በሞትና በሰውነት አደጋ መጎዳት የሚፈትኑ ተግባራትን አጣምሮ በመመልከትና በጥሞና ከታዳጊ ልጆች ጋር በመመካከር ነው።

ጠቅለል አድርገን ለመደምደም ያንደበት መዳበር ባስተዳደግና ባካባቢ ምሪት ችግር፤ ያዋቂ በልጆች ላይ የተደጋገመ ጉዳት (ቻይልድ አብዩዝ) ከቤትም ውስጥ ሆነ ከውጪ በፍርሃት ተሸቆጥቁጦ መብትን ተገፎ የማደግ የሌሎች አስተሳሰብና አባባል ከግንዛቤ በማይወሰድበት አካባቢ ማደግ ሊገታ ይችላል። በመሠረቱ ይህን የመሰሉ ለአንደበት መዳበር እክል የነበራቸው ሁኔታዎች ውስጥ ያደጉ አዋቂዎች በሃላፊነት ደረጃ ታጭተው በሚሠሩበት ጊዜ በየስልቱና ዓይነቱ ሚዛናዊ የሆነ ፍርድን ወይም የሥራ አፈጻጸምን አለመከተል ሊያስቸግራቸው አይችልም። ስነሥርዓትና መብት በሚከበርበት አስተዳደርም አድራጎታቸው በፍርድ ሊያስጠይቃቸውም ይችላል።

እንግዴህ የልጆቻችንን፤ የአንደበት መዳበር በቤተሰብ ደረጃ ካስተካከልን እያደገም ሲሄዱ ከሚገጥማቸው የተሳሳተ ፍርድና ሚዛን በይቅርታም የሚታልፉባቸው ሁኔታዎች በሚሰምሩበት ከመራናቸው ፤ ትክክለኛ ሚዛናዊ ፍርድ እንዲሰጡ የራሳቸውንና የሌሎችንም መብት በመጠበቅ እራስ ወዳድነት ሳያጠቃቸው ለእምነታቸው ለሐገርና ለወገናቸው ታማኝ ዜጎች ሆነው እንዲወጡ የምናደርገው ከመልካም ዜጎች የሚጠበቅ ከፍ ያለ ሃላፊነት ነው።

እንኳን ለኢትዮጵያውያን አዲስ ዓመት በሠላም አደረሳችሁ!!!

